

አርበኞቻችን እና ያሳለፏቸው ፈታኝ ጊዜያት
*በፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም*
③

ይድረስ ለምርጫ 2002 ተላከ ከምርጫ 97
*አቤ ቶኪቻው*
⑩

ኢትዮጵያ፤ሁሌም የምትጨነቅላት አገር
*በብርያን ስትዋርት*
⑤





# አውራምባ ታይምስ

2ኛ ዓመት ቁጥር 85 ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር


- *ለአበበች ጉበና 100 ሺህ ብር ረዳ*
- *«ጃ ያስተሰርያል» ተጠይቆ አልተዘፈነም*
- *በጥላሁን «ዊልቼር» ላይ እቅፍ አበባ አኑሯል*
- *ኤርትራዊ ሙዚቀኞች በባንዱ ውስጥ ተሳትፈዋል*
- *በመንግስት ሚዲያዎች የ«ዜና ሽፋን» አላገኘም*

⑪






ፎቶ ፀሐዬ ጉዛይ (ከአውራምባ ታይምስ)


ቴዲ አፍሮ፡-

# በደማቅ ኮንሰርቱ ፍቅርን ሲሰብክ አመሸ



«መድረክን ለመመስረት አንድነት አሳማውን መስወጥ፣ ስነስርአቱን መሻር የለበትም»
ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም

«የስልጣን ጥምና መጠላለፍ የትብብር መድረኮችን ሲያከስም ኖሯል»
ዶ/ር መረራ ጉዲና
*የወቅቱ የመድረክ ሊቀ መንበር*



⑥ ልዩ ቃለ ምልልስ ⑦

## በውስጥ ገፆች

- *"አንድነት" የዋና ፀሐፊውን አቋም እንደማይጋራ አስታወቀ*
- *ስኬቶች ወደፕሬዝዳንት ኦባማ ወይስ ፕሬዝዳንት ኦባማ ወደ ስኬቶች?*
- *«በዝዋይና ዱግዳ ወረዳ እስካሁን በረሃብ አምስት ሰዎች ሞተዋል»*
  የተከበሩ አቶ ወንድሙ ኢብሳ
- *ሜጀር ጀኔራል ደምሴ ቡልቶና የግንቦት 1981 ዓ.ም መፈንቅለ መንግስት ሙከራ*

# ኤዲቶሪያል

# ለፓርቲ ርእዮተ-ዓለም ሳይሆን ለሕገ-መንግስት፣ለሕዝብና ለህሊናቸው የሚገዙ ህግ አውጪዎችን እንፈልጋለን!

የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 71 በሚደነግገው መሰረት የሕዝብ ተወካዮችንና የፌዴሬሽን ም/ቤትን ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ መስከረም 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፕሬዚዳንቱ ተከፍቷል። ፕሬዝዳንቱም አገሪቱ ባለፈው ዓመት ያጋጠሟትን ችግሮችና ስኬቶች ለመዘርዘር የሞከሩ ሲሆን የኢኮኖሚ ቀውሱ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትና የመሳሰሉት «እንዳይደገሙ» መንግስታቸው እንደሚተጋ ገልፀዋል። የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ስለሚደረገው ጥረት፣ የውጭ ንግድ ተኮር ስለሆነው ግብይትና በዚህ አመት ስሚከናወነው አገር አቀፍ ምርጫ በመግቢያ ንግግራቸው ላይ ማብራርያ መስጠታቸው ይታወሳል።

የፕሬዝዳንቱን የመክፈቻ ንግግር ተከትሎ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት የማሻሻያ ሃሳብ (ሞሽን) በቀጣዩ ስብሰባ ላይ እንደሚያቀርቡም ይታወቃል። በዚህም መሰረት ባለፈው ቅዳሜ በተካሄደው 3ኛው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት 5ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ 14 ያህል የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል። በህገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪነታቸው ለፓርላማው የሆነው ጠ/ሚ/ርም በማሻሻያ ሃሳቦቹ ላይ የራሳቸውን ምላሽ ሰጥተዋል። ጉዳዩን ለመከታተል እንደሞከርነውም የቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች በመሉ ውድቅ ሆነዋል። በዴሞክራሲያዊ አሰራር ሃሳቦች በአብላጫ ድምጽ ወድቅ መደረጋቸው ስነ-አመክንዮዊ ነው ሊባል ይችላል። ሆኖም ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ነጥቦች አሉ ብለን እናምናለን።

በዕለቱ 14 የማሻሻያ ሃሳቦች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ላይ የቀረቡ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ በአብላጫ ድምጽ ውድቅ ተደርገዋል። ጥያቄው የቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች ምን ነበሩ?፣ የፓርላማ አባላት ፓርቲያቸው የሚያቀርበውን የድምጽ ድጋፍ ጥያቄ ስለሚያስተናግዱበት ስርአት ህገ መንግስቱ ያጎናፀፋቸውን መብት እየተጠቀሙበት ነው ወይ? በዕለቱ በተደረገው የድምጽ አሰጣጥ ላይ የቀረቡት ሃሳቦች እና ጉዳዮች እልባት የተሰጠበት መንገድ ለምን ከፍተኛ ቅሬታ አስነሳ? ባለፈው ዓመት አጋጠመን ከተባለው ቀውስ ለመወጣትና አሉብን የምንላቸውን ችግሮች መፈተሔ ለማበጀት ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ መቀመጫ ያላቸው ተፎካካሪ ፓርቲዎችና የግል ተመራጮች ምን ይጠበቅባቸዋል? እያንዳንዱ የውሳኔ አቋም በአገሪቱ

መፃኢ ሁኔታ ላይ ከሚኖረው አንድምታ አንፃር ሁነቶቹ እንዴት ይታያሉ እና የመሳሰሉት ሊዳሰሱ ይገባቸዋል፡፡

ውድቅ የተደረጉት የማሻሻያ ሃሳቦች ምን ነበሩ? የሚለውን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የአካል ጉዳተኞች በተለይም በአገር ሉኣላዊነት አካላቸውን ያጡ ወገኖችን የጡረታ አበል ማሻሻል ስለሚቻልበት መንገድ፣ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ካስከተለው ቀውስ አኳያ ለመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ቢደረግ፣ ባለፈው ዓመት ከተከሰተው የድርቅ አደጋ አንፃር በዚህኛው ዓመት ስላለው ቅድመ ዝግጅት ቢካተት፣ የአየር ብክለት ጉዳይ ቢካተት፣ ግሽበቱ እንዲቀንስ ወይም ባለበት እንዲቆም ማድረግ ስላልተቻለበት ምክንያት ቢጠቀስ፣ አማራጭ የክርክር መፍቻ አዋጅ በዓመቱ የህግ አወጣጥ መርሃ ግብር ውስጥ ቢገባ፣ የኢትዮ ኤርትራና የኢትዮ-ሱዳን ድንበር (ወሰን) በተመለከተ ስላለው አቋም፣ ስለ ወንጀል ህጉ፣ ስለ ስራ አጡ ዜጋ፣ ስለ ኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ተወካዮቹ በማሻሻያ ሃሳቡ ውስጥ ይካተት ሚሉና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡፡

የቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች አንገብጋቢዎች ነበሩ፡፡ አብዛኞቹ በዕለት ከዕለት ኑሮ ውስጥ በህዝባችን ጫንቃ ላይ ተጭነው አላንቀሳቅስ ያሉት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ የተወሰኑትን መመልከቱም ተገቢ ይሆናል፡፡

የመጀመርያውና የፓርላማ አባላቱ በተለያየ መንገድ ሊያስቀምጡት የሞከሩት ያለመጠን የተንሰራፋው ድህነትና ጦሱ ነው፡፡ ድህነቱን እያባባሱ ያሉት ሰው ሰራሽ ጥቃቶች ደግሞ የዋጋ ግሽበት የሚባል ወረርሽኝ ፈጥረዋል፡፡ ድህነቱን የሚያባብሰው ሌላው አደጋ የዝናብ እጥረትን ተከትሎ የሚከሰተው ድርቅ፣ ርሃብና ስደት ነው፡፡ አስከፊ ድህነት፣ ስር የሰደደ ርሃብና ዜጎቻችንን በየጎዳናው የረጨ ስደት መኖሩን እኛም ሌላውም አለም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ቀደም ባሉት አመታትና በ2001 ዓ.ም ይህ ቀውስ ቤተሰቦችን ከቀያቸው እንዲሰደዱ፣ ማህበረሰብን ለእርዳታ ጠባቂነት፣በአጠቃላይም ዜጎችን ለሰቆቃ ዳርጓል፡፡ በዚህ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ያዝናል የሚል እምነት አለ፡፡ እምነት የሚፈተነው፤ ሃዘኔታ ትርጉም የሚኖረው ግን ባለፈው ዓመት ይህ ችግር ገጥሞናል፣ ዘንድሮ እንዳይደገም ስላለው ዝግጅት በቀጣዩ ዓመት መርሃ ግብር ውስጥ ይካተት ለሚለው በሚሰጠው ምላሽና በሚያዘው አቋም ብቻ ነው፡፡

የአገር ባለውለታ የሆኑ ዜጎች ለአገራቸው ከምንም በላይ ውድ የሆነችዋን ህይወታቸውን ለመክፈል መራር ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ እዚህ ለማድረስ አካላቸውን አጥተዋል፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው እነዚህ ወገኖች የሚከፈላቸው የጡረታ አበል ጉዳይ ዝቅተኛነት በተደጋጋሚ ቢነሳም አመርቂ የሚባል ማሻሻያ ያገኙበት አይደለም ብለን እናምናለን፡፡ ከከፈሉት ውድ ዋጋና ባለውለታነት አንፃር ለመክፈል የአገሪቷ አቅም እንደማይፈቅድ እንገነዘባለን፡፡ ያሉባቸው የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች ግን/አካላቸውን በማጣታቸው በፈለጉት ዘርፍ ካለመሳተፋቸውና በእድሜ ጣራ አቅም ማጣት/በአጭር መግለጫ የአገሪቱ አቅም አይፈቅድም ብለን የምናልፈው

አይደለም:: - ሊሆን አይገባውም:: ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ህይወታቸውን የሰጡ፣ አካላቸውን የገበሩ ዜጎች አቅማቸው ሲደክም በዋጋ ግሽበት ያለቻቸው ጥሪት ስትሟጠጥ ያዝናል፣ ውለታቸውንም አይረሳም የሚል እምነት አለ::

እምነት የሚገለፀው ግን ያሉትን አማራጮች በመሉ ፈትሾ፣ ማሻሻያ አድርጎ፣ አጋርነትን በቃል ሳይሆን በግብር የሚያሳዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው ብለን እናምናለን:: «ባደረግነው ደስ ባለን ነበር፤ ሆኖም አቅሙ የለንም::» የሚለው አቋም መሰረታዊ የማይባሉ ጥያቄዎችን ለሚያቀርብ አካል ምላሽ ሊሆኑ ይችላሉ:: ደሙን ከእናት አገሩ አፈር ጋር በመቀላቀሉ ወገኖቹን በኩራት ቀና ብለው እንዲሄዱ ላስቻለና በጣም በዝቅተኛ ጡረታ ቀጣዩ ጊዜው ለጨለመበት ዜጋችን ግን አይሰራም:: መፍትሄ እንጂ ማስተዛዘኛ አይጠቅምም እንላለን::

ግሽበቱ እንዲቀንስ ምን ተደረገ? በያንስ ባለበት እንዲቆም በተወሰደው እርምጃ ዙርያ የቀረበው የማሻሻያ ሞሽንም ተገቢና ቢቻል ግልጽ ማብራሪያዎች ቀርበውበት ችግሩ የሚወገድበት እውነተኛ መላ መነደፍ ነበረበት:: በመሰረቱ ግሽበቱን አስመልክቶ ዓለም አቀፍ ተጽኖዎች ቢኖሩም፣ በአገር ውስጥ ያለውን «የስግብግብ ነጋዴዎች» እንቅስቃሴ ለመግታት በሚል የተወሰዱ እጅግ የዘገዩ፣ እጅግ መጠነኛ እርምጃዎች ቢኖሩም፣ ነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ፓሊሲን የሚያራምዱ አፍሪካውያን ጐረቤቶቻችንና ሌሎች የሚያደርጉትን በጥቆማ መልክ ማንሳቱ ቅንነቱ ካለ ተሞክሮውን በአገራችንም ለመድገም ይረዳል ብለን እናምናለን:: መሰል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይከተላሉ ያልናቸው እነዚህ አገራት «ስግብግብ ነጋዴዎቻቸውን» በሚሸጧቸው ሸቀጦችና በማስጧቸው አገለግሎቶች ላይ ዋጋ እንዲለጥፉና እንዲያሳውቁ በማድረግ ብቻ አይገቱም:: በዘፈቀደ የዋጋ ጭማሪ ሲያደርጉ ተከታትለው እርምጃ ይወስዳሉ:: በአገሪቱ ውስጥ ነፃና ጠንካራ የሸማቾች ማሕበራት እንዲኖሩ ስለሚበረታታ ያለአግባብ የምትጨመር አንዲት ቤሳ ህዝባዊ ቁጣ ልትቀሰቅስ ትችላለች:: መንግስትም የህዝብን ቅሬታ ሰምቶ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል:: በእነዚህ አገራት ነፃ ገበያ ማለት ልቅ የንግድ ስርአት ማለት አይደለም:: በእነዚህ አገራት ነፃ ገበያ ማለት ህገ ወጥ ነጋዴዎች ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ሸቀጦች በጎዳናዎች ላይ ሲቸበችቡ ለይስሙላ በደንብ አስከባሪዎች ማስባረር ማለት አይደለም:: ነፃና ህይወት ያላቸው የንግድ ም/ቤቶች ከህጋዊ ነጋዴዎች ጋር ተባብረው የተረጋጋ ገበያ የሚፈጥሩበት መንግስትም ህግ የማስከበር ግዴታውን የሚወጣበት ስርአት ነው:: መሆን የሚችልና መሆን የሚገባው ስለሆነ ፈጣን ምላሽ እንፈልጋለን::

ፕሬዝዳንቱ ያቀረቧቸው ሃሳቦች ያልዳሰሷቸው ጉዳዮች አሉ ተብሎ ሲታመን/ቢኖር እድል ለመስጠት/ የህዝብ ተወካዮችም ማሻሻያ የማቅረብና ከአገሪቱ ጠ/ሚር ተገቢ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው:: እንደእውነቱ ከሆነ አገራችን ካሉባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንፃር ፕሬዝዳንቱ የሚያነሷቸው /የሚያቀርቧቸው/ ሃሳቦች በቂ ናቸው ብሎ መደምደም ለእውነታና ለአእምሮ የራቀ ጉዳይ ይሆናል:: በሌላ በኩል

በተወካዮቹ የቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች በሙሉ በፕሬዝዳንቱ ሞሽን ላይ ተካተው ይሰራባቸው ማለታችን አይደለም።

በማንኛውም አገር ፓርላማ እንደሚያጋጥመው ሁሉ አንዳንዶቹ ሃሳቦች ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘቡ፣ በቀናነት የቀረቡ ቢሆንም ቢተገበሩ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ፓርላማው ድምፁን ተጠቅሞ ሥራ ላይ እንዳይውሉ ያደርጋቸዋል። ይህ ማለት ግን ሃሳቦችን ውድቅ የምናደርገው ከእኛ አስተሳሰብና የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ውጪ ያለ ወገን ስላቀረባቸው መሆን የለበትም። በዚህ በኩል እየተመለከትነው ስላለው መታረም ያለበት አንድ አደገኛ አካሄድ የምንለው ይኖረናል።

አሁን ባለው ፓርላማ ውስጥ ኢህአዴግ አብላጫ ድምጽ ስላለው የሚያቀርባቸው ሃሳቦች በሙሉ ሲፀድቁ በሌሎች የሚቀርቡ ደግሞ በአብዛኛው ውድቅ ሲደረጉ እስኪበቃን ስንመለከት ኖረናል፡ አሁንም የዴሞክራሲያዊ አሰራር ህግ የሚፈቅደው የአብላጫ ድምጽ ተቀባይነት በመርህ ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ሃሳቦች ከሌላው ወገን ስለቀረቡ ብቻ መቃወም፣ ሃሳቦች ከተወዳደሩበት ፓርቲ ስለቀረቡ ብቻ ለድጋፍ እጅ ማውጣት አንድ እንጠብቀዋለን የምንልለትን የህገ መንግስት ድንጋጌና እሳቤ መጣስ ይሆናል።

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 54 ስር የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት የመላው ሕዝብ ተወካይነታቸውን ካተተ በኋላ ተገዢነታቸው ለህገ መንግስቱ፣ ለሕዝቡ እና ለሕሊናው ብቻ ይሆናል ይላል። ይህ ወርቃማ ህግ አንድ የፓርላማ አባል ከፓርቲውም ይሁን ከተቃራኒ (ተፎካካሪ) ፖርቲዎች ሃሳብ ሲቀርብ ሃሳቡ መሰረታዊ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ይጥሳል? ብሎ ይመረምራል። የቀረበው ሃሳብ ከየትኛውም ወገን ይሁን የወከልኩትን ሕዝብ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅሞች ያስጠብቃል? ብሎ ይገመግማል። ሃሳቡ ቀናነት ቢኖረውም ቢተገበር አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል?፣ ሃሳቡ የቀረበው በአመለካከት ልዩነት ካለን ወገኖች ቢሆንም ደግሞም ጉዳት ያለው ቢመስልም ውጤቱ አዎንታዊ ይሆናል ሲል ያስባል፣ ያብሰለስላል። የህሊና ዳኝነት በመስጠትም ለትክክለኛው እርምጃ እጁን በድጋፍ ወይም በተቃውሞ ያወጣል። ህገ መንግስቱ ይከበራል፣ ሕዝብ ተጠቃሚ ይሆናል እንዲሁም ህሊና ሰላም ያገኛል።

ስለዚህ አንድ ብሎ በጀመረው የፓርላማ የሥራ ዘመን ወኪሎቹ የሚያወጧቸው ህጎች ተፈፃሚ የሚሆኑት / በአውጪዎቹም ጭምር ላይ በመሆኑ/ከላይ ባነሳናቸው ሶስት መሰረታዊ ሚዛኖች ብቻ እየተመዘኑ እንዲያፀድቋቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን። ሕገ-መንግስት ህዝብና ህሊናን ገዢያችን ካደረግን ሃሳቦች በማንም ይቅረቡ ውጤታቸው አዎንታዊ የማይሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ይህ ሃሳብ እውን እንዲሆን እንመኛለን፣ ድጋፋችንም ይቀጥላል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

# Verbatim

«ፓርቲው በእግሩ መቆም እስኪጀምር ድረስ እንጂ በፓርቲው ውስጥ በዘላቂነት አልቀጥልም::አቋሜ ይኸው ነው::»

**ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም**

**«በፓርቲዎ ውስጥ አንዴ ይገባሉ አንዴ ይወጣሉ፤የእርስዎ አቋምና በፓርቲው ውስጥ ያለዎት ሚና ምንድነው?» ሲል መሰናዘሪያ ጋዜጣ ላቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ**

«ቦርዱ ይህን ጉዳይ ቀደም ብሎ አይቶታል:: አንዳንድ ፓርቲዎች ዕውቅናውን ነው ያገኙት እንጂ ተጨባጭ የሆነ ተሳትፎ የሌላቸው ናቸው:: አንዳንዶቹ በተለያየ ምክንያት ከአመራር የተነሱ፤ ፓርቲውን እንደፓርቲ የማያንቀሳቅሱ የአንድ ሰው መሪነት ብቻ ያለባቸውም አሉ:: »

**ዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሔር**
**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ ከመጪው ምርጫ ጋር በተየያዘ ለሪፖርተር ጋዜጣ የተናገሩት**

«ፕሬዚዳንቱ ስኬት ብለው የዘረዘሩዋቸው ነገሮች ተጋንነዋል:: የሰውን ህይወት የማይለውጥ ከወረቀት ላይ የማያልፍ የስታትስቲክስ ጨዋታ እንጂ፤ የህዝባችን ድህነት እየተባባሰ ነው::»

**ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ**
**ፓርላማው የመጨረሻ ዓመት ስራውን ሲጀመር ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ የተናገሩት ንግግር አስመልክቶ ለሰንደቅ ጋዜጣ  የሰጡት አስተያየት**

# ዜናዎች

# ቴዲ አፍሮ በደማቅ ኮንሰርቱ ፍቅርን ሲሰብክ አመሸ

## «ማንንም እንዳትጠሉ፣ ፍቅር ያሸንፋል»

*በአቤል ዓለማየሁ*

- **ለአበበች ጐበና 100 ሺህ ብር ረዳ**
- **«ጃ ያስተሰርያል» ተጠይቆ አልተዘፈነም**
- **ኤርትራዊያን ሙዚቀኞች በባንዱ ውስጥ ተሳትፈዋል**
- **በጥላሁን «ዊልቼር» ላይ እቅፍ አበባ አኑሯል**
- **ኮንሰርቱ በመንግስት ሚዲያዎች«የዜና ሽፋን» አላገኘም**

ተወዳጁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ከማረሚያ ቤት ከወጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከትላንት በስቲያ እሁድ በአዲስ አበባ ስታዲየም ታላቅና ደማቅ ኮንሰርት ለአድናቂዎቹ አቀረበ፡፡

ገቢው ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፐመንት አሶሴሽን ለተባለ መንግስታዊ ላልሆነ ድርጅት ገቢ የሚሆን ሲሆን ድርጅቱ ይህንን ገንዘብ በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን ለመርዳት፣ ለማቋቋምና ወደመጡበት ለመመለስ ይውላል፡፡

የሙዚቃ ዝግጅቱ ከ12 ሰዓት ጀምሮ እንደሚጀምር አስቀድሞ የተገለፀ ቢሆንም ቴዲ አዲስ አበባ ስታዲየም የደረሰው 12:50 ላይ ነበር፡፡ ምንጮች ለአውራምባ እንደገለጹት ከሆነ ድምፃዊው በስታዲየም አቅራቢያ ከሚገኝ አንድ ህንፃ ላይ በመሆን የአድናቂዎቹን ሁኔታ ይከታተል ነበር፡፡

በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው ቴዲ ከዘመናዊ «ሀመር» መኪና ወርዶ ከመድረክ ጀርባ ወደተዘጋጀ ድንኳን ሲገባ የጥላሁን ገሠሠ ባለቤት ወ/ሮ ሮማን በዙ ስመው ተቀብለውታል፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ የቴዲን መድረስ የተረዱ ስታዲየሙን ያጥለቀለቁት አድናቂዎቹ ንዝረት የመፍጠር አቅም ያለው ከፍተኛ ደምጽ በማውጣት ስታዲየሙን

በድምጽ አናወጡት:: በዚህ ሰዓት በመድረክ የአቡጊዳ የባንድ አባላት የቴዲን ዘፈኖች ዜማ «ፕሮቫ» ማሰማት ጀመሩ::

ደረታቸውን በስፖርት ያፈረጠሙ ለጥበቃ ስራው ኃላፊነት የተጣለባቸው በርካታ ወጣቶች እጆቻቸውን እንደ ሰንሰለት ቀጣጥለው አንገታቸው ላይ የማለፊያ ባጅ አንጠልጥለው በመድረክ ዙርያ ወደነበሩት የሚዲያና የተለያዩ የዝግጅቱ አስተናባሪዎች መጠጋታቸው የቴዲ ሙዚቃ መጀመሪያ ሰዓት መድረሱን ምልክት ሰጠ:: «አሲዮ ቤሌማ» የሚለውን ዜማ የአቡጊዳ ባንድ አባላት ማንቆርቆር ጀመሩ::

«ዝግጁ ናችሁ?»፣ ከ35 ሺህ በላይ ለሚሆነው ታዳሚው ጥያቄ ሲያቀርብ በፉጨት፣ በጭብጨባና በደስታ ጩኸት «አዎ!» የሚል ግዙፍ መልስ አገኘ:: በድንኳኑ ውስጥ የጀመረውን «አሲዮ ቤሌማ» ዘፈን ስንኝ እየደረደረ ከመድረክ ደረሰ:: በደስታ የሚያነቡ፣ ደስታቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው የሚያደርጉትን ያጡ፣ የዘፋኙ ምስል ያለበት «ቲሸርት» የሚያውለበልቡ፣ ከዓመት በላይ የተጠሙት ሰው በተሰየመበት መድረክ ከፊት ለፊት በመቆማቸው ደስታ ያነቃቸው ሁሉ ... ጀመሩ፣ «ኡኡኡ ... ቴዲ ቴዲ ቴዲ ...»፣ አሁንም «....ቴዲ!»::

በስፖርታዊ ውድድሮች ተመልካች የተጠማው ስታዲየም ጠጠር መጣያ እስከሚጠፋ ድረስ በተዘጋጁ ስፍራዎች ሁሉ ከአፍ እስከ ገደፉ ተጥለቅልቋል::

በስታዲየሙ አቅራቢያ የሚገኙ ህንፃዎች ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በሙሉ ዓይናቸውን ወደሜዳው አድርገዋል::

የስታዲየሙን ፓውዛ የተሸከሙ ብረቶች ከፍለው ለመግባትና ትኬት ለማግኘት ያልታደሉ ወጣቶች ተንጠላጥለውባቸዋል::

ውስጥ ካለው በደጅ ሆኖ የሙዚቃውን ትሩፋት የሚዘግነው ይበልጣል:: «አቡጊዳ»፣ «ዓይኔ» የተሰኙት ዘፈኖቹን እያከታተለ ሲጫወት ቴዲ አፍሮ ያዘፍናል፣ ወደባንድ አባላቱ በቅርበት እየተጠጋም ሆነ በርቀት መልዕክት ያቀብላል:: ከድምፅ ጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያው ጋር ያወራል:: የድምፅ ጥራት ጥሩ ካልሆነ እጅ ይወራጫል፣ ፊቱ ቅጭም ይላል:: የመሣሪያዎች የድምፅ ውህደት ሲጣመርና ጥሩ ድምፅ ጆሮው ሲደርስም «Sound Man Perfect!» ሲል የመድረክ ባልደረባውን ያወድሳል::

በርካታ ዜማዎችን እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት 30 ድረስ ያቀነቀነው ቴዲ ዘፈኑን የዘጋው «ሀገሬን አልረሳም» በሚል ዜማ ነው::

## የጥላሁን «ዊልቼር»

የታላቁ ኢትዮጵያዊ የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሠሠ አልጋወራሽ ቴዎድሮስ ካሳሁን ነው የሚሉ አሉ:: ጥላሁን «የማይተካ» ስለመሆኑ የሚያምኑት ደግሞ በፍፁም በዚህ ሀሳብ አይስማሙም፤ «እንደ ቴዲ ዓይነት አዳዲስ የሙዚቃ ጀግኖች ይፈጠራሉ እንጂ ጥላሁን አይተካም» ባይ ናቸው::

ቴዲ በኮንሰርቱ ላይ በጥላሁን የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ የሙያ ጓደኞቹ ያቀነቀኑትን «ሳይገባኝ ያከበርከኝ» ዜማ በመድረክ የተጫወተ ሲሆን በዚህ ሰዓት ጥላሁን

ይጠቀምበት የነበረው «ዊልቼር» ላይ ማናጀሩ አዲስ ገሥሠ ያቀበሉትን አበባ አስቀምጧል። ዘፈኑንም እያላቀሰ ተጫውቷል። «ጥላሁን ምልክታችሁ ነው፣ አይደለም?» ሲል ታዳሚውን ጠይቆ እሱም ህዝቡም «አዎ!» ብለዋል። «ሲለዩ ተዋዶ» የሚለውን የጥላሁንን ዘፈንም አቀንቅኗል።

## መልዕክተ-ቴዲ

መድረክ የመቆጣጠር ከፍተኛ ብቃት ያለው ቴዲ አፍሮ እያቀነቀነ በሞራል ከመድረክ ባለሙያዎች፣ ከሙዚቃ ተጫዋቾች፣ እና ከታዳሚው ይጨዋወታል። መልዕክቶችንም ያስተላልፋል። «ሁልጊዜ ጥሩ ሁኑ፤ ማንንም አትጥሉ»፣ ሲል በተደጋጋሚ መልዕክት አስተላልፏል - ቴዲ። «ፍቅር ያሸንፋል፤ እንደ ልባችን ቅንነት ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል፤ ኢትዮጵያን እግዚአብሔር አሁን ይባርካታል፤ ጥላቻ በልባችን እንዳያድር፤ ማንንም አትጥሉ።»

## ለአበበች ጐበና 100 ሺህ ብር፤ ለይልማ ገ/አብ የወርቅ ብዕር

ቴዲ በልመና ለሚተዳደሩ ወገኖች በነፃ ከሰራው ኮንሰርት በተጨማሪ ለአበበች ጐበና ፕሮጀክት የ100 ሺህ ብር ዕርዳታ አድርጓል። «ይሄ ልጅ [ቴዲ] የሁላችንም ልጅ ነው። እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ይሁን፤ የእሱን እድል ለሁላችንም፣ ለዘራችን ይስጥ።» ብለዋል ወ/ሮ አበበች ጐበና የገንዘብ ቼኩን ሲቀበሉ። ቴዲም «በዚህ ምድር ያደረግነው በዚህ ምድር ይቀራል። ከምድር በላይ ያደረግነው ሁሉም ይኖራል። አበበች ጐበና ትልቅ ሴት ናቸው። ዛሬ ተጨማሪ መቶ ልጆችን ለማሳደግ ቃል ገብተዋል።» ሲል መልካም ተግባራቸውን መስክሯል።

በኮንሰርቱ ላይ ሌላው ሽልማት የተበረከተለት በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ በዘፈን ግጥም ደራሲነት የላቀ ድርሻን የያዘው ይልማ ገ/አብ ነው። ግጥም መፃፍ እንዲጀምር ይልማ አርዓያ እንደሆነውም ገልጿል - ቴዲ።

«ክብር የሚገባው ትልቅ ባለሙያ ነው» ላለው ገጣሚ በወርቅ የተሰራ ብዕር በስጦታ መልክ አቅርቦለታል። «ለይልማ ገ/አብ ስጦታ በማበርከቴ እድለኛ እሱ ሳይሆን እኔ ነኝ» ብሏል። ታዳሚውም «ይገባዋል!» ሲል ይልማን አሞግሷል። ይልማ ገ/አብ በበኩሉ «ከዚህ በኋላ መቶና ከዚያ በላይ ብዕሮችን እንዳነሳ ሞራል ሰጥቶኛል። ረጅም እድሜ ከጤና ጋር እመኝለታለሁ።» በማለት ስጦታው ላስከተለለት የሞራል እገዛ ምስጋና አቅርቧል።

## ሙዚቃ + ፍቅር = ሰው መሆን

የቴዲ በሆነው «አቡጊዳ» ባንድ ውስጥ ሁለት ያሬድ አብርሃም እና ሩፋኤል ወ/ማሪያም የተባሉ ኤርትራዊያን ዜግነት ያላቸው ወጣቶች ነበሩ፣ በዝግጅቱ ላይም ተሳትፈዋል። ያሬድ ኦርጋን፣ ሩፋኤል ደግሞ ድራም ይጫወታሉ። «ያሬድ ኤርትራዊ ነው ግን ኢትዮጵያዊ ነው» በማለት የተናገረው ቴዲ «ሰው መሆን አንድ አድርጐናል።»

ብሏል። «እኛ ባንጣመር ሙዚቃው አያምርም ነበር።» ሲል «ካብ ዳህላክ»ን በመድረኩ ባይጫወትም በንግግር መልክ አቀንቅኖታል።

ስፓርክል፣ ኢዲ እና ፒያ የተባሉ የአፍሪካና የአሜሪካ ዜጎች ይገኛሉ። ቴዲ ግን እኛ ስንጠራቸው አልማዝ፣ ፀሐይ እና አስቴር (በቅደም ተከተል) ብለን ነው ብሏል።

## ዘፈኖቹ እና አድናቂዎቹ

እሱ ቃሊቲ እያለ አምልጣ የወጣችው «ጉድ ያረገኝ ዓይኔ ነው» የሚለውን ዜማ ሲያቀነቅን «የክፉ ቀን ዘፈኔ ነው» ሲል 1 ዓመት ከ4 ወር የማረሚያ ቤት ቆይታውን አስታውሷል። ቴዲ በምሽቱ የጥላሁን ገሠሠን እና ለጥላሁን የተዜመውን ዜማ ጨምሮ ከ25 በላይ ዘፈኖችን ተጫውቷል። እንዲሁም «ኡኡታዬ» የሚለውን ዜማውን ሲያቀነቅን የሙዚቃ መሣሪያ እየተጫወተ ነበር - «ኦርጋን»።

ይሁንና ግን በስታዲየሙ እስከጥግ ድረስ የሞላው የቴዲ አድናቂ እና የሙዚቃ አፍቃሪ በታላቅ ድምፅ ያቀረበው ጥያቄ ነበር። ከሳምንት በፊት በዚህ ኮንሰርት ላይ እንደማይዘፈኑ ከተገለጹት፣ ፖለቲካዊ ይዘት እንዳላቸው ከሚነገርላቸው የቴዲ ዜማዎች መካከል (በአውራምባ ታይምስ የባለፈው ሳምንት ዕትም ይህን የተመለከተ ዘገባ መቅረቡ ይታወሳል) «ጃ ያስተሰርያል» የተሰኘው አንዱ ነው። እናም ሙዚቀኛው ያቀነቅንላቸው ዘንድ «ጃ ያስተሰርያል ... ጃ ያስተሰርያል» እያሉ በማዜም የማስታወስ ዓይነት መልዕክት ያዘለ ጥያቄ ለመድረኩ አቅርበዋል። ሆኖም ምላሽ አልነበረም፤ ዝግጅቱ እስከተጠናቀቀበት እስከምሽቱ 5:30 ድረስ «ጃ ያስተሰርያል» አልተዘፈነም ነበር።

ኮንሰርቱን ለመከታተል ከናዝሬት፣ አዋሳ፣ ደ/ዘይት፣ ባህር ዳር የመጡ ወጣቶች ነበሩ። «ይህን ፍቅር ማን ይደርስበታል?» ሲል መስፍን የተባለ ከናዝሬት የመጣ ወጣት ጠይቋል።

የኤልሻዳይ ተራድኦ ድረጅት ሥ/አስኪያጅ አቶ የማነ ወ/ማሪያም፣ «ኮንሰርቱ በጣም ደስ ይላል፤ የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ይውላል» ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ የገለፁ ሲሆን ከዚህ በፊት አሰባስበው ከላኳቸው 28 ሺህ ምንዱባን ጠያቂዎች መካከል ተመልሰው ወደ ከተማ የመጡት ጥቂቶች ብቻ ናቸው ብለዋል። በሙያው ታላቅ እገዛ ያደረገው ቴዲ «የአፍሪካ ምልክት የሆነ ታላቅ አርቲስት ነው» ሲሉም ስራ አስኪያጁ ለአውራምባ ታይምስ ጨምረው ገልፀዋል።

ከቴዲ አፍሮ ኮንሰርት ጋር በተያያዘ በብዙዎች ዘንድ በአስገራሚነቱ ተጠቃሽ የሆነ ክስተትም አጋጥሟል። «ድህነትን ተረት ስለማድረግ» እና ህዳሴን በማብሰር ኃላፊነት ላይ መጠመዳቸውን አዘውትረው የሚገልጹት የመንግስት ሚዲያዎች፤ ታላቅ ሀገራዊ ተልእኮ አንግቦ ወገኖችን ለመታደግ የተዘጋጀውን ኮንሰረት የሚመለከት አንድም ዘገባ አለማቅረባቸው ብዙዎችን አሳዝኗል። ከመንግስት ሚዲያዎች ውጪ ኮንሰርቱን በቀጥታ ስርጭት ሽፋን እንደሚሰጠው ቃል ገብቶ የነበረው ሸገር ኤፍኤም (የግል) ሬዲዮ ጣቢያም በቴክኒክ ችግር ምክንያት ሊሳካለት እንዳልቻለ ገልጿል።

# "አንድነት" የዋና ፀሐፊውን አቋም እንደማይጋራ አስታወቀ

በያዝነው ዓመት ማገባደጃ ላይ በሚካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ለመሳተፍ በእስር ላይ የሚገኙትን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን «እንደቅድመ ሁኔታ አናቀርብም» በሚል የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ዋና ፀሐፊ የሆኑት አቶ አስራት ጣሴ ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እየሰጡ ያለውን መግለጫ እንደማይጋራው ፓርቲው ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቀ።

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ም/ፕሬዚዳንትና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት «የፓርቲው ዋና ፀሐፊ ያለህግ ስርአት የታሰሩትን መሪያችንን አስመልክቶ በግላቸው እየሰጡት ያለው መግለጫ የአንድነትንም ሆነ የአንድነት ፓርቲ አባል የሆነበትን የመድረክን /የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በሚል መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም መስራች ጉባኤውን ያካሄደው/ አቋም ፈጽሞ እንደማያንፀባርቅ ሊታወቅ ይገባል» ብለዋል።

በፓርቲው ውስጥ ያሉ አባላት ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለጽ መብት አላቸው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው «ይሁንና ይህን መብት በመጠቀም የሚሰጡ የአባላት መግለጫዎች የፓርቲው አቋም እንዳልሆኑ ሊታወቅልን ይገባል» ሲሉ አስምረውበታል። ፓርቲው በከፍተኛ ኃላፊነት/በስራ አስፈጻሚ አባልነት እና በዋና ጸሐፊነት/ ላይ የሾማቸውን አመራሮች የሚሰጡት መግለጫ እንዴት ፓርቲውን አይወክልም ይባላል? ሲል አውራምባ ታይምስ ላቀረበላቸው ጥያቄ ዶ/ር ኃይሉ ሲመልሱ «እንነጋገርበታለን። መሰል ክስተቶች ሲያጋጥሙ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወያይተን የጋራ መግለጫ እናወጣለን። አሁን የሚሆነውም እንደዚያው ነው።» ካሉ በኋላ ዋና ጸሐፊውም ለሊቀ መንበሯ ከእስር መፈታት በእጅጉ እየደከሙ ይገኛሉ ብለዋል።

«መሪያችን የህግ ስርአትን ባልጠበቀ መንገድ በእስር ላይ ትገኛለች። እንዲሁም በርካታ ዜጎቻችን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። ለእነዚህ ሁሉ በቁርጠኝነት መታገላችንን እንቀጥላለን። ይህም ማንኛውንም ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል አማራጭ ባካተተ መንገድ የሚካሄድ ነው።» በማለት በምርጫው ለመሳተፍ የወ/ሪት ብርቱካን ከእስር መፈታት የቅድመ ሁኔታ ጉዳይ አንድ አማራጭ እንደሆነ ጠቁመዋል።

# «በዝዋይና ዱግዳ ወረዳ እስካሁን በረሃብ አምስት ሰዎች ሞተዋል»

**አቶ ወንድሙ ኢብሳ**
**የፓርላማ አባል**

በአርሲ ዞን ዝዋይና ዱግዳ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ አራት የቀበሌ ገበሬ ማህበራት ውስጥ እስካሁን አምስት ሰዎች በረሃብ ሲሞቱ በርካቶች በከፍተኛ የረሃብ አደጋ ውስጥ ይገኛሉ ሲሉ የተከበሩ አቶ ወንድሙ ኢብሳ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ።

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልና የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ የስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ወንድሙ ፓርላማው ለእረፍት በተዘጋበት ወቅት ወደመረጣቸው የአርሲ ዞን ዝዋይና ዱግዳ ወረዳ ሕዝብ በመሄድ የተከሰተውን የረሃብ አደጋ መጠን መመልከታቸውን ገልፀዋል። «ሰንበሮ፣ሔረራ፣ ናትሌና ጉልቤ በተሰኙ የቀበሌ ገበሬ ማህበራት እስካሁን አምስት ሰዎች የሚላስ የሚቀመስ በማጣት የሞቱ ሲሆን ህፃናት ትምህርታቸውን መከታተል በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።» ብለዋል።

አቶ ወንድሙ ችግሩን አሳሳቢ ያደረገው ሌላው አደጋ በማለት የገለፁት የወረዳው ካቢኔዎች በተከሰተው ርሃብ ዙሪያ መነጋገር ያለመፈለጋቸው በመሆኑ አፋጣኝ የመፍትሔ እርምጃ ካልተወሰደ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት ይፈጠራል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

## ኮሜንተሪ

# ስኬቶች ወደ ፕሬዝዳንት ኦባማ ወይስ ፕሬዝዳንት ኦባማ ወደ ስኬቶች?

**በነብዩ መስፍን**

በዓለም ፖለቲካ ተሳትፎዓቸው ገንነው ከሚታወቁ የፖለቲካ መሪዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት መጠቀስ ከጀመሩ ሰነባብተዋል- የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ። ለዝናቸው መግነንና ያሉበት ደረጃ ለመድረስ ያስቻሏቸው፣ የበርካታ ዓመታት የእርሳቸውና የመሰል አሜሪካውያን የትጋት ስራዎች እንደሆኑ እምብዛም አይጠያይቅም። ግና መሰረታዊ የሚባሉ ስኬቶችን ተቀናቃኞቻቸውን ጉድ በማሰኘት በአጭር ጊዜ ማስመዝገባቸው እኛን፣ ራሳቸው ተቀናቃኞቻቸውን እና በአጠቃላይ መላውን የዓለም ሕዝብ «አጀብ ነው!» አሰኝተዋል።

እ.አ.አ. ከ1901 ጀምሮ በ*አልፍሬድ ኖቤል* መስራችነት የተቋቋመው *የኖርዌይ ኖቤል ኮሚቴ*፣ በየዓመቱ ታላቅ ስኬትን በተለያዩ ዘርፎች ላስመዘገበ ግለሰብ ወይም ቡድን *የኖቤል ሽልማት* ይሰጣል። በመሆኑም በዚህ ዓመት በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሜዲስን፣ በሥነ-ጽሑፍ ወዘተ ላቅ ያለ ስራ በመስራት ዓለምን ወደፊት እንድትራመድ አስችለዋታል የተባሉ ሰዎች በኮሚቴው ተመርጠው ይፋ ተደርገዋል። በዚህ ላቅ ያለ

ስራ ሰርተዋል ተብለው ሽልማታቸውን ካወቁ ግለሰቦች መካከል የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ አንዱ ናቸው።

የዓለምን ሕዝብ፣ መንግስታትን፣ ደጋፊዎቻቸውን እንዲሁም በውጭም ሁነ በአሜሪካ የሚገኙ ባለጋራዎቻቸውን ጭምር እጅግ ያስደመመውን ይህን *የ2009 የኖቤል የሰላም ሽልማት* ለፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ ይገባቸዋል ብሎ *የኖርዌይ ኖቤል ኮሚቴ* የሸለማቸው አርብ ጥቅምት 9/2009 ነበር። ይህም ሽልማት፣ ኦባማ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ በሁለት ታላላቅ መድረኮች፣ ሁለት አስደናቂ ስኬቶችን ለራሳቸው፣ ለአሜሪካ ሕዝብ፣ ለደጋፊዎቻቸው፣ ለአሜሪካና ለመላው ዓለም እንዳስመዘገቡ አሳይተዋል። የመጀመሪያው ታላቅ መድረክ፣ የታላቋ አሜሪካ ሕዝብ፣ በጃንዋሪ 20/2009 «ልንመራ የሚገባው በእርሶ እንጂ በሌላ አይደለም!» በማለት ፕሬዝዳንት አድርጎ ሲመርጣቸው ያገኙት ስኬት ነው። ሁለተኛው፣ *የኖርዌይ ኖቤል ኮሚቴ* የ2009 የኖቤል ሽልማት አሸናፊነታቸውን አርብ ጥቅምት 9/2009 ባሳወቀበት ዕለት ያገኙት ነው።

ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ ሥርዓት ካላቀቁ መሪዎች መካከል ሽልማቱን ከተሸለሙት ከኔልሰን ማንዴላና ከኤፍ. ደብልዩ. ዴ ክለርክ፣ ከአሜሪካ የ1960ዎቹ የጥቁሮችና ነጮች ወዘተ የቆዳ ቀለም ላላቸው የአሜሪካ ዜጎች፣ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች እንዲከበር ካቀነቀኑና ከታገሉት ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ከበርማዋ የሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መሪና አቀንቃኝ ኦን ሳንሰኪ እና ከሌሎች በርካት *የኖቤል የሰላም ሽልማት* ተሸላሚዎች መዝገብ ውስጥ ስማቸውን ያሰፈሩትና የሰፈረላቸው ፕሬዚዳንት ኦባማ፣ ይህን ታላቅ ሽልማት አስመልክቶ የሰጡት አስተያየት ከሽልማቱ ይልቅ የሚያስገርም ነው።

በአጭርም ሆነ በወደፊት ዓመታት ሽልማቱን አገኛለሁ የሚል ግምት የነበራቸው አይመስልም - የሰጡት አስተያየት እንደሚጠቁመው። ይህ ታላቅ ክብር ለእርሳቸው እንደማይገባ፣ *በታላቅ ትህትና* ነበር «ዱብ ዕዳ» ስለሆነባቸው ሽልማት የተናገሩት። «እኔንና በመላው ዓለም ያሉ ሰዎችን በጀብደኛ የሰላም አቀንቃኝነታቸው አማካኝነት ካነቃቁን ወንዶችና ሴቶች ጋር መካተት ይገባኛል የሚል ስሜት አይሰማኝም።» ነበር ያሉት በኢ-ሜይል ለወዳጆቻቸው ባስተላለፉት መልዕክት። በመላ *የኖቤል የሰላም ሽልማት* ታሪክ፣ የኖቤል የሰላም ሽልማት እንዲሁ ስኬቶችን ለማወደስ ብቻ በጥቅም ላይ የሚወል አለመሆኑንና ይልቁንስ ለበርካታ ግቦች ስኬት ከግብ መድረስ እንደማበረታቻም የሚሰጥ እንደሆነ፣ ሽልማቱን የሚቀበሉት እርምጃ እንዲወስዱ እንደተደረገላቸው ጥሪ አድርገው እንደሆነና በተጨማሪም የ21ኛውን ክ/ዘመን ችግሮች ለመቅረፍ ለሁሉም የዓለማችን አገራትና ሕዝቦች የተደረገ ጥሪ እንደሆነም ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ ለሽልማቱ መታጨታቸውን እንኳን አያውቁም ነበር። ያወቁት በኀይት ኀውስ መኖሪያቸው ከባለቤታቸው ጋር ሳሉ ከንጋቱ 12:00 *የኖቤል ሰላም ሽልማት* ማሸነፋቸው ከእንቅልፍ ተቀስቅሰው በስልክ በተነገራቸው ወቅት ነበር። «ከመኝታዬ ይህን ለመስማት እቀሰቀሳለሁ ብዬ አልጠበኩም ነበር፤» በማለት

ስሜታቸውን የገለፁ ሲሆን ይህም የመደመም ስሜት የእርሳቸው ብቻ አልነበረም - ሌሎች ባልደረቦቻቸውም ተመሳሳይ አስተያየት ነበር የሰጡት፡፡

በኖቤል የሰላም ሽልማት አማካኝነት ከተላላቅ የዓለማችን መሪዎች ጋር ያሰለፋቸው ምክንያቶች በሸላሚው ቡድን ተጠቅሰዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲን እና በሕዝቦች መካከል ትብብርን ለማጠናከር ፕሬዝዳንቱ ባበረታቷቸው ጥረቶችና ከኒኩለር ጦር መሳሪያ የጸዳች ዓለም ለመፍጠር በሰነቁት ርዕይና እንቅስቃሴዎች አንደኛው ነው፡፡ ለዚህም ርዕያቸው ኮሚቴው ትልቅ ትኩረት እንደሰጠው በመግለጫው አስፍሯል፡፡ ባራክ ኦባማ እንደፕሬዝዳንት በዓለም ፖለቲካ አዲስ ድባብ በመፍጠራቸው ምክንያት ዘርፈ-ብዙ ዲፕሎማሲያዊ የመፍትሄ አምጭ መንገዶች የቀድሞ ማዕከላዊ ስፍራቸውን መልሰው እንዲይዙ ማስቻላቸው፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ሌሎች በርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሊጫወቱት የሚችሏቸው አስተዋጽኦዎች አጽንኦት እንደተሰጣቸው ኮሚቴው አውስቷል፡፡

በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ዓለም አቀፍ አለመግባባቶችን እንኳን ቢሆን መፈታት ያለባቸው በመነጋገርና በመደራደር ነው የሚለውን የአለመግባባትን የመፍቻ መርህን ተጨባጭ የሚያደርግ መሆኑን፣ ከኒኩለር ጦር መሰሪያዎች የፀዳች ዓለም ለመፍጠር ኦባማ ያላቸው ርዕይ የጦር መሳሪያዎች ቁጥጥርና የማስወገድ እንቅስቃሴን ማጠናከሩ፣ ዓለም እያጋጠማት ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ፈተናዎች ለመቅረፍ አሜሪካ ገንቢ አስተዋጸኦ እንድታበረክት ማስቻላቸው እና ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች በመላው ዓለም እንዲጠናከሩ እያደረጉ ያሉት እንቅስቃሴዎች በመራጭ ኮሚቴው የተጠቀሱ ፕሬዝዳንቱን ሊያሸልሟቸው ያስቻሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ኮሚቴው እንዳለው፣ ኦባማ እንደሚገኙበት የስልጣን ስፍራ ላይ የሚገኝ ሰው ከስንት አንዴ ብቻ ነው የዓለምን ትኩረት የሚቆናጠጥና ለሚመራው ሕዝብ የተሻለ መጭ ጊዜን ለማምጣት ታላቅ የተስፋ ምንጭ ሆኖ ተስፋ የሚሰጠው፡፡ የእርሳቸውን - የፕሬዝዳንት ኦባማ - «የዲፕሎማሲ መሰረት አመክንዬ፣ ዓለምን መምራት ያለባቸው መሪዎች አብላጮቹ የዓለም ሕዝቦች በሚጋሯቸው እሴቶችና አመለካከቶች» መሰረትነት ነው የሚለው መርህ እንደሚሰራ የኦባማ መመረጥ እንደሚያረጋግጥ መራጭ ኮሚቴው ተጠቅሶታል፡፡ «ሁላችንም፣ ለዓለም አቀፍ ችግሮች ዓለም አቀፍ ምላሾችን ለመስጠት፣ የድርሻችንን ኃላፊነት የምንወስድበት ጊዜ አሁን ነው፡፡» የሚለውንም የፕሬዚዳንቱን መልዕክት ኮሚቴው እንደሚደግፈው በመግለጫው መጨረሻ አስታውሷል፡፡

ፕሪዝዳንት ኦባማ በአሜሪካ ፖለቲካ ተስፋዎች እንዲያብቡ ያስቻሉ *ስልጡን የ21ኛው ክ/ዘመን ሰው* ናቸው ይሏቸዋል ብዙ ታዛቢዎች፡፡ ለብዙ አሜሪካውያንም የኩራትና የመነቃቃት ምንጭ ሆነዋል፡፡ ከፍርሃት ይልቅ በተስፋ ላይ ለተመሰረተ አዲስ የፖለቲካ አካሄድ ባላቸው ቁርጠኝነት ባገኙት ታላቅ ክብር ብዙዎች አድናቆታቸውን ይገልፀላቸዋል፡፡ የሽልማቱን መርሆች በመከተል ቃል የገቡላቸውን የገቡዓቸውን ሥራዎች ከፍፃሜ ለማድረስ በትጋት እንደሚገፉበትም ይተማመኑባቸዋል፡፡

የአሜሪካ ሕግ አውጭ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሆኑት ናንሲ ፔሎሲ፣ «ፕሬዝዳንት ኦባማ በዓለም በጠቅላላ የአሜሪካንን አመራርነት ለመመለስና በመላ ዓለም የወዳጅነት ቁርኝንትን ለመገንባት እየሰራ ነው። ለዚህ፣ የኖቤለ ሰላም ሽልማት ማረጋገጫ ነው፤ ያም ለአሜሪካ ትውፊት ነው።» በማለት የእንኳን ደስ ያሎት መልዕክታቸውን ለኦባማ አስተላልፈዋል። በፕሬዝዳንታዊው የምርጫ ፉክክር በሪፐብሊካን ፓርቲ እጩ ተፎካካሪ ተደርገው የዴሞክራቶቹን ኦባማን የተፎካከሩት ጆን ማኬን፣ «ይህን እፁብ ሽልማት በመቀበሉ፣ ፕሬዝዳንት ኦባማን እንኳን ደስ አለህ እላለሁ።» በማለት የፕሬዝዳንታቸው የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ መሆን ያሳደረባቸውን ስሜትና ከፍተኛ ኩራት ጠቅሰዋ።

በአሜሪካና በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ያሉ የኦባማን መመረጥ የማይቀበሉት ጠቅሰዋል። ታሊባን በቃል-አቀባዩ አማካኝነት፣ አንዳንድ የአሜሪካ ሪፐብሊካኖች፣ ሒዝቦላሕ፣ ሀማስ፣ በኢራቅ የሚገኙ የአሜሪካን ፖሊሲ ተቺዎችና በርካታ የዓላም ፖለቲካ ታዛቢዎች የኦባማ የመሸለም ነገር እንዳልተዋጠላቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። «ገና ምኑ ተነካና!?» ያሏቸውም አልጠፉም። እነዚህ አስተያየት ሰጭዎች ይህን ቢሉም በሸላሚው ኮሚቴ ተጣጥሏል። ኮሚቴው የኖቤል የሰላም ሽልማት ለፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የተሰጠው ከዚህ ቀደም በሰሯቸው ላቅ ያሉ ስራዎቻቸው ምክንያት መሆኑን በሊቀመንበርነት በመሩት የቀድሞ የኖርዌይ ጠ/ሚኒስትር አማካኝነት ጠቅሷል።

በኢራቅና በአፍጋኒስታን ሁለት ጦርነቶች እያካሄደች ያለችውን አገር የሚመሩት ኦባማ በኖቤል ኮሚቴው ትልቅ ኃላፊነት እንደተጣለባቸውና እንደሌላ ሶስተኛም ጦርነት - የሰላም «ጦርነት» - ሊታይ የሚችል እንደሆነ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የተሰጣቸው ሽልማት እጅግ የሰዎችን ተስፋ የሚያጎን በመሆኑ የሽልማቱን ዋጋ እጅግ ከፍ ለማድረግ ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ከባድ ስራ የሚጠብቃቸው መሆኑ ነው።

*የኖርዌይ ኖቤል ኮሚቴ* በ108 ዓመታት ታሪኩ፣ ለሽልማት ከመረጣቸው ሰዎች ስድስቱ ብቻ ናቸው እስከአሁን ሽልማታቸውን ያልተቀበሉት። በራሳቸው ውሳኔ ሽልማቱን አንቀበልም ያሉ ሁለት ሲሆኑ እነዚህም፣ የ1964ቱን *የሥነ-ጽሑፍ* ሽልማት «እንዴት ተደርጎ፣ እምቢኝ!» ያሉት ዣን-ፓል ሳርትሬና የ1973ቱን *የኖቤል ሰላም ሽልማት* ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ጉዳዮች ሚኒስትር (ዩ.ኤስ. ስቴት ዲፓርመንት ሴክሬተሪ) ከነበሩት ሄንሪ ኪሲንጀር ጋር የተጋሩተን ሽልማት ውድቅ ያደረጉት የያኔው የቪየትናም ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ዱክ ታሆ ናቸው። አዶልፍ ሂትለር ሶስት ሎሬቶች ሽልማታቸውን እንዳይቀበሉ ማገዳቸው ይታወቃል። እነዚህም፣ ሪቻርድ ኩን (1938 - በኬሚስትሪ)፣ አዶልፍ ቡተርንድት (1939 - በኬሚስትሪ) እና ጀርሀርድ ዶማግክ ( 1939 - በሜዲስን) ናቸው። ቦሪስ ፓስተርናክ ደግሞ በሶቭየት ሩሲያ ባለስልጣናት፣ የ1958ቱን የሥነ-ጽሑፍ ሽልማት እንዳይቀበሉ የታገዱ ናቸው።

## መጣጥፎች

# ይድረስ ለምርጫ 2002
# ተላከ ከምርጫ 97

**በአቤ ቶኪቻው**

abeto2007@yaoo.com

*ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል ግራ ቀኙ እንደምን ውሎ አድሯል? «በሰላም ውሎ ይደር መንደሩ ክፉም አያሰማን በሃገሩ» የምትለዋን የአርቲስቶቻችንን ህብረ ዝማሬ በፀሎት መልክ ሲያንጎራጉር ለሰነበተ እንደኔ ያለ ሰው ክፉ ነገር ቢያጋጥምም «ደህና ነኝ» ሲሉት ደስ ይለዋልና እባክዎን ወዳጄ «ደህና ነኝ» ይበሉኝ:: ጎሽ እግዜር ያክብርልኝ::*

*እኔ የምለው ወዳጄ የዘንድሮ ምርጫ መጣሁ መጣሁ እያለ ነውኮ! እራስዎን በየትኛው ደረጃ አዘጋጅተውታል? መራጭ ሊሆኑ አስበዋል? ወይስ ተመራጭ ሊሆኑ አስበዋል? ወይስ ታዛቢ ሊሆኑ አስበዋል? ብቻ ይዘገጃጁ እና በተሰማሩበት ዘርፍ ንቁ ተሳታፊ ይሁኑ! (ይህ የእኔ የወገኛ ወዳጅዎ መልዕክት ነው::) ወዳጄ ለዛሬ ይጥልዎ የቀረብኩት ምርጫ 97 ለምርጫ 2002 የፃፈውን ደብዳቤ ነው:: አፈር ስሆን ይኮምኩሙልኝ...*

*ይድረስ ለምርጫ 2002...*

*ውዱ እና ተናፋቂው ምርጫ 2002 ለጤናህ እንደምን ውለህ አድረሃል? የተሟላ ጤንነት ላይ እንደምትገኝ እገምታለሁኝ:: ምክንያቱም ከታላላቆቼም ሆነ ከራሴ ልምድ እንዳየሁት የኛ የምርጫዎች ጤና የሚቃወሰው ከምርጫው በኋላ እንጂ ከዛ በፊት አይደለምና:: እናም ዛሬ ጥሩ ጤንነት ላይ እንደምትሆን ጥርጥር የለኝም:: አይዞህ እንዲህም ስልህ ደግሞ ከምርጫው በኋላ ጤናህ መቃወሱ አይቀርም እያልኩህ አይደለም:: ዋናው ዘዴኛ መሆን ነው:: የእኔን ልጅ ታውቀው የለ? ምነው እንኳ ባልተፈለገ እርግዝና የተወለደ ልጅ እያለ ሀገሪው ያወራለትን አንድያ ልጄን እንዴት ትዘነጋዋለህ? ይህ ልጄ የመሟያ ምርጫ ይባላል:: ያየኸው እንደሆነ ብልህ ዘዴኛ እንደሱም አልተፈጠረ:: እናም የእርሱ አይነት ብልሃተኛ ከሆንክ ከምርጫው በፊትም ሆነ ከምርጫው በኋላ አስተማማኝ ጤንነትን ትጎናጸፋለህ:: ልጅህ የማሟያ ምርጫ በምን ብልሃት ከምርጫ በፊትም ሆነ ከምርጫ በኋላ ፍፁም ጤነኛ ሆነ? ብለህ ልተጠይቀኝ ትችላለህ:: ጥሩ ጥያቄ ነው:: ይሔውልህ ከመራጩ የሚበልጥ ተመራጭ አዘጋጀልህ ከዛም ውስጥ አብዛኛው (መቼም ሁሉም አይባልም ብዬ ነው::) አብዛኛው የገዢው ፓርቲ አባላት ሆኑ:: የምርጫ ጣቢያ በየመንደሩ ተቋቋመ (ያው በየ ቤቱ አይባልም ብዬ ነው::) አንዳንድ ተቺዎች ልጄ ማሟያ ምርጫ ያቋቋማቸውን የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት እና የመራጩን ቁጥር ማነስ ሲገልፁ «ለአንድ መራጭ አንድ ኮሮጆ» እያሉ ሲያሽሙሩት ከረሙ ልጄም ዋዛ አይደለም እና «አንድ ለአንድ በመወሰን ራሳችንን ከአላስፈላጊ ህመም እንጠብቅ» ሲል ቁርጡን*

ነገራቸው:: የሆነ ሆኖ ልጄ ማሚያ ከምርጫው በፊትም ሆነ ከምርጫው በኋላ ፍፁም ጤነኛ ሆኖ አለፈ:: የሆነው ሆኖ ወንድሜ ምርጫ 2002 ጤናህ የተሟላ እንዲሆን እመኝልሃለሁኝ:

እኔ የምልህ ወንድሜ በአሁኑ ሰዓት ትልቁ ስራ ፉከራ ነው:: እናም ፉከራው እንዴት ይዞሃል? ብሎ መጠየቅ ይገባል:: እውነት እንዴት አደረገህ ጃል? ሰሞኑን «መጪው ምርጫ ነፃ ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል!» እያልክ ስትፎክር እየተሰማ ነው:: ተገቢ ነው:: ማንኛውም ምርጫ ከምርጫው በፊት ማለት ያለበት ትልቁ ነገር ቢኖር «ምርጫው ነፃ ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል!» የሚለውን ቃል ነው:: እናም ይህንን በማለትህ የታላላቆችህን ወግ አልሻርክም እና ኮርተንብሃል:: ነገር ግን በመሃል እስከዛሬ ሌሎቻችን ተጠቅመንባት የማናውቀውን  አንድ ዲስኩር አንተ ደጋግመህ ስትደሰኩረው በመስማቴ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ብዬ ሳላማህ አልቀረሁኝም:: «መጪው ምርጫ የህዝብ አመኔታ እንዲኖረው አደርጋለሁኝ» ስትል በተደጋጋሚ ሰምቼሃለሁኝ:: ምን ለማለት ፈልገህ ነው ወንድሜ? የማን ምርጫ «የህዝብ አመኔታ አጥቷል»  አሉህ? መቼም የመጀመሪያ ታላቅህ ነኝና የምትናገራቸውን ንግግሮች በሙሉ አሽሙሩ ለእኔ ሊሆን ስለሚችል በጥርጣሬ ነው የምመለከተው:: ልክ በእኔ ጊዜ «የዘንድሮን ምርጫ ማጭበርበር ሳያስፈልገን እናሸንፋለን!» በተባለ ወቅት ከእኔ በፊት የነበሩት ምርጫዎች «የማን ተጭበረበረ?» ብለው እንዳኮረፉት ሁሉ እኔም ዛሬ አንተ የምትናገረው ንግግር በሙሉ ይመለከተኛል ብዬ አስባለሁኝ:: ከሁሉ ደግሞ ያበሳጨኝ «ካለፈው ምርጫ ስህተት ተምረን...» የምትላት ንግግር ነች:: ሌሎች ንግግሮችህ ላይ እንኳ ስም ካልጠቀሰ ምን ጥልቅ አደረገኝ እያልኩኝ አልፌሃለሁኝ ይሄ ግን በቀጥታ ለእኔ የተሰነዘረ በመሆኑ በእውነት አበሳጭቶኛል:: ተው እንጂ ወንድሜ የእኔን ዘመን ስህተተት እያጎላህ ራስህን ከወዲሁ ንፁህ ብፁህ አታድርግ:: ግድ የለህም እኔን «የስህተት አባት» ብለህ ከመፈረጅህ በፊት ራስህን ፈትሽ:: ለምን ክፉ ደግ እንነጋገራለን ብዬ እንጂ የአንተ ተመራጮች እኮ ገና ከአሁኑ ርስ በርስ መባላት መናከስ መነታረክ የጀመሩ ናቸው:: በእኔ ግዜ ክርክሩ እና ሙግቱ ገዢ ፓርቲ ከተቃዋሚ ነበር:: አሁን ይሔው በአንተው ዘመን ክፉ ደብተራ እንደዋለበት ሰው አንድ የተባሉት ሁለት እየሆኑ ገና በጠዋቱ ጠብ ጠብ ብሏቸው ሳይ «የማያድግ ህፃን...» የሚለውን ተረት ያስታውሰኛል:: እናም ወዳጄ ከእኔ ስህተት ለመማር መሞከርህ የሚደነቅ ቢሆንም ዕጩዎችህን ግን ምከር:: በቀጣዩ «ምርጫ ደግሞ ከምርጫ ሁለት ሺ ሁለቱ ስህተት ተምረን...» እንዳትባል ተግተህ ስራ:: ተግተህም ፀልይ:: እዚህ ላይ ወቀሳዬን ቆም ላድርግልህና ሌሎች ጨዋታዎችን ላጫውትህ:: እባክህን ትዝታ አያረጅም በሚለው ዜማ እያጀብክ ተከተለኝማ!

ትዝታ አያረጅም ሀ

በእኔ ጊዜ ከምርጫ ቅስቀሳዎች አንዱ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ተቃዋሚውም ሆነ ገዢው ፓርቲ ያላቸውን የሰው ሃይል የሚፈታተሹት ትዕይንተ ህዝብ ነበር:: በዛ ትዕይንተ ህዝብ ታድያ ህዝቡ በአንዱ ቀን የገዢው ፓርቲን በሌላው ቀን ደግሞ

የተቃዋሚውን ቲሸርት ለብሶ ወጣ፡፡ ይሔም ከሚያስተላልፈው መልዕክት አንዱ፤ ሁለታችሁም ወዳጆቻችን ናችሁ የሚል ሲሆን ይሔንን የተገነዘበ ገዢም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ ግን አልነበረም፡፡ እና ሁሉም በየፊናው «ይህንን የህዝብ ማዕበል ይዘን...» ሲል ፎከረ፡፡ ሁለተኛው የትዕይንተ ህዝቡ መልዕክት ደግሞ «በምርጫው የምንሳተፈው እኛ ሁሉ ነን፡፡» የሚል ነበር፡፡ ይህ ከእኔ በፊት ተከናውኖ አይውቅም እና እንደ ስኬት ሊቆጠርልኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ ወዳጄ ምርጫ 2002 ይህንን አንተም አድርገው፡፡

ትዝታ አያረጅም ለ

በአንድ ገጠር ቀበሌ የሚከተለው ሆነ፡፡ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ የሚበጀውን መረጠልህ፡፡ (በነገራችን ላይ ከእኔ ከምርጫ 97 በፊትም ሆነ ከዛ በኋላ ህዝብ በነቅስ ወጥቷል፡፡ እንደዛን ጊዜ ያለ ትክክለኛ የህዝብ ነቂስ ግን ታይቶ አይታወቅም) እናልህ በቀበሌው መራጩ ተመራጩ ሳይቀር አንድ ፓርቲን ብቻ መርጦ ሌሎቹ ያልተወዳደሩ ይመስል ዝም አላቸው፡፡ ታድያ ቆጠራ ሲደረግ ከዛ ሁሉ ህዝብ አንዲት ብቻ የተለየች ምርጫ ተገኘች ይህንን የተመለከቱ ያልተመረጡ ፓርቲዎች (ፓርቲዎቹ ብዙ ሆነው ሳይሆን ለማክበር ብዬ ነው ስም ከምጠቅስ አናንተ ብዬ ስጠራቸው ማን እንደሆኑ ይገባሃል ብዬ ነው፡፡) «ምርጫው ተጭብረብሮ ነው እንጂ እንዴት አንድ ሰው ብቻ እኔን ይመርጠኛል?» አሉልህ፡፡ «ለነገሩ እውነት አላቸው ቢያንስ ተወዳዳሪዎቻቸው እንኳ እንዴት አይመርጧቸውም?» ብለው ታዛቢዎችም የግርምት አስተያየት ሰጡ፡፡ ኋላ ላይ ምርጫው ይደገም ሲባል የሣገሬው ህዝብ ምን እንዳለ ታውቃለህ «እኛ ሁላችንም ተስማምተን የመረጥነውን መርጠናል፡፡ ከዚህ በኋላ የምናጣራው ሣገሬው የመረጠውን ትቶ ሌላ የመረጠው ያ አንድ ሰው ማን ነው? የሚለውን ነው እንጂ ዳግም ምርጫ የለም» አሉልህ፡፡ ነገር ግን «ምርጫው ተጭበረበረ» ያሉት ሣይለኞቹ ነበሩና «ዳግም ምርጫ አድርገናል አሸናፊም ሆነናል» አሉልህ፡፡ ህዝቡም አዘነ፡፡ ይህ ጥሩ አይደለምና ከዚህ ተግባር እንዲርቁ ሣይለኞችህን ምከር፡፡

ትዝታ አያረጅም ሐ

በአንዱ የገጠር ከተማ ደግሞ ምርጫው በአግባበቡ ተደረገና ቆጠራው እስኪደረግ ህዝቡ ኮሮጆዬን እጠብቃለሁኝ እንጂ ቤቴ አላድርም ብሎ ጋቢውን ደርቦ ዱላውን ይዞ አዳሩን ከምርጫው ጣቢያ አደረገልህ፡፡ ይሔን ጊዜ ምሽት ላይ በልቡ ክፉ ሣሳብ ያደረ አንድ አሻጥረኛ ፓርቲያችን ይሸነፍብናል የሚል ስጋት ከያዛቸው ሌሎች ጋር ተባብሮ መብራቱን ማጥፋት... በነገሩ ግራ የተጋባው ኮሮጆ ጠባቂ ህዝብ ሲተራመስ ታድያ አንዱ የአሻጥሩ ተባባሪ ኮሮጆውን ይዞ በጨለማ ሊሰወር ቢሞክር ከጠባቂዎች አንዱ በያዘው ባትሪ አጋለጠዋ፡፡ የት ይግባ? ምንስ ይበል? «አንት ሌባ ኮሮጆውን እንዲህ አቅፈህ የት ልትሔድ ነው?» ብለው ቢጠይቁት «የሌባ አይነ ደረቅ» እንዲሉ «የምን ኮሮጆ ታቅፌያለሁኝ?» ብሎ መመለስ... ጠባቂው ህዝብም ወደታቀፈው ኮሮጆ እያመለከቱ «ይሔ ምንድነው?» ቢሉት «ውይ! ልጄን ያቀፍኩኝ መስሎኝ ተሳስቼ ነው፡፡ ይቅርታ

አድርጉልኝ::» አለልሃ! ይህ አይነቱ ልምድ መሳቂያ ያደርግሃልና እባክህ ምርጫ 2002 ሰዎችህን ጠብቅ::

ትዝታ አያረጅም መ

ከምርጫው በኋላ እኔ ያቀድኩት በሃገሪቱ ትልቅ ለውጥ ይመጣል ብዬ ነበር:: ነገር ግን ትልቅ ለውጥ ሳይሆን ትልቅ «ነውጥ» መጣ በርካታ ንፁሃኖች በጥይት ሞቱ በርካታ ብርቱዎች በድንጋይ ቆሰሉ የዛን ጊዜም አንዳንድ ሰዎች በተኳሾቹ ላይ ፈርደው፤ «ድንጋይ ለያዘ ህዝብ ጥይት ይገባልን?» ብለው በጠየቁ ጊዜ «እኛ ወደ ሰማይ ተኮስን ተባራሪ ጥይትም ተባራሪ ሰዎችን መታ!» ሲሉ መለሱ ሰዉም «ወደ ሰማይ የተተኮሰ ተባራሪ ጥይት በራሪ ሰዎችን ገደለ!» ሲል አሽሞረ:: ይህ መራር አሽሙር በአንተ ጊዜ እንዳይደገም ከቻልክ  ከምርጫው በፊት ለተኳሾች «ልብስ እንጂ መሳሪያ ሲተኮስ አያምርም» ብለህ አስተምር:: ለተንኳሾችም «መተንኮስ ያስከትላል የጥይት ተኩስ» ብለህ አስረዳ::

ወዳጄ ምርጫ 2002 እውነትም ትዝታ አያረጅም ብዬ ወደ ኋላ ራሴን ሳየው «ምርጫ 97 ታሪካዊነቱ በርካታ ስህተቶች በመሰራቱ!» ያሰኛል:: ነገር ግን ዛሬ አንተም ቁጭ ብለህ የእኔን ስህተቶች ከመዘከር ይልቅ በእኔ ግዜ ያልተፈጠሩ አዳዲስ ስህተቶችን እንዳትሰራ መጠንቀቅ ይገባሃል::

እንደ እኔ ደምቀህ እንደእኔ አምረህ መጨረሻህ ደም ማፋሰስ  ድንጋይ ማወራወር እና ለእስር መዳረግ እንዳይሆን በፀሎትም በጥንቃቄም ትጋ:: (ለነገሩ አግቦ ተናገርክ አትበለኝና በአንተ ጊዜ እስሩ ቀድሞ ተጀምሯል የሚባል ወሬ እየተወራብህ ነው:: በእኔ ዘመን እኮ ጋዜጠኞች እና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች የታሰሩት ከምርጫው በኋላ ነበር:: ይኸው በአንተ ዘመን የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ከወዲሁ ታስረው ያዩ አንዳንድ ግለሰቦች «ይሔ ነገር ቀብድ ነው እንዴ?» እያሉ ማፌዝ ከጀመሩ ቆይተዋል::)

ወንድሜ ምርጫ 2002 እውነት እውነት እልሃለሁኝ ያ ሰቆቃ ተመልሶ «ታሪካዊ» ከምትባል እንደ ልጄ ማሚያ ምርጫ ፀጥ ረጭ ባለ ስነስርአት የፌዝ ጎተራ ብትሆን ይሻልሃል እልሃለሁኝ::

ናፋቂህ ምርጫ 97!

ወዳጄ እንግዲህ ምርጫ 97 የመከረው ምክር ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ሁላችንም ሃላፊነት አለብንና በአቅማችን እንትጋ በማለት ልሰናበትዎ::

አማን ያሰንብተን!

# አርበኞቻችና ያሳለፏቸው ፈታኝ ጊዜያት

**በአለማየሁ ገ/ማርያም (ፕ/ር)**

የአሜሪካ አብዮት እንደተጀመረ፣ ***የአሜሪካ ሪፐብሊክ*** መስራች ከነበሩት የሚካተቱት ቶማስ ፔይን፣ «እነዚህ ወቅቶች መንፈስን የሚፈታተኑ ናቸው፡፡» ብለው ነበር፡፡ ልክ ቶማስ ፔይን እንዳሉት፣ እነዚህ ወቅቶች የአንድን ሀገር መንፈስ የሚፈታተኑ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ በፖለቲካዊ፣ በማሕበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ስንክሳሮች ባሕር ተዘፍቃለች፡፡ ኢትዮጵያ የሕገ-ወጦች መጫወቻ ምድር ከመሆኗ አስቀድሞ፣ ከውጭ ወራሪዎች ድንበሮቿን የተከላከሉ፣ ክብሯንና ኩራቷን ከአዋራጅ ቡድኖች የጠበቁላት፣ ሊሰነጣጥቋትና ሊከፋፍሏት ካለሙ ጠላቶቿ ሉዓላዊነቷንና ነፃነቷን ያረጋገጡላት የአርበኛ ወታደሮች ምድር ነበረች፡፡

እነዚያ አርበኛ ወታደሮች፣ የሚንቀለቀል ሙቀት ያመቁ በረሃዎችን ያቆራረጡ፣ የሸንተረራማ ተራራዎችን ቅዝቃዜ በጽናት የተቋቋሙ እና በጥሻዎች፣ በሸለቆዎችና ጥንት ጥቅጥቅ በነበሩ ደኖች ወራሪን የተከላከሉ የቅርብ ዓመታት የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አባላት የነበሩ ናቸው፡፡ ዝቅተኛ ደሞዝ የሚከፈላቸውና ብርቱ ስራ የሚሰሩ፣ ከባድ ግዴታ የሚወጡና እጅግ አነስተኛ ድጎማ የሚተቀበሉ፣ ኃያል ቀንበር የሚሸከሙ ነበሩ፡፡ አድናቆት የተነፈጋቸውም ነበሩ፡፡ በዓመታት አገልግሎታቸው ለመገመት አዳጋች ስቃይ ደርሶባቸዋል፡፡ በርካቶች በሀገሪቱ ጥጎች ለጥበቃ በሰፈሩባቸው ስፍራዎች በርሀብ፣ በጥማትና በብቸኝነት ተሰቃይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለሌላ 3ሺህ ዓመታት ነፃነቷን መጠበቋን ለማረጋገጥ፣ ከተግባራቸው ሳይገቱ ባሕር ቀዝፈዋል፣ በሰማያት ላይ ከፍ ብለው ተንሳፈዋል፡፡

ከጥቂት ሳምንታ በፊት፣ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አባላትን ለመሸለም በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አንድ ዝግጅት ተካሂዶ ነበር፡፡ «የጀግኖች ምሽት» ተብሎ የተሰየመው ይህ ዝግጅት፣ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሽላሚ ኮሚቴ የተዘጋጀ ነበር፡፡ ዝግጅቱ ጀግና አርበኛ ወታደሮችን ለመዘከር፣ ለመስዋዕትነታቸው ክብርና አድናቆት ለማሳየት እና ለረዥም ዓመታት አገልግሎታቸው ጥልቅ ምስጋና ለመግለፅ ዓላማው አድጎ የተዘጋጀ ነበር፡፡ በዝግጅቱ የተጠቀሱ ወታደሮች፣ በሁሉም የውትድርና ማዕረግ ላይ የነበሩትን፣ የወደቁትንና በውጊያ ሜዳ የት እንደደረሱ ያልታወቁትን ይወክላሉ ተብለው የተዘረዘሩ ነበሩ፡፡ ሁለት ታሪካዊ ጡረተኛ ጄኔራሎች - ተስፋዬ ኃ/ማርያም እና ካሳዬ ጨመዳ - ላገራቸው ባበረከቱት ተምሳሌታዊና ታላቅ አገልግሎት ክብር ተሰጥቷቸዋል፡፡ በበርካታ የጦር አውድማዎች በጀብደኝነቱ የሚታወቀው ሚሊሺያ አሊ በርኬ፣ በሌሉበት ተሸልመዋል፡፡ ባለፈው ዓመት ጄኔራል ለገሰና ሌሎች በኮሚቴው ተሸልመው ነበር፡፡ እውነት ለመናገር፣ እነዚህ ጄኔራሎችና በርካታ የእነርሱ የበታች ባልደረቦቻው እጅግ

የተዋጣላቸው ወታደሮች መሆናቸውን ያስመሰከሩ ናቸው:: ምክንያቱም ያዝዋቸው የነበሩ ወታደሮቻቸው የተዋጣላቸው ወታደሮች አድርገዋቸዋልና፤ በመሆኑም ሽልማቱ ወታደሮቻቸውንም ይመለከታል::

**እውነተኛ ጀብድና እውነተኛ ቀለሞች**

ለኃብትና ለፖለቲካ ሥልጣን ያለሙ በአገራቸውና በሕዝባቸው ላይ ጦር ያነሱ ቅጥረኞችን የኢትዮጵያ ታሪክ ጠርዞ ያስቀመጠው ነው:: የፖለቲካ ጥማቸውን ለማራመድና የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ፣ እግረመንገዳቸውንም ሲቪሉን ለመጨቆን ወታደራዊ ተቋማትን አላግባብ የተጠቀሙ፣ የመለዮአቸውን ክብርና ታላቅነት የከዱም ነበሩ:: ግና፣ ግዴታቸውን በጥበብ፣ በሥነ-ግባር፣ በጥብቅ ሥብዕናና ክብር ቆራጥ እንደነበሩት በዋሽንግተን እንደተጠሩት ያሉ እውነተኛ የወታደሮች ወታደሮችም ነበሩ:: የጦርነትን ጥበብና የሰላም መንገድን የተካኑም ብቻ ሳይሆኑ የአገርን ዕሴቶች፣ ክብርና ግዴታ በመላ ሕይወታቸው የኖሩ ያልተለመደ ዓይነት የወታደር ፍጡሮችም ጭምር ነበሩ::

የውትድርና ጥበብን መቅሰምና ማስተማር ይቻላል፤ ሆኖም ድፍረት፣ ሙሉዕ ስብዕናና ራስን የበታች ማድረግ አርበኛ ወታደሮቹ የረቀቁበት መገለጫዎቻቸው ናቸው:: እነዚህ የታፈሩ ወታደሮች ሙያቸውን ያዋሉት ለአንድና አንድ ግብ ብቻ ነበር - ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለመከላከል:: በሰላም ጊዜ ወይም በጦርነት፣ በመልካም ጊዜ ወይም በመጥፎ፣ እነዚህ አርበኞች በጭራሽ የዘር ሸማ አልለበሱም፣ የጐሳ ማንነታቸው በጭራሽ ይታይልን አላሉም:: በእሳት ውስጥ ሆነው ሁለት ነገሮችን ብቻ አሳይተዋል - ከአባቶቻቸው የወረሱትን እውነተኛ ጀብድና እውነተኛ ቀለሞች - አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ:: ከሁሉም ነገሮች በላይ፣ ባንዲራቸውን ከፍ አድርገው አውለብልበዋል:: የቤተ-ሰባቸውን መጠበቅ እና የራሳቸውን ደህንነት ጭምር አሳልፈው በመስጠት አገራቸውን አስቀድመዋል:: ይህንንም ያደረጉት ለአገራቸው በነበራቸው የማያጠያይቅ ቆራጥነትና ገደብ-የለሽ ፍቅር የተነሳ ነበር::

በኢትዮጵያ የነፃነት ደወል ሲያቃጭል ታሪክ የእነዚህን አርበኛ ወታደሮች ታላቅ መስዋዕትነቶችና ጀብድ ማውሳቱ የማያጠራጥር ነው:: ቢሆንም፣ በዝግጅቱ የተሸለሙ ጄኔራሎች ግለ-ታሪክና የጦር አውድማ መዛግብት በማንበብ ስለእነርሱ ብዙ ማወቃችን አይቀርም:: ጦርነት በወታደር አእምሮ፣ መንፈስና አካል ላይ በሚያደርሰው አስፈሪ ስቃይ እና በአሳዛኝ የጦርነት ወጥመድ ውስጥ በገቡ ሲቪሎች ስቃይ እንባችን ሳንወደ በግድ ድቅን ይልብናል:: እነዚህ አርበኛ ወታደሮች የጦር አውድማ ውሎዎች ያደረሱባቸውን ጠባሳዎች፣ የስሜትና የመንፈስ ስቃይ ሸክሞቻቸውንና የጦርነት ጥቁር ትውስታዎቻቸውን የምናውቀው ነው:: አገራቸውን ሲከላከሉ የደረሱባቸውን ቁስሎችና የአካል ጉድለቶች ስንመለከትም ብቻ ነው ታላቅ መስዋዕትነታቸውን ልንገምት የሚቻለን::

እነዚህን አርበኛ ወታደሮች ለማዋረድ፣ ስማቸውን ለማጉደፍና ለማሳፈር የተደረጉ ጥረቶችን ከእኛ የተሸሸጉ አይደሉም። ወንጀለኞች ወንጀሎቻቸውን ለመሸፋፈን እነዚህን አርበኛ ወታደሮች እስር ቤት እንደወረወሩም አሳምረን እናውቃለን። ሞራላቸውን ለማቀጨጭ፣ የሚገባቸውን ለመንፈግና ክብራቸውን ለማሳጣት ሁሉንም የማጭበርበር ሙከራዎች ሞክረዋል። ሆኖም አልተበገሩም፤ ከሁሉም በላይ አርበኛ ወታደሮች እንደሆኑ ፀኑ።

**አርበኛ ወታደሮች ምን ነክቷቸው ነበር?**

አንጋፋዎቹ አርበኛ ወታደሮች ሕመማቸውን፣ የልብ ቁስላቸውንና ስቃያቸውን በመዋጥ ተክነውበታል። ያ ጥቂቶቻችን ልንቋቋመው ይቅርና ልንገምተው የሚያዳግተን በበርካታ ዓመታት የተፈተነ የሙያ ብቃት ነው። በእነርሱ መጫሚያ አንድ ማይል ያልተራመድን፣ አውሎንፋስ ያጥለቀለቃቸው በረሀዎችን ውጣ ውረድ ያልቀመስን፣ ተራራማ መሸጎች ጭራሽ ያልተመለከትን እና የጦርነት ሽብርን ጭራሽ ያላየን በርካቶች አብዛኛውን ጊዜ፣ «አንጋፋ አርበኛ ወታደሮች አእምሮ ውስጥ ምን ተከስቶ ነው?!»፤ «ለዓመታት ለአገራቸው ስላበረከቱት አገልግሎትና መስዋዕትነት ትውፊት ምንድን የሚያስቡት?»፤ . . . እያልን በመጠየቅ እንደመማለን።

ለአገር ጥሪ ጆሮአችንን የዝሆን ያደረግን የሆነ የማይካድ እውነታ ተምረናል። አርበኛ ወታደሮቹ የኢትዮጵያ አንድነት፣ ደህንነትና ሉዓላዊነት እንዲሁ የሚታይ አለመሆናቸውን አስተምረውናል። ሽክማችን የተማርነውን ለቀጣዩ ትውልድ ማሸጋገር ነው፡- «በሕግ የበላይነት ስር የተዋሀደች አገርን ለማግኘት የሚከፈል ዋጋ አለ።» ያ ዋጋ ከውስጥና ከውጭ ወራሪዎች ዘላለማዊ ፅናትን የሚጠይቅ የትኩረት ዋጋ ነው።

**አንጋፋ ወታደሮች በጭራሽ አይሞቱም፤ በልቦቻችን ለዘላለም ይኖራሉ እንጂ**

«ሰዎች አገራቸውን ይወዳሉ፤ የሚወዷት ግን ታላቅ በመሆኗ ሳይሆን የራሳቸው በመሆኗ ነው።» ይባላል። ኢትዮጵያ ምንም እንኳ በጣም ድሃና እድለ ጠማማ ብትሆንም እነዚህ አርበኛ ወታደሮች ይወዷታል። ይወዷታል ምክንያቱም በጠቅላ ያላቸው እርሷ ናትና።

አብዛኞቻችን ያን ወይም ይሄን ለእናት አገራችን ማድረግ ይቻለን ነበር ወይ? በሚል እየጠየቅን ሕይወታችንን እናሳልፋለን፤ ድብን ባለ ለሊት ይህን አስተዋፅኦ ወይንም ያን መስዋዕትነት ማድረግ ይቻለን ነበርን? እያልን ራሳችንን እንጠይቃለን። እነዚህ አርበኛ ወታደሮች ግን ራሳቸውን ምንም ዓይነት ጥያቄ መጠየቅ አላስፈለጋቸውም። ከእኛ በተፃራሪ፣ ጥሪውን መልሰዋል።

«አንጋፋ ወታደሮች አይሞቱም፣ ይደበዝዙ ይሆን እንጂ» የሚባል አባባል አለ። የእኛ አርበኛ ወታደሮች ግን እንደዛም አይደሉም። በጭራሽ አይሞቱም፣ እንዲሁም በጭራሽ አይደበዝዙም። በልባችን ለዘላለም እንዲሁ ይኖራሉ። የእኛዎቹ አርበኛ ወታደሮች ለመጨረሻ ጊዜ ሲያሸልቡ፣ ለዘላለሙ ልክ ዓይናቸውን ከመክደናቸው

አስቀድሞ፣ በመጨረሻዋ እስትንፋሳቸው፣ «እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ፤ ቤቴን፣ ጣፋጯን ቤቴን!» እንዳሉ አንዳች ጥርጥር የለኝም።

የማይረሳ ውለታ አለብን። እግዚብሔር ሁሉንም ይባርክ!!!

*/አለማየሁ ገብረማሪያም፣ በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ/ሳንበርናንዲኖ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰርና ሎስ አንጀለስ በሚገኝ አንድ ተቋም የህግ ኮንሰልታንት ናቸው/*

# ስለ ፓርቲዎች ህብረት፤ የፕሮፌሰር በየነ ጥናት

በታምራት ታረቀኝ

ታኅሣሥ 18/2001 ዓም «መድረክ በኢምፔሪያል ሆቴል ባዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ የጥናት ወረቀት ካቀረቡት አምስት ሰዎች መከከል አንዱ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ነበሩ። «የፖለቲከ ድርጅቶች የህብረት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናንትናና ዛሬ» የሚል ርዕስ በሰጡት ባለ 20 ገፅ ጽሁፋቸው የቀድሞው የፖለቲካ ታሪክ ያሉትን በመጠኑ በማሳየት ጀምረው በኢትዮጵያ ተፈጥረው የነበሩ ህብረቶችን/ትብብሮችን ይነካኩና በሁሉም ሂደት ውስጥ ያለፉ መሆናቸውን ገልጸው ከተግባራዊ ተሞክሮአቸው ያገኙትን ልምድ ያካፍላሉ። መድረክ ሊያስተውላቸው የሚገባ ያሉትንም መፍትሄ ያመላክታሉ።

አንድ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ቀናት የቀረውን ይህን ፅሁፍ እንደገና ለማየት ምክንያት የሆነኝ ሰሞነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ የሆነው መድረክ ከፕ/ር በየነ የጥንት ፅሁፍ ትምህርት የወሰደ መስሎ ስላልተሰማኝ ነው።ፕ/ር ከመድረኩ አመራር አባላት አንዱ ሆነው ለፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት ችግር ነበሩ ብለው ጊዜ ወስደው አጥንተው የገለፁት በመድረክ ውስጥ ሳይታረም መስተዋሉ ጥናቱ ሳይታመንበት ቀርቶ ወይንስ ተፈፃሚ ለማድረግ ሁኔታዎች ስላልፈቀዱ በዛው መንገድ [መሄድ]() ተመረጠ ብሎ ጥያቄ አንስቶ ለመወያየትና «ተጣመርን ባሉ ማግስት ተለያየን» የማለትን የሰለቸ መርዶ ዳግም ላለመስማት ይረዳል።

ስህተታቸውን በትዕግስት ጥፋታቸውን በስስት እየቻልንና ድክመታቸው እየሸፋፈንን፤ ያልሰሩትን እየካብንና ሲናገሩ እያጨበጨብን «ሰባተኛው ሰማይ» ላይ እየሰቀልን ፤ተባበርን ሲሉን እንዴትና በምን ሁኔታ እንዳከናወኑት ሳናጤን ስንደግፍ፤ ተለያየን ብለው መርዶ ሲነግሩን ስናዝንና «ድሮስ እነርሱ መች ይሆንላቸዋል» እያልን ስናማርር የመጣንበት [ሂደት]() ከእንግዲህ ማብቃት ይኖርበታል። መታመን በቃል ሳይሆን በተግባር መሆን አለበት ። የሚናገሩትን የሚፈፅሙ የሚፅፉትን የሚያምኑ የአደባባይ እና የጓዳ መልካቸው አንድ የሆነ ፖለቲከኞችን ማየት እንሻለን። በየወንዙ ሲማማሉ ማየት ሰልችቶናል። ያስገኘውም እርባና የለም። ትግላቸው ለውጥ ባያስገኝልንም ዳፋቸው ሲያዳፋን ነውና የኖረው እንቅስቃሴአቸውን

ልንከታተል የሚነግሩንን ልንመረምር የሚሰሩትን በአትኩሮት ልንፈትሽ ተገቢ ይሆናል:: አባልነትም ሆነ ደጋፊነት ጀሌነት መሆን የለበትም::

**የፖለቲክ ድርጅቶችና «ህብረቶች»ድክመቶች**

በጥናት ወረቀቱ በተራ ቁጥር 3 በቀረበው በዚህ ርእስ ስር ፕ/ር በየነ ትኩረት ሰጥተው ያቀረቡት «የአፈጣጠር ጉድለት» ያሉትን ነው:: በተራ ቁጥር 3.1 «ህብረት የሚፈጥሩ ድርጅቶች ከአባል ድርጅቶች ያላቸውን የፖለቲከ መስመር ልዩነትንና እንድነት በተገቢው ባለማወቅና ከዚህም ድክመት የተነሳ የሰፋ የፖለቲካ አቋም ልዩነት የሌላቸው ድርጅቶች በተለያዩ ስሞች እየተጠሩ በአንድ ህብረት ውስጥ አባል ሲሆኑ ይስተዋል ነበር:: ይህ ሁኔታ ለከፍተኛ የጊዜና የሪሶርስ ብክነት ሲዳርግና አባላትንና ደጋፊውንም ግራ ሲያጋባ እንደኖረ ይታወቃል:: ከዚህም የተነሳ ትግሉም ተገቢውን ድጋፍ ከህዝቡ አንዳያገኝ ጥርጣሬን ሲያሰፋ ቆይቷል::» በማለት ይገልጻሉ::

ይህ አብይ ችግር ሆኖ በጥናቱ የተነሳ ጉዳይ ሳይታመንበት ቀርቶ ይሆን ወይንስ አርሞ ለመጀመር የማይቻል ሆኖ ነው? ዛሬም በመድረክ በተመሳሳይ ሁኔት እየፈፀመ ያለው በማለት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል:: በኦህኮና በኦፌዴን : በደቡብ ህብረትና በኢሶዴፓ መከከል የሰፋ የፖለቲካ አቋም ልዩነት ኖሮ ነው በተለያየ ስም የመድረክ አባላት የሆኑት? በስምንቱ የፖለቲከ ፓርቲዋች መከከል ያለው አንድነትና ልዩነትስ በግልፅ ታውቆ ተለይቶ ሰፍሯል? የየፓርቲዎቹን አንድነትና ልዩ ነት በየደረጃው የሚገኙ የሁሉም ፓርቲዎቸ አመራሮችና አባላት እንዲያውቋቸው ተደርጓል? የመድረክ ጉዳይ ጥርጣሬ ከመፍጠር አልፎ ለአንድነት አመራሮች የውስጥ ድክመት መሸፈኛ እየሆነ ነው የሚል ክስ በስፋት እየተደመጠ ነው:: በዚህ ሁኔታ መድረክ ምን አዲስ ነገር ይዞ መጣ ብለን እንቀበለው::

ሌላው በጥናቱ ውስጥ የአፈጣጠር ማሳያ ተብሎ በቁጥር 3.1.3 ገፅ 15 ላይ የቀረበው «ህብረት የሚፈጥሩ ድርጅቶች ብቃታቸው አናሳ በመሆኑ የተፈጠሩ ህብረቶች ዓላማቸውን ሳያከናውኑ ይቀራሉ:: በተለይም በአደረጃጀትም ሆነ በአባላት ረገድ ይህ ነው የሚባል ብቃት የሌላቸውና በአንድ ሁለት ግለሰብ «መሪዎች» አማካኝነት ብቻ «ድርጅት» ነኝ የሚሉትን ሁሉ በአባልነት ይዞ ለመጓዝ መሞከር ለውጤት እንደማያበቃ..» በማለት ይገልፃል:: መድረክን የመሰረቱ ተብሎ የሚገለፁት ስምንት ፓርቲዎች በዚህ መሰረት ቢመዘኑ ፈተናውን የሚያልፉት ስንቱ ናቸው? ስንቶቹ የፓርቲ መዋቅር ማለትም ጠ/ጉባዔ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አላቸው:: ስንቶቹስ የፕ/ር በየነ ጥናት እንደሚለው በአንድ ሁለት ግለሰቦች ብቻ ፓርቲ የሚባሉ ናቸው? ስንቶቹ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት አላቸው?::ግለሰቦችና ፓርቲን በእኩልነት የሚያስተናግደው አዲስ ሊባል የሚበቃው አሰራርስ መስፈርቱ ምን ሆኖ ነው? ሌላም ሌላም ጥያቄ ማንሳት ይቻላል::ይህ እንደ ችግር የተገለፀ ጉዳይ ያውም የጥናቱ አቅራቢ በአመራር ላይ ባሉበት ሁኔታ እንደምን ትኩረት ተነፈገውና ዛሬም ሊደገም በቃ ለሚለው ጥያቄ መልስም ሆነ ማስተባበያ ሊቀርብለት የሚችል አይመስለኝም::

**በህብረቶች እንቅስቃሴ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች፤**

ችግሮቹ ውጫዊና ውስጣዊ መሆናቸውን የገለፀው ጥናት ሰፊ ድርሻ ሰጥቶ የሚያስነብበው ውስጣው ችግር ያለውን ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ በፊደል «ለ»ሰፍሮ የሚነበበው እንዲህ ይላል፡፡ «ህብረቱ የተቋቋመበትን ሁሉም አባል ድርጅቶች የተስማሙበት ፕሮግራም በደንብ ተብራርቶ ያለመቀመጥና በግልፅ የታወቀም ቢሆን የማስፈፀሚያው ደንብና ሥርዓት በብቃት ተቀርፆ ሁሉም የተስማሙበት መሆኑ አለመረጋገጥ»፡፡

መድረክ የተብራራ ፕሮግራምና ደንብ በመስራት ይህኛውን ችግር የተላለፈው ይመስላል ፡፡ ነገር ግን ሁሉም የተስማሙበት ያለመሆን ብቻ ሳይሆን የመድረኩ አባል የሆነው አንድነት ፓርቲ አመራር «መድረክን ተቃወሙ» በማለት በርካታ የአመራር አባላትንና አባላቱን በማባረር አዲስ ሪከርድ ለማስመዝገብ መብቃቱ የእለት ተእለት ዜና እየሆነ ነው፡፡ በጥናቱ ለተገለጹ ጉዳዮች በቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ ካለመስራቱ ባልተናነስ ችግሮች በገሀድ ሲስተዋሉ ከማረም ይልቅ በጀመሩት መንገድ መሄድን መምረጡ ተደረጉ የተባሉ ውይይቶችን ሁሉ እንደ ግብ እንጂ እንደ መማሪያ አልተወሰዱም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይህን ያህል ጊዜ ተወያይተናል ይህን ያህል ሲምፖዚየም አዘጋጅተናል ለሚል ብቻ መዋሉ የወጣውን ገንዘብ ጊዜና የአዕምሮ ሥራ ሁሉ ተጨማሪ ኪሳራ ያደርገዋል፡፡

መድረክ በቃል ጥምረት/ቅንጅት መሆኑ እየተነገረ ፕሮግራሙና ደንቡ ደግሞ የአንድ ውህድ ፓርቲ ሆኖ መቅረቡ የግልፅነት ጉድለት ያለበትና በተምታታ ሁኔታ ውስጥ የሚጓዝ ያስመስለዋል፡፡ ተሳክቶላቸው ከምርጫው በፊት ውህደት ፈጥረው በፍፁም አንድነት ምርጫው ላይ ቢታዩ የሚጠላ ያለ አይመስለኛም፡፡ ግን እንዴት ሆኖ የብሄርና ህብረ ብሄር ፓርቲ ውህደት ይታሰባል፡፡ ስለዚህ የሰሚን ልብ ለማማለል ሲሉ የማይሆን ከማለም ሊሆን የሚችለውን ቅንጅት በፍፁም ግልፅነት የየፓርቲዎቹ አባላት ሁሉ በሚገባ አውቀውትና አምነውበት መፈፀም በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መስራቱ ነው የሚበጀው፡፡

ስለሆነም የፕ/ር በየነ ጥናት «ማን ያርዳ የቀበረ ማን ይናገር የነበረ» ይሉት ነውና ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ ሊሆን በተገባው ነበር፡፡ ፕ/ር በጥናታቸው «ሁሉም አባል ድርጅቶች የተስማሙበት» በማለት የጠቀሱትን ጉዳይ አሁን በተለይ አንድነት ውስጥ እየተነሳ ከለው ጥያቄ አንፃር እንዴት እንደሚመለከቱት አይታወቅም፡፡ የመድረኩ የአመራር አባል እንደመሆናቸው በልምድ ያከበቱትን እና በጥናት ወረቀታቸው ላይ ያሰፈሩትን ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይገባቸው ነበር፡፡

የመድረክ አንድነትን ጉዳይ በተመለከተ ፕ/ር በየነ እስከሁን ያሉት ነገር አልተሰማም፡፡ በአንድነት ሰፈርም ብዙ አይታዩም፡፡ የመድረክ ስልት ቀማሪዎች የሚባሉትና ከአንድነት አመራሮች ጋር አዘውትረው የሚታዩት ዶ/ር ነጋሶ እና አቶ ስየ «ሁሉም አባል ድርጅቶች የተስማሙበት» የሚለውን የፕ/ር በየነን የጥናት ውጤት አንድነት ውስጥ እየሆነ ካለው ጋር እንዴት አጣጥመው እየሄዱ እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ድርጅት ማለት መሪዎቸ ማለት ከልሆነ በስተቀር የመድረክ ጉዳይ በሁሉም አባል ድርጅቶች ውስጥ ግልፅ ውይይት ተደርጎበት አግባቢ ደረጃ እንዲደረስ ሁለቱ ግለሰቦች ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ነገሮችን ሁሉ አይቶ

እንዳላየ ማሳለፍና «ወንበሩ ላይ» ካለው ጋር ተስማምቶ ግፋ በለው ማለት ከማንም በላይ የሚጎዳው መድረክን ይሆናል፡፡

የፐ/ር በየነ ጥናት በተራ ቁጥር 3.1.3 በፊደል መ «የህብረቱን ዓላማዎች በተግባር ለመተርጎም አስፈላጊው አቅም ያለመኖር በተለይ በዘመነ ኢህአዴግ የተፈጠሩትን «ህብረቶች» በእጅጉ የተፈታተናቸው ጉዳይ ነው፡፡ ዘወትር ይታይ የነበረው ስለ «ህብረት» መፈጠር አስፈላጊነት አጉልቶ ማቀንቀንና እነርሱን ለመፍጠር መጣደፍ እንጂ «በምን መልክ በቂ አቅም አግኝቶ የተመሰረተበትን ግብ ይመታል» የሚለው ጥያቄ ብዙ ትኩረት ሲያገኝ አልነበረም፡፡ እስከ ዛሬም በዚህ ረገድ በታሳቢነት ተይዘው የቆዩት ሁለቱ የአቅም ምንጮች የየራሳቸው ችግሮች ነበሯቸው» በማለት ይገልፃል፡፡

ይህ በጥናቱ የተገለጸ መሰረታዊ ችግር በመድረክ ምስርታ ሂደት ሰፊ ትኩረት ሊሰጠው ሲገባ በተግባር የሚታየው ግን የጥናት ወረቀቱ እምፔሪያል ሆቴል ከቀረበ በኋላ ዘወር ብሎ ያየው ያለመኖሩ ነው፡፡ ጥናቱ በቂ አቅም ማግኘት ያለመቻልን ለነበሩት «ህብረቶች» አንድና ዋና ችግር አድርጎ መግለፁ እየታየ መድረክ ተጨማሪ አቅም መፍጠር ቀርቶ ያለውንም የሚያሳጣ ሥራ እየሰራ ነው የሚታየው፡፡  የአንድነት ፓርቲ አመራር ከመድረኩ አባላት በሚያገኘው አይዞህ ባይነት በፖለቲከ ውሳኔ ያባረራቸውበተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ 22 አባላትን ማጣት ለመድረኩ ጥንከሬ ይበጃል የሚል ይኖር ይሆን !!

የፐ/ር በየነ ጴጥሮስ ጥናት በግልፅ እንደሚያመለክተው «ህብረት» ስለመፍጠር አስፈላጊነት የሚቀነቀነውን ያህል ህብረቱ እንዴት ለምን መቼ በእነማን ወዘተ ይቋቋም ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የመፈለግ ተግባር አይስተዋልም፡፡ በስሜት ይጀመራል በጥድፊያ ይከናወናል በዛው ፍጥነት መለያየት ይፈጠራል፡፡ በተለይ ምርጫ ሲደርስ አብረን ብንቆም ህዝቡ ይመርጠናል፡ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ይደግፈናል ከሚል የጠበበ ዕይታ በመነሳት የተጣደፈ ህብረት ምስረታ በየምርጫ  ዋዜማ ሲስተዋል የነበረ ነው፡፡ ቀዳሚውን ከተከታዩ ከለዩ፡ የአጭር ጊዜውን ግብ ከረዥም ጊዜው ፍላጎት ሳያደበላልቁ በየፈርጁ ማስኬድ ከልተቻለ ህብረት/ቅንጅት መፍጠር ብቻውን ግብ አይሆንም፡፡ ይልቁንም የተናጠል ጥንካሬን በእጅጉ ስለሚያዳክም ጉዳቱ የከፋ ነው፡፡ በመሆኑም ዛሬ መድረክ በቅድሚያ ሊሰራ የሚገባው ስለ መቀናጀት ብቻ ነው፡፡ ግንባርና ውህደት ደግሞ በየተራ በየደረጃቸው እንደ ፓርቲዎቹ መቀራረብ እንደ ዓላማና ግባቸው መጣጣም እንደ ፕሮግራማቸው ተቻችሎ <u>መሄድ</u> እየታየ የሚሰራ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ ሁሉንም ማቀላቀል አንዱንም ያሳጣል፡፡

ፐ/ር በጥናታቸው የወደፊት አቅጣጫ በማለት ስድስት ነጥቦችን አመላክተው በተራ ቁጥር 1 «የህብረቱን ምስረታ የሚደራደሩት ተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ብቃት ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ አስፈላጊነት» ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ መድረክን የመሰረቱት ፓርቲዎች የቁጥር ብዛታቸው ተፈልጎ ይህም በራሱ ፋይዳ አለው ተብሎ ከልሆነ በስተቀር ሁሉም እኩል መሆን ቀርቶ ተቀራራቢ የሆነ ድርጅታው ብቃት እንደሌላቸው ይታወቃል፡፡ አዲስ አበባ ላይ ከሚገኝ ዋና ቢሮአቸው ውጪ አንድም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሌላቸው የመኖራቸውን ያህል አንድነት ደግሞ ከሰላሳ በላይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አሉት፡፡

ይህም የፐ/ር በየነ ጥናት ትኩረት እንዳልተሰጠው የሚያሳይ ነው፡፡ አስገራሚው ነገር ግን የጥናቱ ባለቤት በአመራር ቦታ የሚገኙ መሆናቸው ነው፡፡

መድረክ ለውይይት የተመሰረተ ነው ሲባል፤ሲፖዚየም በማከሄድም በትናንት ህብረቶች ዙሪያ በተለይ በውስጡ ያሉ የጥናት ወረቀት እንዲያቀርቡ ሲደረግ ከትናንት የተማረ የተሻለ ቅንጅት ይፈጠራል የሚል ተስፋ አሳድሮ ነበር፡፡ በተግባር የምናየው ግን እንዲህ አድርገን ነበር ከማለት ያላለፈ በዛው በትናንቱ መንገድ መሄድን ነው፡፡ አብሮ መስራት የሚወሰነው በጥቂት መሪዎች በጎ ፍቃድና የግል መቀራረብ ሳይሆን በየፓርቲዎቹ ዓላማና መርሆ ላይ የመሆኑ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የሚናገሩትንና የሚፅፉትን በተግባር የሚያውሉ መሆንም መታመንን ለማትረፍ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ «የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ» ይላሉ አባቶች የቃልን ክቡድነት ሲገልጹ፡፡

***/ታምራት ታረቀኝ፣የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባል ናቸው/***

# ኢትዮጵያ፤ሁሌም የምትጨነቅላት አገር

**በብርያን ስትዋርት**

ስለእርሷ መጨነቁን መቼም ማቆም የማይቻለኝ አገር ናት - ኢትዮጵያ፡፡ ዓለምም ቢሆን አይቻለውም፡፡ ላለፉት 25 ዓመታት ተመልሼ በሄድኩኝ ቁጥር ዓለምን ካንቀጠቀጠውና እኛ ካናዳዊያንን ካስደመመን ከ77ቱ ታላቁ ርሃብ በኋላ ብዙ ነገር የተለወጠ መሆኑን ስመለከት ተበራትቻለሁኝ፡፡ ይሁንና አሁንም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ እና አሳሳቢ ነው፡፡

ከቀደመው አሳዛኝ ጊዜ የተረፉ የጥንት ወዳጆች ከሚሊዮን በላይ ህዘቦችን የጨረሰው ርሃብ ዋነኛ ማዕከል በነበረችው ትግራይ የመሻሻል ምልክቶችን ሲያሳዩኝ በኩራት ነው፡፡ በገጠራማው ክፍል የዝናብ ውሃ ለማጥመድ ትናንሽ ማጠራቀሚያ ግድቦች የተገነቡ ሲሆን የደን ተከላ ፕሮጀክቶችም መንገድ ላይ ናቸው፤ በአሁኑ ሰዓት በትንሿ መቀሌ ከተማ ዘመናዊ ዩንቨርሲቲ፣ በሥራ የተጠመዱ ገበያዎች እና ንቁ የወጣትነት ባህል ሊያስጉበኙ ችለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁሉ አበረታች ምልክቶች ቢኖሩም እስከዛሬ ድረስ በዘላቂነት የቆዩ ሁለት ጉዳዮች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ አንድም፣ ኢትዮጵያ ከተቀረው ዓለም እርዳታ እስካላገኘች ድረስ አሁንም እራሷን መመገብ

አትችልም፤ ሁለትም፣ የዚህ እርዳታ ተገማችነት ማጣት ማለት ከፍተኛ የምግብ ቀውስም ሆነ ርሃብ የመከሰቱ ነገር ፈጽሞ ሩቅ አይደለም ማለት ነው፡፡

## የድርቅ የተለመደ መሆን

አብዛኛው የአገሪቱ ህዝብ ህይወቱን የሚታደገው በአየር ጠባይ መለወጥ እየጨመረ የመጣ መሰናክል በሚገጥመው ዝናብ ጠባቂ ግብርና ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ድርቅ በአስርት ዓመታት አንድ ጊዜ ይከሰት ነበር፤ አሁን ግን እስከ ሦስት ጊዜ ሆኗል፡፡ እንደትግራይ ያሉ ቦታዎች ከ77ቱ አስከፊ ጥላ ማምለጥ እንዲችሉ ግዙፍ ተስፋ ቢሰነቅ እንኳ በጥቂት ዓመታት ልዩነት ዝናብ ሊጠፋ፣ ወይም ዘግይቶ ሊመጣ፣ አልያም በከፍተኛ መጠን ሊያወርደው እንደሚችል ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ የዓለም «ቀውስ» ተጋንኖ ያልታየባት ቦታ ናት፡፡ በዚህ ዓመት ስጋቱ በጣም ከፍተኛ ነው፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የምርት መጠን 70 በሙቶ አሽቆልቁሏል፡፡ ከአሁኑ ለሚሊዮኖች የምግብ እርዳታ የተሸከሙ የጭነት መኪናዎች በረጅም ሰልፍ ሲጓዙ ትመለከታላችሁ፡፡ ያለእነዚህ አቅረቦቶች በትክክልም ዓይናችን እያየ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሊራቡ ይችላሉ፡፡

## የህዝብ ቁጥር በእጥፍ መጨመር

የቁጥሩ መጠን አስደንጋጭ ነው፡፡ በቀጣይ ጥቂት ወራቶች ኢትዮጵያ ለ15 ዓመታት የቆየው የአስጊ ድርቅ አስከፊ ውጤቶችን እንደምትመለከት አስተውሉ፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳ ቀድሞውኑ ሰባት ሚሊዮን ህዝቦች በግድቦች እና በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ሥራ በመስራት በሚያገኙት የምግብ እርዳታ ህይወታቸውን እያቆዩ ቢሆንም እጅግ አስከፊው የምግብ ችግር ገና ይጠበቃል፡፡ ይህም አጠቃላዩ ዓለም እና የኢትዮጵያ መንግስት በ77ቱ ርሃብ መመገብ የነበረባቸውን ቁጥር ያህል ይበዛል!

ከሩብ ክፍለ ዘመን [ከ25 ዓመታት] በፊት ኢትዮጵያ 36 ሚሊዮን ህዝብ ብቻ ነበራት፡፡ አሁን ከእጥፍ በላይ ጨምሮ የህዝቡ ቁጥር ወደ 78 ሚሊዮን አካባቢ አድጓል፡፡ ብዙ ህዝብ ማለት ክፉኛ የተቸገሩ ብዙ ቤተሰቦች ማለት ነው፡፡ ያ ትኩረት ለመስጠት በቂ ምክንያት ካልሆነ ዓለም አቀፍ የረድዔት ድርጅቶች አስከፊው ጊዜ ገና የሚመጣ መሆኑን በማመናቸውና የምግብ ክምችቶች ሊያሽቆለቁሉ እንደሚችሉ በመጨነቃቸው ምክንያት ከአሁኑ የሚያድሏቸውን ሬሽኖች እየቀነሱ መሆናቸውንም ጭምር አስተውሉ፡፡ በመላው ዓለም የአየር ሁኔታን የሚያዛባው ተገማችነት የሌለው የፓስፊክ «ኤል ኒኖ» ተጽዕኖ የሚገኘውን ደካማ ምርት እና እንስሳቶች ሊያወድም የሚችል ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የማስከተል አዝማሚያ ሌላው ሁሉን ዳሳሽ ስጋት ነው፡፡

## የመጠባበቂያ እጥረት

በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ለእንዲህ ያሉ አደጋዎች ምንም ዓይነት መጠባበቂያ የለም፡፡ አብላጫ ቁጥር ያለው ህዝብ በትናንሽ የእርሻ መሬቶች ላይ የተሰማራ ሲሆን የያዘውን በጣም ትንሿን ሊያጣ ይችል ይሆናል፡፡ የሁኔታው መባባስ በዚሁ ከቀጠለ ሌሎች ስድስት

ወይም ሰባት ሚሊዮን የሚሆኑትን በርግጠኝነት በእርዳታ ምግብ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ሊያስገድድ ይችላል፡፡ በርግጥ በመጪ ወራቶች 13 ሚሊዮን የሚደርሱ ህዝቦች የምግብ እርዳታ ፈላጊ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ግምቶችም አሉ፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ራስ ምታቴ የጀመረው፡፡ ይህ ምናልባትም ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ካቀረበችው የምግብ እርዳታ ጥሪ እጅግ የገዘፈ ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና እስካሁን ለመረዳት እንደቻልኩት በቂ እርዳታ መቼ ወይም እንዴት እንደሚደርስ ሊያውቅ የቻለ የመንግስት ባለስልጣን የለም፡፡ በተባበሩት መንግስታት በኩል ለተደረገ የእርዳታ ጥሪ ለጋሽ አገራት እየሰጡት ያለው ምላሽ ከመደበኛው በግማሹ እንኳን እየተካሄደ አይደለም፡፡ በመዲናዋ አዲስ አበባ በተባበሩት መንግስታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ኃላፊዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተጨንቀዋል፡፡ ተደጋጋሚነት ያላቸው ቀውሶች -- ጦርነት፣ የመንግስት ብዝበዛ፣ በቂ ያልሆነ የነፍስ አድን መሰረተ-ልማት፣ ደካማ የመገናኛ መንገድ -- ተሳታፊውን ሁሉ ባስጨነቀበት ሁኔታ እንደ 1977ቱ ርሃብ የከፋ ነገር እየተጋፈጥን ስለመሆኑ አለመተንበያቸውን ሳስገነዝብ እወዳለሁ፡፡

ዛሬ የነፍስ አድን እንቅስቃሴ ከቀድሞ በተሻለ የተደራጀ ሲሆን እርዳታ የማቅረቢያ ቁሶች የተሻሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦችን ህይወት እና ጤና ማሰናከል፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ እራሷን በጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም የምታደርገውን ሙከራ በከፍተኛ ሁኔታ ማደናቀፍ በሚችል መልኩ እውነታው አሳዛኝ ነው፡፡

## መዘናጋት

በአሁኑ ሰዓት ችግሩን ለማባባስ ብዙ መንስዔዎች ከእርዳታ ጥሪቱ በተቃራኒ እየሰሩ ነው፡፡ የተቀረው ዓለም እስካሁን ድረስ በኢኮኖሚው አለመረጋጋት ትኩረቱ እንደተሰረቀ ይገኛል፤ እናም የሀብታም አገራት አመለካከት «በምናዋጣው እርዳታ ላይ ከመወሰናችን በፊት ምን ያህል አስከፊ እንደሚሆን ቁጭ ብለን እንመልከት» ዓይነት ይመስላል፡፡ ሆኖም ቁጭ ብሎ መጠበቅ ብቻውን ብዙ ችግሮችን ያስከትላል፤ ምክንያቱም በቅርብ ዓመታት የሸቀጦች ዋጋ እየጨመረ መምጣት በቂ የአደጋ ጊዜ እህሎችንና የመሳሰሉትን ማግኘት ከባድ ያደርገዋል፡፡ የሚያሳዝን እውነታ ቢሆንም የምግብ ቀውሱ እየባሰ በመጣ ቁጥር ዋጋዎችም በፍጥነት እየጨመሩ ይመጣሉ፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን የህዝቦች በስፋት መራብ የገበያ አለመረጋጋትን ይጨምራል፡፡

በተጨማሪ የኢትዮጵያ የተለመደ የአቅረቦት ችግር አለ፡፡ ምንም እንኳን የማቅረቢያ መሣሪያዎች እንደ 1977 መጥፎ ባይሆኑም የምስራቅ አፍሪካ ወደቦች (ኢትዮጵያ የራሷ የባህር በር ስለሌላት) በአፋጣኝ ይጨናነቃሉ፡፡ እንዲሁም ብዙዎቹ መንገዶች ደረጃቸውን ያልጠበቁ ሲሆኑ የጭነት መኪናዎች አቅርቦት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ማዳበሪያዎች (ከረጢት) የተያዘውን የተፈለገውን ምግብ የማድረስ አቅሙ አስተማማኝ አይደለም፡፡ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ኃላፊዎችም በግለሰብ ደረጃ ሌላ አሳሳቢ ነገር እየገለፁ ይገኛል - የኢትዮጵያ የራሷ መንግስት የችግሩን አስከፊነት

ለማድበስበስ ይሞክር ይሆናል፤ ምክንያቱም በዚህ ዓመት ብሔራዊ ምርጫ የሚካሄድ ሲሆን መንግስታት በተለምዶ በገጠራማ ክፍሎች ያለን የምርት መውደም ለማመን በጣም ይቸግራቸዋል::

## በቂ ትኩረት ማጣት

የኢትዮጵያ መንግስት ይሄኛውን ዓመት ካለፈው የባሰ አድርጐ እንደማይጠብቅና «የተራበውን ህዝቡን ለመመገብ የተቻለውን ሁሉ ስለማድረጉ» እንደሚተማመን ገልጿል:: የኢትዮጵያ መንግስት በጐ ለመሆን የሚሞክር ነገር ግን «ከሰለጠነው ዓለም አንጻር የኢኮኖሚ ግንዛቤው አነስተኛ/ኋላቀር የሆነ መንግስት» ሲል የኢኮኖሚስት መጽሔት ባስቀመጠው ፍረጃ ለሚስማሙ የእርዳታ ሰጪ ኃላፊዎች ይህ ግዴለሽ ሊሰኝ የሚችል አመለካከት ነውና በምንም መልኩ ምቾች አይሰጥም::

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አስቸኳይ መፍትሔ የሚጠይቅ እውነታን ለማድበስበስ ግዴለሽ የመሆናቸው እድል የጠበበ ነው፤ ነገር ግን የክልል ኃላፊዎች የራሳቸውን የፖለቲካ ሽፋን ለመከላከል ሲሉ የምግብ እጥረት እየጨመረ መምጣቱን ሊደብቁ እንደሚችሉ ሁልጊዜ ይነገራል:: እኔ እንደተመለከትኩት ከሆነ ኢትዮጵያዊያን የአገራቸው ገጽታ የአደጋዎች ዘላለማዊ ተጠቂ መሆኑን ይጠሉታል:: እንዲሁም ለጋሽ አገራት በዓመታዊ የድረሱልኝ ጥሪ እየተሰላቹ መምጣታቸው በግልጽ ይታያል:: በሁለቱም አመለካከቶች ሊታዘን ይችላል:: ነገር ግን እንዲህ ያሉ አመለካከቶች እውነታዎቹን ይደብቁ ዘንድ ሊፈቀድላቸው አይገባም:: አዎ፣ እየተካሄዱ ያሉት የልማት ጥረቶች በርግጥም መሻሻልን ማስከተል ጀምረዋል:: ሆኖም በምድራችን 12ኛዋ ድሃ ሃገር ኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት እራሷን ሙሉ ለሙሉ ለመመገብ አይቻላትም፣ ምናልባት ቢያንስ ለአንድ ትውልድ ያህል:: አስከፊ የመሬት እና የህዝብ ድህነት አስገዳጅ ሲሆን የትኛውም ዓይነት የኢኮኖሚ ወይም የገበያ ማሻሻያዎች ቢሞከሩ ለዚህ ተደጋጋሚ ሰቆቃ ፈጣን ማብቂያ ለማቅረብ እጅግ ከባድ ነው::

ያኔ በ1977 ርሃቡን በምዘግብበት ወቅት ኢትዮጵያ እንዲህ ዓለም ሊፈታው ያልቻለ ከባድ ችግር ትሆናለች የሚል ሀሳብ ጨርሶ አልነበረኝም፣ ወይም ስጋት አልገባኝም:: ጊዜ የማይገድበው ድህነቷን ለመቅረፍ እረፍት የለሽና ያላሰለሰ ጥረት ስለማስፈለጉ ቦታ አልሰጠሁትም ነበር:: የዛሬ ትልቁ ስጋቴ እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላም ቦታ አለመስጠታችን ነው::

**/ብርያን ስቱዋርት፣የካናዳ *CBC ቴሌቭዥን ዘጋቢ ሲሆን »* በዚሁ የቴሌቭዥን ጣቢያ የሚስተናገደውና በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ትኩረት ያደረገ «Our World» ቶክ ሾው አቅራቢም ነው/**

# «ወገኖቼ አይዟችሁ፤ ከአሁን በኋላ ብዙ አንወድቅም!»

*አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)*

በናፍቆት ዮሴፍ

እኛ ኢትዮጵያውያን እጅግ አኩሪ ታሪክ ነበረን፡፡ አለንም፡፡ በጀግኖች አባቶቻችን ታፍረንና ተከብረን የኖርን፣ በነፃነታችን የአፍሪካዊያን ተምሳሌቶችም ነን፡፡ በሩጫው ዓለም ከጀግናው አበበ ቢቂላ ጀምሮ አሁን እስካሉት ፈርጦቻችን ትልልቅ በሚባሉት የዓለም አደባባዮች አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራችን የተውለበለበ፣ በዩኔስኮ ከተመዘገቡት ስምንቱ ምርጥ ቅርሶቻችን በተጨማሪ ያልተነኩ እምቅና ድንግል ቅርሶች እንዳለን ደግሞ የፈጠጠ ሀቅ ነው፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል ዓለም አንፃራዊ ናትና በተቃራኒው በዓለም የምንታወቅበት አሳፋሪ ገጽታም አለን፡፡ በተለይ እጅግ ደሃ ከሚባሉትና ከሰሀራ በታች ከሚገኙት የአፍሪካ ሀገራት ግንባር ቀደሞቹና ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ ድርቅና ረሃብ መታወቂያችን ናቸው፡፡ በእነ ሉሲ (ድንቅነሽ) የሰው ልጅ መገኛ ተብለን በታሪክ ራስ እንዳልሆንን ከላይ በጠቀስናቸው አሳፋሪ ገጽታዎቻችን ጭራ መሆናችን አንገታችንን ቀና አድርገን እንዳንሄድ እንደቀንበር በላያችን ተጭኖ አጉብጦናል፡፡ ታዲያ ይሄ ለረጅም አ መታት አንገት አስደፊ የሆነ ታሪካችንን እርስ በእርሳችን ተመካክረን ከመፍታት ይልቅ ሌሎች አገሮች መጥተው እንዲፈቱልን እጃችንን አጣጥፈንና አንቀላፍተን ረጅም ጊዜያትን እንዳቃጠልን የባነንነው ምናልባትም ከትናንት ወዲያ እሁድ እለት በቀረበው የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት ሊሆን እንደሚችል አንጠራጠርም፡፡

አሁን አሁን ልመና እንደ ክፍት የስራ ቦታ እና እንደ አማራጭ ተደርጐ የተያዘበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ በዚህም ምክንያት ከተለያዩ የአገሪቱ የገጠር አካባቢዎች በተለያየ ምክንያት ፈልሰው በሚመጡና በልመና ስራ በሚተዳደሩ ሰዎች ምክንያት ከተማችን አዲስ አበባ ለተለያዩ ችግሮች ተጋልጣለች፡፡ የእነዚህ ልመናን መተዳደሪያቸው ያደረጉ ወገኖች ከተማዋን ማጥለቅለቅ የአገርን መልካም ገጽታ ጥላሸት ከመቀባቱም ባሻገር ለአዲስ አበባ ንጽህና መጓደል የበኩላቸውን ተጽእኖ ማሳደራቸው እሙን ነው፡፡

## በምን ምክንያት ከገጠር ፈልሰው ይመጣሉ?

ከተማችን አዲስ አበባ ውስጥ በልመና ስራ ላይ የተሰማሩ ወገኖቻችን የእድሜና የጾታ ገደብ የላቸውም፡፡ ከወጣት እስከ አዛውንት ከታዳጊ እስከ አዋቂ ብርድና ፀሀይ እየተፈራረቀባቸው የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ብዙ በሮችን ሲያንኳኩ አሊያም በአንድ ቦታ ቁጭ ብለው አላፊ አግዳሚውን አንጀት በሚበላ የልመና ዘዴ ሲጠይቁ ውለው የዕለት ጉሮሮአቸውን ደፍነው ያድራሉ፡፡ በመንገድ ላይ በልመና ስራ ከሚተዳደሩት

ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ያገኘናቸውን ወገኖች እንዴት ከአገራችሁ መጣችሁ? ስንል አነጋግረናቸዋል።

የቀይ ዳማ ወጣት ናት። ምንም ችግር ቢያጐሳቁላትም የውበቷ ለዛ አልጠፋም። ስሟ ፀሀይነት አሸኔ ይባላል። የመጣችው ከሰሜን ሸዋ ደራ ከሚባል አካባቢ ሲሆን የተሰደደችው ሁለት እምቦቀቅላ ልጆቿን ይዛ ነው። ለምን መጣሽ? አልናት «ባሌ አባሮኝ»አለችን። አሁን የምተዳደረው በልመና ነው በወር 60 ብር እየከፈልኩ አምስትም አስርም ለቃቅሜ ለልጆቼና ለራሴ የቤት ኪራይ እከፍላለሁ አለችን። አሁን ጠቀም ያለ ገንዘብ ቢሰጥሽ ወደ አገርሽ ትመለሻለሽ ወይ? የሚል ጥያቄ አከልንላት። እሷም ፈገግ ብላ «እንዴታ ጐጆ የምቀልስበትና የምቋቋምበት ካገኘሁ እዚህ ምን እሰራለሁ?» ስትል አታንጉኝ አይነት አሽሙር ጣል አደረገች።

### የመፈናቀሉ መንስኤዎች ምንድናቸው?

አብዛኛዎቹ አባቶች በዝናብ እጦት ምክንያት ሞፈርና ቀንበራቸውን ሰቅለው እንደተሰደዱ አጫውተውናል። እናቶችም እንዲሁ ተያይዞን ከምናልቅ ብለን ባለቤቴ ግማሽ ልጆች ይዞ ቤት ይጠብቃል እኔ ደግሞ ተሰደድኩ ይላሉ። በወጣትነት እድሜ ላይ ሆነው ወደ ልመና የገቡ ሴት ልጆች ደግሞ ለመሰደዳቸው እንደዋና ምክንያት የሚያቀርቡት ያለ አቻ ጋብቻ እና ወላጅ አልባነትን ነው።

እቴነሽ የተባለች ወጣት ናት። ከሁለት ልጆቿ ጋር ሰሜን ሆቴል አካባቢ አገኘ ናት። የመጣችው ከጐንደር እንደሆነና በሰባት ዓመቷ እንደወጣች ነገረችን። ለምን በለጋ እድሜሽ ቀየሽን ለቀቅሽ? አልናት። «እናትና አባቴ ሞተው ወላጅ አልባ ሆንኩኝ፣ ከዚያም የሚያሳድገኝ ሲጠፋ አዲስ አበባ ከምትገኝ አንዲት አክስቴ ጋር ተቀምጩ መማር እንደጀመርኩ አክስቴም ታማ ሞተች በዚህን ጊዜ 15 ዓመት ሆኖኝ ስለነበር ትምህርቴን አቁሜ በሰው ቤት ሰራተኝነት ተቀጠርኩኝ እዛ ቤት ውስጥ አንድ ዓመት እንደሰራሁ አሰሪዬ ሚስቱ በሌለችበት ደፈረኝ። ማርገዜን ሲያውቅም ከቤት አባረረኝ ከዚያ በኋላ ጐዳና ላይ ወጥቼ ልጄን ተገላገልኩ» ስትል አጫወተችን። ታዲያ ለምን ሌላ ደገምሽ? የእኛ ጥያቄ ነበር። «ኧረ ወዲያ! ሴት ልጅ ጐዳና ከወጣች ምን መላ አላት ብለሽ ነው? ምንስ ጥላ ከለላ አላት? አንዱ በግድ ተገናኘኝ በዛው አረገዝኩኝ» ስትል የችግሩን አስከፊነትና ተደራራቢነት አጫወተችን። ይህች ወጣት መቋቋሚያ ብር ቢሰጣት ወደ ጐንደር እንደማትመለስ ግን እዚሁ አዲስ አበባ በጉልት ንግድም ቢሆን ለመተዳደር ቁርጠኝነቷን ነገረችን።

ያነጋገርናቸው በርካታ በልመና የሚተዳደሩ ወገኖች የሚረዳቸው ካለ ወደ ቀያቸው ለመመለስ ፈቃደኞች ናቸው። «ሁሌ ፎቶ ታነሱናላችሁ ወይ አትረዱን ወይ መላ አትፈልጉ ዝም ብላችሁ ፎቶ ማንሳት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? ብለው የወረፉንም አልጠፉም።

**በልመና ላይ ላሉ ሰዎች አምስትና አስር ሳንቲም መስጠት መፍትሄ ነው?**

«የአዲስ አበባ ህዝብ ሩህሩህ ነው የሚለምኑት ጠግበው እስኪደፉት ድረስ የሚበሉትን ይሰግሳቸዋል:: ከዚያም አልፎ ተርፎ ብርም ሳንቲምም ይሰጣቸዋል:: ግን ይሄ ጉዳይ ወደ ልመና የሚገቡ እንዲበዙ ምክንያት ሆኗል::» ያሉት ወ/ሮ ውብአለም ከበደ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው:: እንደምን? አልናቸው «እኔ እንደማውቀው ልመና ህሊናን እስከሽጡ ድረስ አድካሚ አይደለም:: ከላይ እንደገለጽኩት የአዲስ አበባ ሰው ለልመና ለመጡ ሁሉ እጁን ሲዘረጋ ይህን አጠራቅመው ወደአገራቸው ሲመለሱ ይህንን ያዩ የገጠር ሰዎች ሀብትና ንብረት እያላቸው ወይ ባል ወይ ሚስት ይሰደዳሉ:: በዚህ ምክንያት ቁጥሩ ቢጨምር እንጂ አዲስ አበባ ላይ የሚለምን ሰው ይጠፋል የሚል እምነት የለኝም::» ሲሉ ጥፋተኛው ተመጽዋቹ ሳይሆን ሰጪው እንደሆነ ወ/ሮ ውብ ዓለም በአጽንኦት ይናገራሉ::

እርግጥ ነው ሳይቸግራቸውም ከአገራቸው እየወጡ ከተማ የሚያጨናንቁ የኔ ቢጤዎች ሞልተዋል:: ችግሩ  ሰው ተቸግሮ ይምጣ  አሊያም አዲስ አበባ ብር የሚታፈስ ስለሚመስለው ብቻ ቤቱን ንብረቱን እንዲሁም ልጆቹን ጥሎ የሚመጣውን መለየቱ ላይ ነው:: ያም ሆነ ይህ «ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶስዬሽን» ፋና ወጊ ስራዎችን እየሰራ ነው::

**ለመሆኑ ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶስየሽን ማነው?**

ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶስየሽን ከ18 አመት በፊት በአቶ የማነ ወ/ማርያም የተቋቋመ የበጐ አድራጐት ድርጅት እንደሆነ በኤልሻዳይ ውስጥ በበጐ ፈቃደኝነት ስራ እያገለገሉ ያሉት አቶ ጌታቸው ተስፋዬ ገልጸውልናል::

ይህ ድርጅት ስራ የጀመረው አምስት ወላጅ አልባ ህጻናትን በማሳደግ ሲሆን ከዛም በኋላ ከ900 በላይ ህፃናትን በማሳደግና በማስተማር ብዙ ኢንጂነሮችን፣ ዶክተሮችንና በተለየዩ ሙያ ላይ የተሰማሩ ዜጐችን አፍርቷል::በአሁኑ ጊዜ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በሐረርና በድሬዳዋ ቅርንጫፎችን በመክፈት መጠነ ሰፊ በጎ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል:: ይህ ድርጅት ከዚህ ቀደም የተለያዩ ገቢዎችን በማሰባሰብ ከ28 ሺህ በላይ በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን ወደቀያቸው በመመለስ የበኩሉን የተወጣ ድርጅት ነው::

የአልሻዳይ መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ የማነ ይህንን ስራ ለመስራት ሲነሱ መጀመሪያ ጥናት አካሂደው ነበር:: ጥናቱን ሲያካሂዱ እራሳቸው ተመጽዋች ሆነው ጉዳና እያደሩ አዳፋ ልብሶችን እየለበሱና ፍርፋሪ እየበሉ ነው የሚሉት በኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶስየሽን ድርጅት ውስጥ በበጐ ፍቃደኝነት የሚያገለግሉት አቶ ጌታቸው ተስፋዬ ናቸው:: እንደ አቶ ጌታቸው ገለፃ ይህ በጐ ተግባር ትክክለኛ ኢትዮጵያዊነትን የሚያሳይና አላማውም የተቀደሰ ስለሆነ ሁላችንም ከድርጅቱ ጐን ልንቆም ይገባል ብለዋል::

በኤልሻዳይ መስራችና ስራ አስኪያጅ በአቶ የማነ የተጠናው ጥናት እንዳመለከተው በአዲስ አበባ ውስጥ ከ200 ሺህ በላይ በልመና የተሰማሩ ወገኖች የነበሩ ሲሆን ወደ 28 ሺህ የሚጠጉት በኤልሻዳይ አማካኝነት ወደ ቀያቸው ሲመለሱ አሁን ደግሞ ከ170 ሺህ በላይ ነዳያን በከተማዋ እንዳሉና በስታዲየም የተካሄደውም ኮንሰርት እነዚህን ወገኖች ወደቀያቸው ለመመለስ እንደሆነ አቶ ጌታቸው ገልፀው «የዛሬው ኮንሰርት ከገቢው ይልቅ የልመናን አስከፊነት ለወገን ማሳወቃችን አብላጫ ጥቅም አለው እርግጥ ነው ከዛሬው ኮንሰርት ችግሩን ለመቅረፍ መነሻ የሚሆነንን ገንዘብ ያገኘን ይመስለኛል፡፡» በማለት አጠቃላይ የኮንሰርቱ ገቢ ሰሞኑን ለሚዲያዎች ይፋ ይሆናል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

**ድር ቢያብር አንበሳ ያስር**

በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው በትብብር ችግራችንን ከመፍታት ይልቅ የተቸገሩ ወገኖችን እያየን የሀበሻ የመጀመሪያ እርዳታ የሆነውን ከንፈር መጥጦ ማለፍ እንጂ ወደ መፍትሄ ሃሳብ ለመምጣት መነሳሳትን አናውቀውም፡፡ በትናንት በስቲያው ኮንሰርት ላይ ያየነው ጉዳይ ለመሆኑ ይሄን ትብብራችንን እስከዛሬ የት አስቀምጠነው ነው የመጥፎ ታሪክ ባለቤት የሆነው? ብለን እንድንጠይቅ አስገድዶናል፡፡ በኮንሰርቱ ላይ የታየው የህዝብ ስነ-ስርዓት መላበስ፣ በአርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ይሰበክ የነበረው እንዋደድ እና ማንንም አንጥላ፣ በአገራችን አሉ የተባሉ ትልልቅ የንግድ ተቋማት አጋርነት፣ የአዲካና የኤምጂ ፕሮሞሽን ቀና ትብብር፣ ህዝቡ የኑሮ ውድነቱን ሳይፈራ ቲኬቱን ከ10-300 ብር ለመግዛት ያሳየው ተነሳሽነት እውነት ለመናገር ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ያሰኛል፡፡ በስታዲየሙ እጅግ የሚያኮራ ታሪክ ተሰርቷል፡፡ ቴዲና ኤልሻዳይ እንዲሁም አጋር ድርጅቶች የዜግነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ ህዝቡም ድህነትን ድል ለመንሳት ያለውን ተነሳሽነት ከቀጠለበት በንድፈ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ድህነት ተረት ይሆናል፡፡

የሆነ ሆኖ አሁንም የተፈናቀሉ ወገኖችን ወደቀያቸው በመመለሱ ስራ ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ ችግሩ ስር ነቀል ለውጥ አያመጣም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ምክንያታቸውን ጠይቀናቸው ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

በተሰበሰበው ገንዘብ ወደቀያቸው የሚመለሱ ወገኖች እዚያ ከደረሱ በኋላ ተመልሰው አዲስ አበባ ላለመምጣታቸው ማረጋገጫ የለንም ይላሉ አቶ ብርሃኑ ይገዙ፡፡

አቶ ብርሃኑ ይገዙ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/04 ነዋሪ ናቸው፡፡ የእርሳቸው አስተያየት ይህ ጉዳይ በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች ትከሻ ላይ ብቻ የሚጣል ሳይሆን መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እልባት ሊያበጅለት ይገባል ባይ ናቸው፡፡ በእነዚህ በጎ ፈቃደኞች አማካኝነት ወደ አገራቸው የሚመለሱት ወገኖች ተመልሰው እንዳይመጡ ወይም ሌሎች እንደ አዲስ እንዳይሰደዱ ጥብቅ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው በስተቀር የበጎ ፈቃደኞችን ድካም ገደል ይሰደዋል ባይ ናቸው፡፡

ከነዋሪዎች የቀረበ ሌላም አስተያየት አለ፡፡ «ከየክልሉ የመጡና በልመና ላይ የተሰማሩትስ በዚህ መልኩ ወደ ቀያቸው ይመለሱ እንበል፤ እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ

ተወልደው በአላዋቂነትም ይሁን በችግር ጉዳና ላይ የወጡ እንዲሁም አባትዬ እናትዬ እኛችሁን ዘርጉልን በማለት ቀን በቁልምጫ ሲለምኑ ውለው ማታ ጨለማን ተገን በማድረግ ሞባይል ቦርሣ፣ የአንገት ወርቅና የመሳሰሉትን በመዝረፍ ሕብረተሰቡን የሚያሰቃዩት ምን መፍትሄ ሊበጅላቸው ነው?» የሚል ጥያቄ ያቀረቡም ነበሩ፡፡ ይህም ሊነሳ የሚገባውና አፋጣኝ መፍትሄ የሚያስፈልገው እንደሆነ፣ በዚህ ጉዳይ የሚመለከተው አካል መላ ሊፈልግለት ይገባል የሚለው መልዕክታችን ነው፡፡

በመጨረሻም በኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፐመንት አሶስየሽን ውስጥ በጐ ፈቃደኛ የሆኑት አቶ ጌታቸው «ሰው ለሚለምን ሰው ሳንቲም ሲሰጥ የሚፀድቅ ይመስለዋል፤ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ይህን ማድረግ የሚሰሩ እጆችን፣ የሚያስብ አዕምሮን ማኮላሸት እንጂ ጽድቅ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጡ ተግባሮች ላይ ለመተባበር ብንተጋ ያ ነው ፅድቅ ማለት» ካሉ በኋላ ከዚህ በኋላ መያዶች፣ ኤጀንሲዎች፣ የሚመለከተው የመንግስት አካልና ሕብረተሰቡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ታሪካችንን እናድስ፡፡» ያሉ ሲሆን ዝነኛው አርቲስት ቴዲ አፍሮም ወገኖቼ አይዟችሁ ከአሁን በኋላ ብዙ አንወድቅም እንለወጣለን ብሏል፡፡

## ቃለምለልሶች

# «መድረክን ለመመስረት አንድነት አላማውን መለወጥ፣ ስነስርአቱን መሻር የለበትም፡፡»

ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም

መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ጽ/ቤት ውስጥና ከቅጥር ግቢው ውጭ ሁለት የተለያየ ጽንፍ ያላቸው ሁነቶች እየተከናወኑ ነበር፡፡ የመጀመሪያው አንድነት ፓርቲ አባል የሆነበት መድረክ የመስራች ጉባኤ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ «መርህ ይከበር» የሚለውና ከአንድነት የተሰረዘው አካል «መድረክ መታገያ እንጂ መደበቂያ አይሆንም!» በሚል ያሰማ የነበረው ተቃውሞ ነው፡፡ ባልደረባችን ዳዊት ከበደ ከተቃውሞ አቅራቢዎች መካከል አንዱ ከሆኑት ከፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም ጋር ቀጥሎ ያለውን ቃለ ምልልስ አድርጓል፡፡

*በስምንት ፓርቲዎችና በሁለት ግለሰቦች እንደተመሰረተ የሚነገርለት መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ ዛሬ (ቃለምልልሱ የተከናወነው ባለፈው ቅዳሜ ነው) በይፋ ተመስርቷል በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?*

እኔ መድረክ በሚባለው ድርጅት መመስረት ተቃውሞ የለኝም:: ምክንያቱም ጠቃሚም አስፈላጊም በመሆኑ መልካም ነው:: የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ አንድ መድረክ መጥተውና ተሰባስበው መመካከራቸው ለውጥ የሚያመጣም ይመስለኛል:: ነገር ግን የእኛ ችግር ያለው አንድነትን በመመረዙ ላይ ነው:: መድረክን ለመመስረት አንድነት አላማውን መለወጥ፣ ስነ-ስርዓቱን መሻር የለበትም አይገባውምም:: አላማውን ይዞ ደንቦቹን ጠብቆ በዛ የሚሄድና ከመድረክ ጋር የሚተባበር ቢሆን በግለሰብ ላይ የተመሰረተ መብትና የፖለቲካ ተሳትፎም ነው:: አሁን ግን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚለውን ያንኑ የኢህአዴግ ፈሊጥ ከያዘው መድረክ ጋር ይህንኑ ተቀበለ::

በመሬት ጉዳይ አንድነት ያለው ሀሳብ ፈጽሞ የተለዬ ነው:: እነዚህ ደግሞ የመጠቀም መብት አይነት ብቻ እንዳለው ይስመስላል:: ግልጽም አይደለም:: የመንግስት አወቃቀር የአንድነት የፕሬዚዳንታዊ ስርዓት እንዲሆን ይፈልጋል:: እነዚህ አሁን ያለው ስርዓት እንዲቀጥል ይፈልጋሉ:: ይህን ስንመለከት አላማዎች ተለውጠዋል ማለት ነው:: ጠቅላላ ጉባኤ ሳይፈቅድ አላማዎቹ ያውም አንኳር አንኳር የሆነት አላማዎችም መለወጥ ትክክል አይደለም:: ሁለተኛው ደግሞ ይህ የተደረገበት ሥርዓት የአንድነትን ደንብ ሁሉ የሚጥስ ነው:: ይህም ትክክልም ተገቢም አይደለም:: በአምባገነንነት የተፈፀመ ተግባር ነው:: ዋናውና ትልቁ ተቃውሞአችን በዚህ ምክንያት ነው እንጂ መድረክ በመመስረቱ ተቃውሞ የለንም::

*እንግዲህ ዝግጅቱ በሚደረግበት ጊዜ እናንተም በጽ/ቤቱ አካባቢ የተቃውሞ ድምጾችን እያሰማችሁ ነበር:: ለጥያቄያችሁ የተሰጠ ምላሽ አለ?*

እሱማ ሰውየው «ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢሉት ማንን ወንድ ብላ» ያለው ነገር ነው:: ጭራሽ ከመጤፍም አልቆጠሩንም:: እንደውም አንዳንዶቹ የእኛ ሰዎች ሲወጡም አይተናቸው ነበር ግን ዝም ብለው እየገረመሙን ነው ያለፉት:: ከመኪናው ወርዶ ሰላም ያለን አቶ ስዬ ብቻ ነው::

*እኛ በዝግጅቱ ላይ የእናንተን ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄ አቅርበን ነበር:: የተሰጠው ምላሽ ደግሞ አንዱ የዴሞክራሲ መገለጫ ነው የሚል ነው:: እናንተስ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?*

ምኑ ነው የዴሞክራሲ መገለጫ?

*እናንተ ከቅጥር ግቢ ውጭ የተቃውሞ ድምጽ በምታሰሙበት ጊዜ በመፈክር ባነሳቻኋቸው ነጥቦች ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡን ለኢ/ር ግዛቸው ጥያቄ አቅርበን ነበር ለዚህ የተሰጠን ምላሽ ደግሞ «ተቃውሞዎች መቅረብ ይችላሉ ግን ያ የዴሞክራሲ አንዱ መገለጫ ነው» የሚል ነው*

ኢ/ር ግዛቸው እንዲህ አይነት የጮሌ መልስ ቢሰጥ አይደንቀኝም:: ሌሎች ሰዎች አሉ ከ141 በላይ የሆኑ እነዚህ ሰዎች ተሰባስበውና ፈርመው ሁለቱን ቡድኖች እናናግራችሁ እና እኛ ባለንበት በጉዳዮ ላይ ተወያዩ የሚል ሀሳብ አቀረቡ:: እነዚህን ሰዎች ነገ ዛሬ እያሉ ካቆዩአቸው በኋላ «የአንድነት አባሎች አይደሉም ኢህአዴጎች ናቸው» ተባልን (ይህን ያለው ኢ/ር ግዛቸው ነው ተብሏል እያጣራን ነው):: እንግዲህ ጉዳዩ ታይቶ እኛ መስራች አባላት ነን ምርጫ ቦርድ የሄደው ሰዎችን የፈረምንበት ይታይ:: አባሎች ለመሆናችን ምስክር ነው:: ግን እንዲህ አይነት ሰው ላይ አንድ ነገር መለጠፍ ያው የተለመደ ነው:: አሁን ደግሞ ይሄ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው ይላሉ:: ዴሞክሪሲያዊ ስርዓት እኮ- ተወው ይቃወም ወይ ይጬህ ማለት አይደለም ኑ እንነጋገር እንወያይ ብሎ ማስተናገድ መቻል ነው:: እነዚህ ራሳቸውን ብዙሀን ብለው የሚጠሩትና ሲጮሁ የነበሩት «በቅድሚያ ከአባሎቻችሁ ጋር መነጋገር መቻል አለባችሁ» እያሉ ነበር ሲጮሁ የነበሩት:: ይህንን ማድረግ ሳይችል ምኑ ነው ዲሞክራሲያዊ? እነሱ በጉልበት ደፍጥጠው ስለሄዱና እኛ በሩ ላይ ቆመን ስለጮህን ይሄ ነው ዲሞክራሲ? ይሄንንም ሊነፍጉን አስበው ከሆነ ይሄ ሌላ ነገር ነው:: እንደውም ሁለት ሰዎች (አንድ ፖሊስና አንድ ሴኩሪቲ) መጡና ምን እንርዳችሁ አሉን:: አይ አሁን አዲስ ጡንቸኛ መጥቶብን ነው እና ልትረዱን የምትችሉ አይመስለንም አልናቸው:: እነዚህ ጡንቸኞች እኮ ጠብመንጃና እስር ቤት የላቸውም እንጂ ይከቱን ነበር:: እንግዲህ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ትልቁ አላማ የተለያየውን መገጣጠምና ማስተባበር ነው:: እነሱ እኮ የያዙት በሃሳብ የተያየን ሰው ማስወጣት ነው:: ግዛቸው ይህን ዴሞክራሲ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ ስለዴሞክራሲ እንደገና ራሱን መጠየቅ አለበት::

*ወደ ሽማግሌዎቹ ልምጣና ሽማግሌዎቹ እናንተን ለማስማማት ጥረት ሲያደርጉ ነበር ነገር ግን ሰሞኑን ሲገለፁ የነበሩት ነገሮች ሁለቱም ወገኖች ፈቃደኞች ከሆኑ በኋላ በስራ አስፈፃሚዎች በኩል የትብብር ነገር አይታይም የሚል ነው:: የእኛ አገር ሽምግልና ደግሞ አንተም ተው አንተም ተው አይነት ነገር ነው መሆን ያለበት:: አንዳንድ አስተየየት ሰጪዎች ደግሞ ለሽምግልና የመጡት ሰዎች ትንሽ ለእናንተ የመወገን አዝማሚያ እንዳለቸው እየገለፁ ይገኛሉ:: ይህን የሚሉበት ምክንያት ልክ እናንተ ያንን ስብሰባ ስታወግዙ ሽማግሌዎቹም በራሳቸው መንገድ ያንን ወገን የማውገዝ ተቃውሞ ሰልፍ ነበር ያደርጉ የነበረው:: ይህን እንዴት ያዩታል?*

በእውነቱ ለሰዎቹ ትክክለኛ ግምት ለመስጠት ጉዳዮን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሰዎቹ ተሰባሰቡና በፊርማቸው አረጋግጠው አንድ ደብዳቤ ለእነሱም ለእኛም ኮፒ ፃፉልን እኛም ወዲያውኑ ደስ ይለናል የሚል ምላሽ ፃፍን፡፡ እንደውም ይህን በማድረጋችሁ ትልቅ ስራ ነው የሰራችሁት እናመሰግናለን፡፡ በበኩላችን እናንተ ሲመቻችሁና ስትዘጋጁ በፈለጋችሁበት ቦታ ቀርበን በፊታችሁ ለመነጋገር ዝግጁ ነን ብለን ወዲያው መልስ ሰጠን፡፡ በነዚያ በኩል ግን ቆይ ስብሰባ ተደርጐ ከስራ አስፈፃሚው ጋር ተነጋግረንና ተወያይተ ነው የሚሆነው አለ፡፡ ከስራ አስፈፃሚው ጋር ከተገኙ በኋላ ደግሞ የለም ቆይ ምክር ቤቱ ተሰብስቦ ከወሰነ በኋላ አሉአቸው፡፡ መጨረሻ ላይ እንደውም እናንተ ብዙዎቻችሁ  ኢህአዴግ ናችሁ የሚል ነገር መጣና የሰዎቹን በጐ ፈቃድ አበላሹት ሰዎቹም ተናደዱ፡፡ ከነዚህ ሽምጋዮች ጋር ደብዳቤ ከመለዋወጥ በስተቀር ምንም ግንኙነት የለንም፡፡ ዛሬም ቢሆን ያየ ሰው አይቷል፡፡ እኛ ለብቻችን እነሱም ለብቻቸው ነበሩ፡፡ እኛ እነሱ ይመጣሉ ብለን ሳንገምት በራሳችን ተቃውሞአችንን ለማሰማት ነው የሄድነው፡፡ ከዚህ ውጭ  በእውነት ነው የምልህ ምንም አይነት ግንኙነት የለንም፡፡ ግን ከእኛ በተቃራኒ ያሉት ወገኖች እነዚህን ሰዎች በጣም አናደዷቸውና ቁጥራቸው ጨመረ፡፡ ዛሬ የመጡት ቁጥር  እንዳይበዛና ረብሻ እንዳይፈጠር ሲባል ተወካዮቹ ብቻ ናቸው፡፡ ለእናንተ ወግነዋል የሚባለው ነገር የተነሳው ምናልባት እኛ አዎንታዊ ምላሽና ተቀባይ ሆንንላቸው እነዛ በፍፁም አንቀበልም አሉ፡፡ ይሄ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ እነሱ ለእኛ በጐ አመለካከት ቢኖራቸው በእኛ በጐ ምላሽ ላይ የተመሰረተ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

***ተቃውሞ በምታሰሙበት ጊዜ «አንድነትን በመግደል ወ/ሪት ብርቱካንን መግደል አይቻልም» የሚልና «መድረክ መታገያ እንጂ መደበቂያ አይደለም» የሚሉ መፈክሮችን አንግባችሁ ነበር ምን አይነት መልእክት ለማስተላለፍ ነው?***

ይህን ጉዳይ አቶ አስራት ለአንድ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ ግልጽ አድርጐታል፡፡ ብርቱካን ለምርጫው በተለይ አትነሳም፡፡ ብዙ የፖለቲካ እስረኞች አሉ እሷ አንድ የፖለቲካ እስረኛ ሆና በእነዛ ውስጥ ትካተታለች ነው ያለው፡፡ እንግዲህ ተመልከት ይህ የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሀፊ ነው ይሄንን የሚለው ዛሬ የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሀፊ ነው፡፡ የመረጥነውም እኛው ነን፡፡ አሁን ይህ ሰው ምን ማለቱ ነው በቃ በእርሱ አዕምሮ ውስጥ አንድነት ተበርዟል የተበረዘው ደግሞ መድረክ ውስጥ ገብቶ ነው፡፡ ስለዚህ መድረክ ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች ሁሉ የፖለቲካ እስረኞች አሏቸው ስለዚህ ብርቱካን ከእነዛ እስረኞች አንዷ ነች፡፡ የተለየ ነገር የለም፡፡ አንድነት መድረክን ይዞና ተበርዞ ከተነሳ መደምደሚያው ይኸው ነው፡፡ ነገር ግን ሳልተበረዘ አንድነት ሰዎች እንደሚያምኑት ዝም አንልም፡፡ ብርቱካን የአንድነት ሊቀመንበር ነች፡፡ መሪያችን ነች፡፡ ስለዚህ እሷን ከሌሎች ሰዎች ጋር አናያትም፡፡ በመሪነቷ፣ በእናትነቷና በመስራችነቷ ለብቻዋ ነው የምንመለከታት እና እርሷን እስር ቤት አስገብተን ምርጫ ሊኖር አይችልም

የሚል አስተሳሰብ እና አቋም ነው ያለን። በሌላ በኩል ደግሞ የሚደንቅ ነገር አለ። ግዛቸው ተጠባባቂው ሊቀመንበር እሱም ብርቱካን እስር ቤት ሆና ምርጫ የሚባል ነገር አይታሰብም ሲል እኔ በጆሮዬ ሰምቼዋለሁ። ነገር ግን አስራት እና ሌሎች ደግሞ ይህንን ለውጠው በጭራሽ እሷ እዚህ ውስጥ አትገባም ከሌሎች ጋር መታየት አለባት ይላሉ። እንግዲህ ተመልከት እነዚህ ሰዎች አንዱ ስለአንድ ነው የሚያሰበው እነዛኞቹ ደግሞ በመድረክ መንፈስ ነው የሚያስቡት። እና ራሳቸው በውስጣቸው በሰከነ አዕምሮ አስበውና ተነጋግረው የወሰኑት እንዳልሆነ በሚናገሩት የተለያዩ ነገር ማወቅ ይቻላል። ይሄ ራሱ ስዎቹ እንደተደናበሩና አስተሳሰባቸው ግራ እንደተጋባ የሚያሳይ ነው። እንግዲህ በአንድነትና በዝም አንልም በኩል ስታየው ብርቱካን የእኛ መሪ ነች አንድ ነች፣ እርሷን ከሌሎች ጋር ደምረን አናይም። ያም ሆኖ ለሌሎች የፖለቲካ እስረኞችም እንጮሀለን። ግን እሷን ከሌሎች ጋር ደምረን አናይም ከሌሎች ጋር አንበርዛትም። ይሄ ነው የእኛ አቋም ለማለት ነው እነዛን መፈክሮች ያሰማነው።

*ሰሞኑን የሰሜን አሜሪካ አንድነት ድጋፍ አሰባሳቢ አንድ መግለጫ አውጥቶ ነበር። ደብዳቤው ደርሷችኋል ወይ? ከደረሳችሁስ እንዴት ነው የምትመለከቱት?*

አዎ ደብዳቤው ተጽፏል።። በጣም የሚያሳዝን ነው። በእርግጥ መልስ ሰጥተንበታል ግን በቂ አይመስለኝም። በቂ የሚሆን መልስ እኔ እያዘጋጀሁ ነው። በመጀመሪያ የተሳሳተ የፖለቲካ አስተሳሰብ አለ። እንደሚመስለኝ አሜሪካም አገር ሆነው ያ የኢትዮጵያዊነት ባህል አይለቅም። 20 እና 30 አመት እዛ ቆይተው ያ በሽፍንፍን፣ በማድበስበስና በሴራ እንዲሰራ ይፈልጋሉ። ይህ ውጭ የሚወጣውና ትክክለኛው ፖለቲካ እውነቱን ይዞ ለህዝብና ለህዝብ የታወቀ ሆኖ እንዲጓዝ አይፈልጉም።

ፖለቲካ የህዝብ ነው ካልን ደግሞ እየንዳንዱ ፖለቲከኛ በህዝብ የሚመዘን መሆን አለበት። እኛ በዚህ እምነት ነው የወጣነው። የምንፈልገውም አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ነው። እንደው አንድ ገዢ ፓርቲ ላይ ለመውቀስ መረባረብ ብቻ ሳይሆን እኛስ እርስ በርሳችን ያው አመለካከት ሊለቀን አይገባም ወይ? እዚህ አጠገባችን ያለውስ ሲሳሳት ተሳሳትክ ለምን አንለውም? ነገ በለስ ቀንቶት አንዱ ፓርቲ (እግዜር አያድርገው ማለት ይቃጣኛል) ስልጣን ቢጨብጥ ከኢህአዴግ በምንም አይሻልም። አሁን አንድነትን ብትወስድ በምንም መንገድ አይሻልም። ስለዚህ ይህን ለህዝብ አውጥተን በማሳወቅ ሰዎቹን እንዲላክና እንዲመዘን ማድረግ መቻል እውነተኛው ፖለቲካ ነው።

እንግዲህ አሜሪካ ውስጥ ተቀምጦ የዴሞክራቲክ ፓርቲ ሰዎች በኦባማ የጤና ፖሊሲ አመራር ላይስንት የዴሞክራቲክ ፓርቲ ሰዎች እንደተቃወሙት በገንዘቡ ውጥረት ጊዜ የድጐማውን ስንት የዴሞክራቲክ ፓርቲ ሰዎች እንደተቃወሙት አያውቁም? ለመሆኑ ጋዜጣ ያነባሉ? ለመሆኑ ቴሌቪዥንስ ያያሉ? እዛው አሜሪካ ውስጥ የሚደረገውን ያውቃሉ?

እውነትን ትክክለኛ ህጋዊ ስርዓትን ለኢትዮጵያ ህዝብ እናመጣለን ብለናል። ይህን ነገር ደግሞ እዚሁ እኛ ፓርቲ ውስጥ መጀመር አለብን። ግልጽነትና ተጠያቂነት ከእኛ መጀመር አለበት ብለን እናምናለን። ኢህአዴግ ጋር ከመሄዳችን በፊት እኛው ልናዳብረው ይገባል። እኛ እርስ በእርሳችን በሽፍንፍንና በድብብቆሽ እየሰራን ኢህአዴግን ግልጽነትና ተጠያቂነት አምጣ ማለት ተገቢ አይመስለኝም። እና ይህን ደብዳቤ ከፃፉት መካከል እጅግ የማከብራቸው ሰዎች አሉበት። በእርግጥ እነሱ ይፃፉት አይፃፉት እርግጠኛ አይደለሁም። ነገር ግን በጣም የሚያሳዝንና ትክክል ያልሆነ ደብዳቤ ነው። ደብዳቤው ትንሽ ወደብልግናም ይሄዳል። በተጨማሪም አሜሪካን ሰማይ አድርገው እኛን አቆልቁለው ሲመለከቱን ትክክል አይደለም። እኛ ሁኔታው ውስጥ ስላለንበት ያንን ሁኔታ እንመለከታለን። ደግሞ ለእኛ ትንሽ ግምት ቢሰጡንና እንደ እኛም ባይሆን ትንሽም ያስባሉ ብለው ግምትና ቦታ ሊሰጡን ይገባል እንጂ እንደዚህ በኩርኩም ለመምታት መቃጣት ተገቢ አይደለም። አንዳንዶቹ ስም እንዲጠቀስ አይፈልጉም ለምንድን ነው ስም የማይጠራው ፈረንጆች እኮ የአንዳንዶቹን ፖለቲከኞች መኝታ ቤት እስከመግባትና የሚሰራውን እስከማየት ይደርሳሉ። በየሆቴሉም ያወራሉ እኛ እዛ ባንደርስ እንኳን በአስተሳሰቡና በስልጣን አጠቃቀሙ በፓርቲ ገንዘብ አያያዙ ያለውን ሁኔታ አንዳች አንናገርም እንዴት አናውራም። ይህንን ለህዝብ መግለፃችሁ ትክክል አይደለም የሚል ሰው በእኔ እምነት ፖለቲካ ምን ማለት እነሆነ አያውቅም። እርግጥ በስም ጠርቶ እከሌ እንዲህ ነው እንዲህ አደረገ ማለት በኢትዮጵያ ባህላዊ አሰራር ነውር ይመስለል። አንድ ሰው ግን ፖለቲካ ውስጥ ሲገባ ለመጋለጥ ነውና ምን የስፈራዋል። ከአሁን በኋላ የኢትዮጵያ ፓለቲካ በሽፍንፍን የሚሄድ አይመስለኝም መሆንም የለበትም። ግልጽና ሁሉም ሰው ተጠያቂ የሚሆንበት ፖለቲካ ማካሄድ ያስፈልገናል። ይህን ሁሉ ነገር አሜሪካ እየኖሩ አለመረዳታቸው ግን ይበልጥ ያሳዝነኛል።

***ከዚህ ጉዳይ ወጣ ያለች አንድ ጥያቄ አለችኝ። ሰሞኑን በሀገራችን የባንዲራ ቀን ተከብሯል በዚህ ዙሪያ የሚሉት ነገር ካለ?***

እኔ የሰንደቅ አላማ ቀን እንደ ንስሃ አድርጌ ነው የምወስደው። አንድ ጊዜ ጨርቅ ብየዋለሁና ለዛ ለጨርቅ ከብር ልሰጠው የሚል ልዩ አይነት ንስሀ። አቶ መለስ ያኔ ጨርቅ ነው ያለ ጊዜ አንድ ነገር በጋዜጣ ላይ ጽፌ ነበር። ምንድን ነው ያልኩት «እውነቱን ነው ጨርቅ ነው ሰንደቅ አላማው ጨርቅ ላይ ሊሆን ይችላል ግን ጨርቅ ላይ ብቻ አይደለም፤ ሰንደቅ አላማ የሚባለውም ጨርቁ አይደለም። ስንትና ስንት ዕልፍ አዕላፍ ህዝብ መስዋዕት የሆነበት ምልክት ነው። እና አንድ የሶስት ዓመት ልጅ ይሄ ሰንደቅ አላማ ጨርቅ ነው ቢል አያውቅምና አያስደንቀኝም። ምክንያቱም ህፃኑ ትክክል ነው ጨርቅ ነው። ግን ያ ልጅ ሲያድግና ሰባት አመት ሲሞላው ይሄ ምንድን ነው ሲለው ሰንደቅ አላማ ነው እንደሚል ጥርጥር የለኝም። ግን አቶ መለሰ እዛ ደረጃ ላይ አልደረሰ እንደሆነ አላውቅም?» ብዬ ነበር የፃፍኩት።

ሰንደቅ አላማው ጨርቅ ላይ ብቻ አይደለም የሚሆነው:: ፕላስቲክ ላይ፣ እንጨት ላይ ብረት ላይ ሊሆን ይችላል ግድግዳ ላይም ሊሆን ይችላል:: ግን ምልክትነቱ ትርጉም አለው ያንንም ነው ሰንደቅ አላማ የምንለው እንጂ፣ ይሄ ብረት ነው፣ ይሄ ብር ነው ወይም ይሄ ወርቅ ነው አይደለም ቁም ነገሩ መስቀል ከምንም ይሰራ የክርስቶስ መስዋዕትነት ምልክት ነው:: አሁን የሰንደቅ አላማ ቀን መምጣቱ ጥሩ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግር የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ ህዝብ አንድ ነገር ይዞ የሚሄድ ሳይሆን አንድ ባለጡንቻ በመጣ ቁጥር ብሄራዊ መዝሙሩ ይለወጣል ሰንደቅ አላማው ይለወጣል:: ቢያንስ እዛ ላይ ያለው አርማ ይለወጣል:: እና «ይሄንን አሁን ያለው አርማ ወደፊት እንዳይለወጥ በአይናችሁ ልመዱት» ለማለት ከሆነ አልገባኝም:: ለእኔ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ መሠረቱ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ነው:: ላዩ ላይ የሚለጥፉት አንበሳ ሆነ፣ ኮከብ ሆነ ሌላ ነገር በሰንደቅ አላማው ላይ አንዳች የሚያመጣው ለውጥ የለም:: የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያወቀው፣ በውስጡ የቀረፀውና ህሊናው የተቀበለው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀስተ ደመና (የማሪያም መቀነት) ነው:: እንግዲህ ቅድም እንዳልኩህ ንስሀ ነው የሚመስለኝ:: በእውነት ንስሀ ለመግባት ለፈለገ ሰው ደግሞ ንስሐ የሚገባባቸው የተሻሉ ነገሮች አሉ አይደለም እንዴ? እንድንተማመን፣ እንድንቀራረብና እንድንነጋገር ከተፈለገ ከዚህ የተሻሉ ብዙ ነገሮች አሉ:: በዚህ ላይ ጥሩ ወኔ አሳይቷል:: ጥርጥር የለውም:: ይህ አይነት ወኔ በሌላውም ላይ ቢታይ በጣም ጥሩ ነው ከጥፋትም እንድናለን::

# «የስልጣን ጥምና መጠላለፍ የትብብር መድረኮችን ሲያከስም ኖሯል»

*ዶ/ር መረራ ጉዲና*

ላለፉት 18 ወራት ያህል ከተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች በመውጣጣት የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም ሲያዘጋጅ የቆየው «መድረክ» ከ60 በላይ የሚሆኑ ስብሰባዎችን ካደረገ በኋላ ባለፈው ቅዳሜ «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ» በሚል ስያሜ መስራች ጉባኤውን አካሂዷል:: ከሶማሊያ እስከ ትግራይ የተደራጁ ኃይሎች የተሰባሰቡበት መሆኑን መስራቾቹ የገለፁለት መድረክ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ሊቀ መንበር የሆኑትን ዶ/ር መረራ ጉዲናን ለቀጣዮቹ አራት ወራት ሊቀ መንበር አድርጎ ሰይሟል:: መድረኩን እስካሁን እየታዩ ከከሰሙት የፖለቲካ ፓርቲ ህብረቶች የተለየ የሚያደርገው ምን አዲስ ነገር ይዞ መጥቷል? የአባል ፓርቲዎቹ የፖለቲካ ፕሮግራም አሁን የተፈጠረው መድረክ ከቀረፀው መለስተኛ የፖሊሲ ሰነድ ጋር ተሰናሳይነቱ ምን

ያህል ነው? በሚሉትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ባልደረባችን ውብሸት ታዬ የወቅቱ የመድረኩ ሊቀ መንበር ከሆኑት ከዶ/ር መረራ ጉዲና ጋር ቆይታ አድርጓል።

***የአገራችን የተቃውሞ ፖለቲካ ትግል ከ1960ዎቹ መባቻ ጀምሮ የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችንና ርዕዮተ ዓለሞችን በማንገብ ሲካሄድ ቢቆይም ጠንካራ ህብረት ተፈጥሮ ስኬት ላይ የተደረሰበት ሁኔታ አልታየም። ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ብቻ እንኳ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በርካታ የተቃውሞ ህብረቶች ቢመሰረቱም ከአንድ ወቅት ግርግር አልፈው ለውጤት አልበቁም። የፖለቲካ ሳይንስ ባለሙያ እንደመሆንዎ ጭምር ምክንያቱ ምንድነው ይላሉ?***

የተቃውሞ ፖለቲካ ህብረቶች ለምን ለስኬት አልበቁም? ለምን ይከፋፈላሉ? ስንል ምክንያቱ ከአይዲዮሎጂ (ጽንሰ ሃሳብ) ልዩነት የራቀ ሆኖ እናገኘዋለን። የስልጣን ትግል ነው። የኢህአፓና የመኢሶንን የውዝግብ መንስኤ እንደምሳሌነት ማየት ይቻላል። ሁለቱም የሶሻሊዝም ርዕዮተ-ዓለም አራማጆች ነበሩ።-ከኢዲዩ በስተቀር። የትግሉ ማዕከል ግን ስልጣንን ትኩረት ያደረገ ነበር። እንዲህ እያለ ነው እንግዲህ እስከ 1983 ዓ.ም የቆየው። በታሪክ አጋጣሚ ምኒልክ ቤተ - መንግስት ለመግባት የቻሉትም የዚሁ የኋልዮሽ ጉዞ አካል ነው የሆኑት። ሰፊ ሕዝባዊ አጀንዳ ከመያዝ ይልቅ ስልጣንን ጨምድዶ ለመያዝ የሚረዳ አካሄድ ነው የተከተሉት። ጎድቶናል።

***ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚቀርበው ትችት ደግሞ አብዛኞቹ የፖለቲካው ተዋናዮች መሰረታዊ የፖለቲካ ሳይንስ እውቀት ሳይኖራቸው በአገር ፍቅር ስሜት ወደ ጐራው መቀላቀላቸውና ሌሎቹ ደግሞ ትግሉን ለቁሳዊ እሩት ማካበቻ ማዋላቸው ነው ይባላል። ይስማሙበታል?***

እስማማበታለሁ። ፖለቲካ ራሱን የቻለና አላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ስሌት ያለው ሳይንስ ነው። የምትደምረው የምትቀንሰው ነገር አለ። የምትጓዝበት መንገድ የት እንደሚያደርስህ ሳታውቅ በስሜት የምትመራው አይደለም። ሌላው ይህ ብዥታ የሚፈጥረው ስነ-ልቦናና መጠላለፍ ነው። ሰፊ የመጠላለፍ ፖለቲካ ታሪክ አለን። «መሰረታዊ የፖለቲካ ሳይንስ እውቀት ሳይኖራቸው» ያልካቸው ፖለቲከኞች ሲጠልፉ ይህ ተግባራቸው በእኔስ ላይ ምን ያስከትላል? የምወረውረው ድንጋይ እኔ ላይ ላለመመለሱ ዋስትናው ምንድነው? ልዩነት ቢኖርም አገራዊ አጀንዳዎችን በጋራ ማራመድ አንችልም ወይ? ብለው አይጠይቁም። ወይም አንድ የፓርቲ መሪ የተለየ ሃሳብ ካነሳ የዓለም መጨረሻ የደረሰ የሚመስላቸው አሉ።

**ቀደም ሲል እንደተነሳው በተለያዩ ጊዜያት ተፈጥረው የከሰሙ ቁጥራቸው ከፍ ወይ ዝቅ የሚል የተቃዋሚ ፓርቲ ህብረቶች ነበሩ፡፡ አሁን በተመሰረተው መረድክ ውስጥ ያላችሁ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የስብስቡ አካል የነበራችሁበት ሁኔታ ይታወቃልና አንድ ሆናችሁ ጀምራችሁ «ተባበርን» ባላችሁ ማግስት «ተሰባብራችሁ» የምትገኙበት መሰረታዊ ምክንያቶች ምን ነበሩ?**

*በተወሰነ መልኩ ቀደም ሲል ለመጥቀስ የሞከርኩት ነው፡፡ አራት ነጥቦች በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ የመጀመርያው ከአገራዊ አጀንዳ ይልቅ በአንድ ጀምበር ስልጣን ለማግኘት መመኘትና ይህን ለማሳካት በተሳሳተ ስሌት የሚደረግ መጠላለፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ሌኒን «የሞኝ ሩጫ ፍጥነት አይጨምርም» ሲል የገለፀው አይነት የጠራ የፖለቲካ ፕሮግራምና አቅጣጫ ሳይኖር መኳተን ነው፡፡ ሶስተኛው የኢትዮጵያ ገዥዎች ባላቸው አቅም ሁሉ ዴሞክራሲንና የተቃዋሚዎቻቸውን ትግል ለማጨናገፍ የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ በመጨረሻ ባህላችን ራሱ ለክፍት ፖለቲካ አመቺ ያለመሆኑ ነው፡፡...*

**«ክፍት ፖለቲካ» የሚለውን በሌላ አገላለጽ እንዴት ያስቀምጡታል?**

*የውይይትና ድርድር መርሆዎችን፣ ሰጥቶ የመቀበል ፖለቲካንና የመሳሰሉት ማዕቀፍ ያደረገ ማለት ነው፡፡*

**እስካሁን ካነሳናቸው የተቃውሞ ፖለቲካ ህብረቶች ህፀፅ ሚዛን በመነሳት መድረኩ ከዚህ አደጋ ያመልጣል ለማለት የሚያስችለው መከራከሪያ ምንድነው?**

*መድረኩ መስራች ጉባኤውን ለማካሄድ አንድ ዓመት ከግማሽ ወስዶበታል፡፡ ይህን ያህል ጊዜ የፈጀነው ከዚህ ቀደም የነበሩት የትብብር መድረኮች ያጋጠሟቸው መከፋፈሎች እንዳይደገሙ በሚል ሰፊ ጥናት በማካሄድ ነው፡፡ ሲከፋፍሉን የነበሩት ነገሮች ምንድናቸው? ብለናል፡፡ ሌላው አብዛኞቹ አባላት በትግሉ ረዥም ጊዜ ያሳለፉ ናቸው፡፡ ድክመታችንና ጥንካሬያችንን ገምግመናል፡፡ የብሔር ስብጥሮችን ያየን እንደሆነ ደግሞ ከሶማሊ እስከትግራይ መዋቅሩ ተዘርግቷል፡፡ በተሻለ አደረጃጀት ነው መድረክ የተመሰረተው፡፡*

**የመድረክን መለስተኛ ፕሮግራምና የአብዛኞቹን አባል ፓርቲዎቹን ማኒፌስቶ ለማንበብ ሞክሬያለሁ፡፡ የሁለቱ ጽንፍ ማኒፌስቶዎች ሲገናዘቡ መሰረታዊ በሚባሉ አጀንዳዎች ላይ ተመሳሳይ አቋም የሚያራምዱ አይደሉም፡፡ በሌላ አባባል ቅንጅት ለመፍጠር የማያስችል ክፍተት ያላቸው ይመስላል፡፡ የዜጎች ነፃነት መብት አጠባበቅ መርህ፣ የመሬት ስሪት የመንግስት አወቃቀርና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ምን ምላሽ አለዎት?**

ይህ እንግዲህ መለስተኛ ፕሮግራም ነው፡፡ በሚያስማሙ ነጥቦች ላይ በጋራ ለመስራት ከዚያ በተረፈ የየፓርቲያችንን ልዩነት አክብረን መቀጠል ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ መሰረታዊ በሚባሉ አጀንዳዎች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት በአገራችን እንዲኖር፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በህዝብ ድምጽ እንዲፈጠር እንዲሁም ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማምጣት ተስማምተናል፡፡ እነዚህ ሶስት ነጥቦች መሰረታዊያን ናቸው፡፡

**በመድረኩ አባል ድርጅቶች መካከል ያለው ልዩነትና መድረኩ ከኢህአዴግ ጋር ያለው ልዩነት ይመሳሰላሉ ይባላል፡፡ ይህ ደግሞ በምርጫ አሸንፋችሁ ስልጣን ብትይዙም የእርስ በርስ ውዝግብ ውስጥ ሊከታችሁ ይችላል፡፡ ስለዚህ ትግሉን ለስልጣን የሚደረግ ብቻ አያስመስለውም?**

በመጀመርያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በትክክል ተፈጠረ ማለት ልዩነት ይጠፋል ማለት አይደለም፡፡ ዋናው ነገር ቅድም የጠቀስኳቸው ሶስት ነጥቦች መተግበራቸው ነው፡፡ ያገኘ ናቸውን ድሎች ይዘን በቀጣይ ሁነቶች ላይ ወደ ህዝቡ እንሄዳለን፡፡

**ኢህአዴግም ፌዴራላዊ የመንግስት አደረጃጀትን ይከተላል፡፡ እናንተም «ፌዴራላዊ» አደረጃጀትን የሚከተል መድረክ መስርታችኋል፡፡ ልዩነታችሁ ምንድነው?**

ልዩነቱ የኢህአዴግ ፌዴራሊዝም ዴሞክራሲ አልባ መሆኑ ነው፡፡ የዩጎዝላቪያ ፌዴራሊዝም አገሪቱን የበታተነውም በዴሞክራሲ አልባነቱ ነበር፡፡

**ከዴሞክራሲያዊ አሰራሮች አንዱ ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃ እንዲገልፁ ማስቻልና ለጥያቄዎቻቸውም ተገቢ ምላሽ መስጠት መሆኑ ይታወቃል፡፡ መድረኩ በአንድነት ጽ/ቤት ምስረታውን እያከናወነ በነበረበት ወቅት ከፓርቲው የተሰረዙ መስራች አባላት ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ቢውሉም ምንም ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ገልፀውልናል፡፡ በሊቀ መንበርነት የሚመሩት ድርጅት አባል ፓርቲ ይህን በመፈፀሙ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?**

ይህ በቀጥታ የሚመለከተው አንድነትን ነው፡፡ በዕለቱ ሃያ እና ሰላሳ ሰዎች ተሰልፈው ተቃውሟቸውን እያሰሙ ነበር፡፡ አዛውንቱም /ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያምን ለማለት ነው/ በልጆቹ መሐል ቆመው ነበር፡፡ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ የአገር ጉዳይ ከግለሰብም ከፓርቲም በላይ መሆኑን የተረዱ አልመሰለኝም፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎች ተባብረው አንድ ጥሩ ነገር ለመስራት ሲሞክሩ በልፋታቸው ላይ ውሃ ለመድፋት መጣር ምን

ይባላል? አልገባኝም:: በዚህ አይነት ተቃዋሚዎችን እንጉዳለን ተብሎ ከሆነ ኢህአዴግ ይበቃናል::

**ስምንቱ የመድረክ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ሰባት ተወካዮችን ማለትም 56 ግለሰቦችን ለምስረታው ቢልኩም በአመራር ምርጫው ላይ አንድም እንስት እንድትገባ አልተደረገም:: ይህ ለሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ግምት የሰጣችሁ አያስመስልባችሁም? ረዥም የትግል ጉዞ አድርገናል የምትሉ ፓርቲዎች እንዴት አንድ ሴት እጩ እንኳ ማቅረብ ተሳናችሁ?**

ለዚህ ተጠያቂው ኢህአዴግ ያሰፈነው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርአት ነው:: ኢህአዴግ የፖለቲካ ምህዳሩን በማጥበቡ የተፈጠረው አሉታዊ ስነ ልቦና ነው:: የወ/ሪት ብርቱካንን የእስር ሁኔታ ካየን ለዚህ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል::የታሰረችው ወንጀል ፈጽማ አይደለም:: ብቸኛዋ ሴት የፖለቲካ መሪና በችሎታዋ ለዚህ ደረጃ የበቃች ነበረች:: የእኛ አባል የሆነችውና ከአቶ አባዱላ /የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት/ ጋር ተወዳድራ የነበረችው መምህርትም የደረሰባትን እናውቃለን::አሁን ከአገር ተሰዳለች:: ስለዚህ ጥፋቱ የኛ አይደለም::

**መድረኩን ከመሰረቱት ፓርቲዎች በተጨማሪ በግለሰብ ደረጃ አስተዋጽኦዋቸውን ሲያበረክቱ የቆዩት የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ እና አቶ ስዬ እስካሁን የአንዱም ፓርቲ አባል ለመሆን ያለመፍቀዳቸው ሌሎች ስለስብስቡ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓል ይባላል::....**

ማለት?

**የመድረኩ መመስረት ጠቃሚ ነው ከተባለና በግል ሳይሆን በድርጅት ደረጃ (በጋራ) መታገል ውጤታማ ያደርጋል ከሚል መርህ በመነሳት የግለሰቦቹ ወደየትኛውም ፓርቲ ያለመግባት ልባቸውን የገዛ ወይም ለቁመታቸው የሚመጥን ፓርቲ አጥተው ነው የሚል እመታ ፈጥሯል:: ለአባልነት የጠየቋቸውን አንዳንድ ፓርቲዎች ጥያቄም ውድቅ አድርገዋል::**

ለቁመታችን የሚመጥን ፓርቲ የለም ብለው እንኳ አይመስለኝም:: እንደምገምተውና በአንዳንድ ውይይቶቻችን እንደተረዳሁት ከሆነ ግን ፓርቲዎቹን የማጠናከርና የተለያዩ አስተዋጽኦዎችን ለማበርከት እንዲያስችላቸው የመረጡት ይመስለኛል:: በሌላ በኩል ሁለቱም ግለሰቦች ቀደም ሲል ባሳለፉት የፖለቲካ መድረክ ያጋጠሟቸው ውጣ ውረዶች ይታወቃሉ:: እና ራሳቸው ግምገማ አድርገው አቋም ለመያዝ በቂ ጊዜ አላቸው::

**መድረኩ የህጋዊነት ሰርተፍኬት ለማግኘት ወደ ምርጫ ቦርድ የሚሄደው መቼ ነው?**

በዚህ በሁለት ሶስት ቀን ውስጥ እንሄዳለን፡፡ የምንዘገይበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

**ከኢህአዴግ ጋር ጀምራችሁት የተቋረጠው ድርድርስ?**

እንደሚታወቀው ይህ ድርድር ለጊዜው ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ኢህአዴግ አቋሙን ካስተካከለ ለአገራችን ይጠቅማሉ ብለን ባመንባቸው አጀንዳዎች ላይ ለመደራደር ዝግጁ ነን፡፡ ለሁላችንም የምትሆን ኢትዮጵያን ለመፍጠር የጀመርነውን ትግል ግን ውጤት ላይ እስከምንደርስ እንቀጥልበታለን፡፡

## ኪነ-ጥበብ

# «የፊልም ኢንዱስትሪውን የሚያበረታታ ስትራቴጂ ሊነደፍ ይገባል»

**አቶ ዮናስ ብርሃነ መዋ /የፊልም ዳይሬክተር/**

የአገራችን የፊልም እንቅስቃሴ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እየጐለበተና አዳዲስ አምራቾችን ወደ ኢንዱስትሪው እየጎተተና የተሻሉ ፕሮዳክሽኖችንም/የፊልም ውጤቶች/ እንድናይ እያስቻለ ነው፡፡ የፊልም ዳይሬክተር የሆነው ዮናስ ብርሃነ መዋ የዚህ የፊልማችን ግስጋሴ አጋፋሪና የለውጡ አራማጅ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በአሜሪካን አገር የፊልም ሙያን የተማረው ዮናስ እስከ ዛሬ ስድስት ፊልሞችን በመሥራት ተመልካች ልቦና ውስጥ የራሱን አሻራ ከትቧል፡፡ የራሱን ቀለም እየፈጠረ መምጣቱንም ይናገሩለታል፡፡ የዮናስ የላቀ ስራ እንደሆነ እየተነገረለት ያለውና በቅርቡ በሲኒማ ቤቶች ለዕይታ የበቃው «የታፈነ ፍቅር» የተሰኘው ፊልም ከወዲሁ ተወዳጅ እየሆነ መጥቷል፡፡ እኛም በዚህና በኢትዮጵያ የፊልም እሴት ገጽታ ዙሪያ እንዲያወራን ጋብዘነዋል፡፡
**«የታፈነ ፍቅር» ስንተኛ ፊልምህ ነው?**

ስድስተኛ ፊልሜ ነው፡፡ ይህ ፊልም በተለይ ከባለፉት አራት ስራዎቼ ጋር ሲነፃፀር በካሜራ፣ ላይት፣ ሲኒማቶግራፊ ስራዎች ኤዲቲንግ፣ ድምጽ የምስል ኳሊቲ ላይ ባለፉት ፊልሞቼ ላይ ደከም ያሉትን አሻሽለንበታል፡፡ የታሪክ አመራረጥ ላይም የተለያዩ ታሪኮችን ለማየት የመሞከሬን ያህል በይዘቱ ከሌሎች ወጣ እንዲል አድርገናል

- የፊልሙ ደራሲ ማርታም በጣም ጥሩ ሥራዎችን ወደፊት መስራት የምትችል መሆኗን የሚያመለክት ስራ ነው:: ይሄ ፊልም ሮማንቲክ ድራማ ኳይት የሆነ ሲኒማ ነው - ከሰራኋቸው ውስጥ::በዚህም ተመልካቹ ዘና እንደሚልበት አምናለሁ::

**የፊልሙ ደራሲ የሆነችዋን ማርታ አበበ የትግል ሀይል እንዴት አየኸው? የሴትነት ጥንካሬዋን ማለት ነው...**

እንደ ፕሮዲዩሰርም እንደ ደራሲም ስታያት በጣም ትልቅ ስራ ነው የሰራችው:: የፀሀፊ ስራ ፕሮሰስ ነበረው:: የተሻሉ ነገሮችም ነበሩት:: በዚህ መልኩ ታሽቶ መሰራቱ እንደ ደራሲነቷም እንደ ሴትነት ጥንካሬዋም የሚያስመሰግን ስራ ሰርታለች:: በዚህ አጋጣሚ በርቺ ልትባል ይገባል:: ብዙ  የተለፋበት ስራ ነው::  ከምርቃቱ ብንነሳ ጥሩ ምላሽ ነው ያገኘንበት:: የታሪኩ ይዘት ትንሽ ኳይት መሆንና ወጣ ያለ መሆኑ ሰውን አስደስቷል - እኔም ከሰራኋቸው ስራዎች ይህ ፊልም ለየት ማለቱን አስተያየት እየደረሰኝ ነው:: ነገር ግን ፊልሙ ላይ ያለው ሃሳብ ደግሞ (የተነሱት ነጥቦች) ለብዙ ሰዎች ጥሩ መዝናኛ ነበር የሆነው:: የዚህን ምላሽ እዚያ በነበረው የአስተያየት ማሰባሰቢያ ወረቀት ላይ ብቻ የሰበሰብነው ሳይሆን በአሁን ወቅትም የኤድናሞል ተመልካች ስሜት ተመሳሳይ እየሆነ መጥቷል::

**ፊልሙ ላይ በአብዛኛው ያሳተፍከው ወጣት አክተሮችን ነው - በአዲስ ሃይል ትተማመናለህ?**

ታሪኩ ሲጀመርም ብዙም ትልልቅ ሰዎችን የሚፈልግ አይደለም:: በአዲስ ትውልድ ደግሞ ማመን አለብህ - ማበረታታት አለብህ:: «ባለታክሲው»ን እንዳየኸው ለውጤት ያበቃነው በወጣቶችም ጭምር ነው:: «የታፈነ ፍቅር» ደግሞ የበለጠ ወጣቱ በተመልካቹ ላይ የተለያዩ ስሜት ሲፈጥሩ የሚያሳይ ፊልም ነው:: ታለንት ያላቸውን ወጣቶች ወደ ኢንዱስትሪው ማቅረብም ትልቁ ዓላማዬ ነው:: እዚህ ላይም የተሳካው ይሄው  ነው::

**የታሪኩን ተሰናስሎትና (Chains) አጠቃላይ ጭብጥ ከአገራችን ነባራዊ ሁነት አንፃር እንዴት አየኸው?**

እንግዲህ ከዚህ በፊት የሰራነው ስራ ላይ «ባለታክሲው» ወስጥ የተነሱ ጥያቄዎች አሉ:: ፊልሙ ኢትዮጵያዊነት የለውም የሚል ነገር ይሰማ ነበር:: እንግዲህ ኢትዮጵያዊነት ታሪክ ነው:: በነገራችን ላይ መጀመርያ ፊልሙን ስንሰራ ሰው ካለበት ህይወት ወጥቶ የሌላን ሰው ህይወት የኔ ብሎ እንዲያስብና እንዲማርበትም ነው:: ይህንን «የታፈነ ፍቅር» ስናየው ግን በዕድሜ ልዩነት ... በማህበራዊ ህይወት ልዩነት ውስጥ ያሉ ሰዎች በቀጥታ በፍቅርና ጋብቻ ውስጥ ያለውን የህይወት እውነታ

የሚገልጽ አስቂኝም - አዝናኝም የፍቅር ፊልም ነው። ለዚህም ነው ተመልካቹ ጥሩ አቀባበል ያደረገለት።

**እንደሚታወቀው በአሜሪካን አገር በፊልም ተቋም ተምረህ ተመርቀሃል። እስካሁን የሰራሃቸው ፊልሞችም ስኬታማነታቸው ይነገራል። የተለየ አካሄድ የምትለው አለህ?**

አሁን እየሰራነው ያለው በተለያየ ይዘት ላይ መሰረት ያደረጉና ከመሰላቸት ወጣ ያሉ ፊልሞችን ነው። አንደኛ ራሴን ለመፈተንም ነው።ሁለተኛ የተመልካቹንም ስሜትና ፍላጐት ከመረዳት አኳያ ነው። ከዚያ በተረፈ እኔ ራሴ የምፈልጋቸው አካሄዶች አሉ።- በኢንዱስትሪው ውስጥ እንዲያብቡ የምፍልጋቸው። ወይም ራሴ ለመስራት የምፈልግበት መንገድ። ራሴ በምንዝበት መንገድ የሰራሁት ስራ እንዳልከው እስካሁን ውጤታማ ነው። እንደ ኢንዱስትሪ ስናስብ ግን ብዙ ማምረትና መስራት ይጠበቅብኛል ብዬ አስባለሁ።

**የኢትዮጵያ የሲኒማ እሴት (value) ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?**

የመጀመሪያው እሴት እውቀት ነው መሆን ያለበት። እሱ ካለን በማንኛውም ሁኔታ መስራት የምንችልበትን መንገድ እንፈጥራለን። የሚከብዱ ነገሮችም ቢኖሩብን እንሰራለን። ማንኛውም ሰው ቢያንስ ግንዛቤ ሊኖረው ከፍ ሲልም ዕውቀት ሊኖረው ሲችል የሲኒማ ኢንዱስትሪ የሚያሳየው የዕድገት ብርሃን ይሄዳል። ከዚያ በኋላ ወደ ካፒታልና ወደ ልምድ የምንሄድበት መንገድ ማመቻቸት ይመስለኛል።

**አሁን ባለበት ሁኔታ የፊልሙ ኢንዱስትሪ ጥሩ ነገር የለውም ትላለህ?**

የፊልሙ ዕድገት ለውጥ እያሳየ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ማለት ያስችላል። ጥሩ ታለንት/ክህሎት/ ያላቸው አክተሮች፣ ጥሩ ፀሀፊዎች - ጥሩ ዳይሬክተሮች እየተፈጠሩ ነው ያሉት። ጥሩ ለውጥ ሊያሳይ የሚችል ነገር እየታየበት ነው። በቀረጥና በታክስ ላይ ያለው ጫና የሁሉም እሮሮ ስለሆነ በዚህ ረገድ መንግስት ኢንዱስትሪውን የሚያበረታታ ስትራቴጂ እንዲነድፍ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

**በመጨረሻ . . .**

«የታፈነ ፍቅር» እንግዲህ ፍቅር ህይወት ላይ ያለ ወይንም ፍቅርን ያጣጣመ ሁሉ ሊያየው የሚገባ ሲኒማ ነው እላለሁ።

## Book Review

# *«አባቴ ያችን ሰዓት»፤* ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶና የግንቦት 1981 ዓ.ም *መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሲዳሰስ*

በ*ነአሚን ዘለቀ*

የመጽሐፉ ርዕስ:- *አባቴ ያቺን ሰዓት*

ደራሲ:- *ደረጀ ደምሴ ቡልቶ*

የመጽሐፉ ዳሳሽ:- *ነአሚን ዘለቀ*

ደራሲ ደረጀ ደምሴ *«አባቴ ያቺን ሰዓት»* በሚለው መጽሐፉ፣ የአባቱን ሜጀር ጄነራል ደምሴ ቡልቶን ታሪክ ይተርክልናል። ደረጀ ስለወላጅ አባቱ የግልና የመንግስትታዊ ኃላፊነት ሕይወትና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይሎች ታሪክ መነሳትና መውደቅ ጋር ስለተቆራኙ ሌሎች ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች ይተርክልናል፤ ስለአባቱ ሕይወትና ስለሰጡት ወታደራዊ አገልግሎት ከዚህ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ሰራዊት ታሪክ ይነሳና በ1981 ዓ.ም አሳዛኙ ሕልፈታቸው እስከ ተከሰተበት ድረስ ባለው ታሪክ ዙሪያ ያጠነጥናል። በተጠቀሰው ዓመት፣ ጄኔራል ደምሴ በኢትዮጵያ ብቸኛውን ግዙፍ ወታደራዊ ጦር በሜጀር ጀኔራልነት ማዕረግ አዛዥ በመሆን የወታደራዊ አዛዥነታቸው ጉልላት ላይ ለመቀመጥ የደረሱበት ወቅት ነበር። መጽሐፉ ልጅ ስለተወዳጅ አባት ሕይወት ከሚተርከው በላይ ነው።

ድርሰቱ ተጀምሮ እከሚጠናቀቅበት ድረስ፣ ጥልቅ የአባትና ልጅ ቅርርብ ያለው ግለ-ሕይወትን ዘመናዊ የአፍሪካ አንድ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ለመመስረትና ቀጣይ ለማድረግ የተደረገ ሙከራን ከታላላቅ ታሪካዊ ክንውኖች ጋር በጥበባዊ መንገድ በማያያዝ የተረከ ነው። ብቃት ባልነበረው በአብዮታዊው ደርግ ቁጥጥር ስር ስለነበረው የኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይል መነሳትና መፍረክረክ፣ በሁሉም የጦር አውድማዎች ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ስለተሳተፉባቸው የወታደራዊ ኃይሉ ድሎችና ሽንፈቶችም በድርሰቱ የተዘረዘሩ ናቸው።

የጄኔራል ደምሴ የውትድርና ሕይወት የተጀመረው ገና ንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ የኢትዮጵያን ወታደራዊ ኃይል ዘመናዊ ለማድረግና መሉ በሙሉ እንደምዕራብያውያኑ ተዋጊ ኃይል ለመለወጥ የመጀመሪያ ሙከራቸውን ባደረጉበት ወቅት ነው ማለት ይቻላል። ጄኔራል ደምሴ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ የነበረውን ***ክቡር ዘበኛ*** የተቀላቀሉት በሶስተኝነት ለስልጠና ከተመለመሉት ጋር በእጩ ኦፊሰር በመሆን ነበር። ያ በኢትዮጵያ ታሪክ የተነገረለት የማርሻል ታሪክ ውስጥ ታላቅ ተሞክሮ ነበር። በመሆኑም የደምሴ የሰልጣኝነት ዓመታት ምናልባት በጣም በእውቀት የታነፁበት ወቅት ነበር። ከሶስት

ዓመታት በጣም አርኪና በደስታ የተሞላ የስልጠና ቆይታ በኋላ ደምሴና አብረው ከእርሳቸው ጋር ይሰለጥኑ የነበሩ ሰልጣኞች ወዲያው የዩ.ኤስ. ጦር መርከብ በሆነው ዮ.ኤስ.አስ. ራድፎድ ተጫኑ፤ የተለመደው የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ሳይደረግ በሌተናንትነት ወደ ኮሪያ ኮሚሽን ተደረጉ:: ወቅቱ የኮሪያ ጦርነት ነበር:: ንጉስ ኃይለስላሴ ኃያላን ምዕራብያውያንን ለማስደመም በመጓጓት በተ.መ.ድ ስር በነበረው ዩ.ኤስ. 7ኛ እግረኛ ክ/ጦር አካል እንዲሆን ለኮሪያ ዘመቻ ለአራት ተከታታይ ጊዜ ፍቃደኛ ሆኖ:: ይህም የኮሪያ ዘመቻ ጄኔራል ደምሴ ለሶስት አስርት ዓመታት ከተሳተፉባቸው በርካታ ዘመቻዎች በመጀመሪያነት የሚጠቀስ ነው::

ደረጃ የሚተርከው ታሪክ አንዳንዴ የግል ጀብደኝነትንና ሌላ ጊዜ ደግሞ ቆራጥነት እንዲሁም በጦርነት አይቀሬውን የሞራል ወዠንብር ያካተተ ነው:: የሰሜኑን ጦርነት ፍፃሜ ለመስጠት ወሳኝ የፖሊሲ ለውጦች እንዲተገበሩ ምሁራዊና ሙያዊ ምክራቸው በተደጋጋሚ በአምባገነናዊው መሪ ተቀባይነት በማጣታቸውና መንግስት የአገሪቱን የውስጥ ችግሮች ለመቅረፍ ፓለቲካዊ መፍትሄ ለመፈለግ እምብኝ በማለቱ በመሰላቸት ሶስት ከፍተኛ ወታደራዊ አዣዦች - ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ - ቺፍ ኦፍ ስታፍ፣ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ - የኢንዱስትሪ ሚኒስትርና የቀድሞ አየር ኃይል አዛዥ እና የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊትና ከ200 ሺህ በላይ ጠንካራ ሰራዊት አዛዥ የነበሩት ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ - መንግስትን ለመገልበጥ አደገኛ ውጥን ለመንደፍ ወሰኑ:: ብዙዎችን የውጥናቸው ተሳታፊ እንዲሆኑ በማሳመን በመንግስቱ ኃ/ማርያም ላይ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አደረጉ::

በመፈንቅለ መንግሰቱ የመጀመሪያ ቀን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ የተደረገው መፈንቅለ መንግስት በከሸፈበት ወቅት፣ ጄኔራል ደምሴ ሙከራቸውን በወቅቱ ሁለተኛዋ ግዙፍ ከተማ በነበረችው አስመራ ገፉበት:: ጄኔራል ደምሴ ለሶስት ተከታታይ ቀናት፣ አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲያበቃና የውክልና መንግስት እንዲመሰረት ጥሪያቸውን ማቅረብ ቀጠሉ:: ሻዕቢያም የ15 ቀናት የቶክስ አቁም ስምምነት በመስማማቱ አምባገነኑን መንግስቱ ኃ/ማርያምን እየጠበቋቸው የነበሩ የቤተ-መንግስት ጠባቂዎችን ለማስወገድ ወደመዲናዋ ወታደሮችን ለማዝመት ዝግጅቶች መካሄድ ጀመሩ:: እቅዱ አደገኛ የነበረና ከጊዜ ወደ ጊዜም የስኬት እድሉ የእየመነመነ የመጣ ነበር:: ያም ቢሆን ጀኔራል ደምሴ በአስመራ አየር ኃይል በራሳቸው ቁጥጥር ስር በነበሩ በአንዱ አውሮፕላን በመሳፈር ሕይወታቸውን ለማትረፍ ከመሸሽ ይልቅ እስከመጨረሻ መፋለምን መረጡ:: ደረጀ፣ ልክ በዚህ ወሳኝ ሰዓት አባቱ የተጋፈጡትን ኃያል ፈተና እና ያሳዩትን ጀብደኝነት በጥልቀት ይዳስሰዋል::

በመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ ወቅትና በኋላ ብቃት ያላቸው ጄኔራሎች መጨፍጨፋቸውና በመቶዎች የሚቆጠሩ አዛዦች መታሰራቸው ለኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይሎች መገርሰስ እንደምክንያት በዋናነት ከሚጠቀሱት የሚቀመጥ ነው:: ከፍተኛ ሙያተኞቹን፣ ጀግና መሪዎቹን እና አዛዦቹን በማጣቱ ሰራዊቱ የአማፂ ኃይሎቹን

ግፊት ሊቋቋም አልተቻለውም:: በበርካታ ገጽታዎች ተቃርኖዎች በመታጀቡና በጣም ቅራኔ ካደረበት ሕዝብ ከመቼውም በበለጠ በመነጠሉ፣ በግንቦት 1981 ከተሞከረው መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ የኮሎኔል መንገስቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ የሻዕቢያንና የሕውሓትን ጥቃት ለመቋቋም የተቻለው ለሁለት ዓመታ ብቻ ነበር:: የሥርዓቱ መገርሰስ አሁንም በስልጣን ላይ የሚገኘውን የሕውሓት/ኢሕአዴግ መንግስትን አስከተለ::

በርካታ ጸሐፊዎች፣ ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ሩቅ ተመልካችና ምጡቅ ወታደራዊ አእምሮአቸውንና የለገሱትን ወሳኝ ወታደራዊ አመራር በማዳነቅ በጣም በሚያሞጋግሱ ቃላት ጽፈውላቸዋል:: በዘመናዊው የኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይል ላይ ያተኮረ፣ ***«የኢትዮጵያ አብዮት»*** በሚል ርዕስ በእንግሊዘኛ በታተመ አዲስ ትምህርታዊ መጽሐፍ፣ ዶ/ር ገብሩ ታረቀ ከሶማሊያ ጋር በተካሄደው ጦርነት የጄኔራል ደምሴን የወታደራዊ አመራርነት ብቃት እንደሚከተለው ገልፀውታል:- *«የሶማሊያ ዘመቻ የተመራው በነበራቸው የስትራቴጂ አነዳደፍ ምልከታ፣ ስብዕና፣ ዲሲፒሊን እና ወሳኝነት ታላቅ ዝናን በተላበሱት ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ነበር:: እነዚህ መገለጫዎች ከባልደረቦቻቸውና ከወታደሮቻቸው አድናቆትንና ቆራጥነትን ያጎናፀፏቸው ነበሩ:: እነርሱም በተራቸው በከፍተኛ ተነሳሽነትና ጽናት አብረዋቸው ይፋለሙ ነበር:: ጄኔራል ደምሴ አዝማች አዛዦቻቸው መሉ በሙሉ ኃላፊነቱን እስከወሰዱ ድረስ በራሳቸው ወታደራዊ እርምጃ እንዲወስድ በቂ ነፃነት ይፈቅዱላቸው ነበር:: ለተወሳሰበ ሁኔታ የእነዚህ የተቀናጁ ምላሾች በጣም ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋገጡ ናቸው::»*

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በፖሲፊክ ግንባር የጃፓንን ሽንፈት የመሩት እና ጄኔራል ደምሴ ገና የኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ውስጥ ሌተናንት በነበሩበት ወቅት ያስለጠኗቸው አማሪካዊው ጀኔራል ማክአርተር አንዴ እንዲህ በለው ነበር:- ***«አንጋፋ ወታደሮች በጭራሽ አይሞቱም፣ ቢደበዝዙ እንጂ::»***

ደረጃ በመጽሐፉ የጄኔራል ደምሴን ትውፊትና አብረዋቸው ኢትዮጲያን ያገለገሉ ወታደሮችን ግልጽ በሆነ ማብራሪያ ዳግም ሕይወት ዘርተውባቸዋል:: መጽሐፉ የኢትዮጵያን የአንድ ትውልድ አርበኝነት፣ ጀግንነትና ሙያተኝነት የሚመሰክር ነው:: ከትውልዱም የአሁኑ ትውልድ ጥንካሬንና መነቃቃትን ሊያገኝ ይገባል::

እንደሌሎች ጥሩ የስነጽሁፍ ስራዎች፣ መጽሀፉ ቅርስ ተደርጎ የመቀመጥ ብቃት አለው:: የአይን ምስክሮችን እማኝነት፣ በመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ የተሳተፉ ቁልፍ ግለሰቦችን ቃለ-መጠይቅ እና የተለያዩ የታተሙና ያልታተሙ ስራዎችን በማጣቀስ ለ17 አመታተ የተደረገ ጥናቶችን ያካተት ነው:: በተጨማሪ በአሜሪካ መረጃ የማግኘት ነፃነት ሕግን በመጠቀም ከአሜሪካ ውጭ ጉደይ መስሪያ ቤት የተገኙ መረጃዎችንም በመጠቀም የተጻፈ ነው::

በሰሜን ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ላይ በታወጁ ሁለት በጣም ስኬታማ ዘመቻዎች ወቅት በጄኔራል ደምሴ ቡልቶ የተፃፉ ዕለታዊ ግለ-ታሪኮች በመጽሀፉ ተካቷል:: ዘመቻ

ባሕረ ነጋሽና የቀይ ባሕር ዘመቻ በንድፋቸውና በትግበራቸው ውስብስብነት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ዘመቻዎች ናቸው:: ዘመቻዎቹንና ትግበራቸውን የመሩት ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ነበሩ::

# ስፖርት

## ያልተጠናቀቀው ጠ/ጉባዔ

## የሳህሉ «ተባበሩን» የት ድረስ?

**መስከረም 27 እና 28 የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በሀዋሳ የመጀመሪያውን ጠ/ጉባዔ ሲያካሂድ የተከታተለው የአውራምባ ታይምስ የስፖርት ገጽ አዘጋጅ አቤል አለማየሁ የጉባዔውን የሁለት ቀን አንኳር ውሎ እንደሚከተለው ጽፎታል::**

የሲዳማ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ በዓል «ፊቼ» በመስከረም አጋማሽ ሀዋሳ ላይ ይከበራል:: በ«ጉዱማሌ» (በዓሉ የሚከበርበት ቦታ ስም) በዓሉን ለማክበር ከሀዋሳ፣ አካባቢዋና ከውጪ ሀገራት በሚመጡ የብሔሩ ተወላጆች፣ ከውስጥና ከውጪ ሀገር ከበዓሉ ትሩፋት ለመቋደስ በሚመጡ ቱሪስቶች ሀዋሳ ትደምቃለች:: በባጃጅ ታክሲ የታጨቀችው የደቡቧ መዲና የመስከረም ወርን ሳትሸኝ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የክልል ተወካዮች የሚሰባሰቡበት ሌላም አጋጣሚ ነበራት፤ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባዔ::

ሐምሌ 11/2001 ዓ.ም በተደረገ ምርጫ ወደ ፌዴሬሽኑ የመጡት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት አንዱ ከሆኑት አምባሳደር ተወልደ ገብሩ በስተቀር ቀሪዎቹ አባላት በሙሉ በመድረክ በተገኙበት በዚህ ጉባዔ ላይ በፊፋ እውቅና ያልተሰጠው ፌዴሬሽን አሻሽሎ አዘጋጅቶት በነበረው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ መካተት ይገባቸዋል ያሏቸውን አንቀጾች በማካተት ፌዴሬሽኑ ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ ለአንድ ቀን ተኩል አወያይቷል::

በውይይቱ የጠቅላላ ጉባዔ አባላቱን ቀልብ በእጅጉ ገዝተው ለመናገር እድል እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ በርካታ እጆችን ከፍ ካስደረጉ ነጥቦች መሀከል የመተዳደሪያ ረቂቅ አንቀጽ 8/2/ሠ ላይ የሰፈረው «አንድ ክለብ ሲፈርስ ንብረቱን ፌዴሬሽኑ በአዳራነት ይረከበዋል» የሚለው ሲሆን አንቀጹ በብዙሐኑ ተሳታፊዎች ተወግዟል::

ክለቦች ሲፈርሱ ያፈሩትን ንብረት ላቋቋሚቸው አሊያም ተጠሪነት ላለው አካል መሰጠት አለበት እንጂ በክለቦች ንብረት ፌዴሬሽኑ ማዘዝ አይገባውም በማለት «እንዴት?» ሲሉ የተከራከሩት ክለቦቹ አንቀጹ እንዲሰረዝ ጠይቀው በሙሉ ድጋፍ

ፀድቋል:: «ክለቡ የሚፈርስ ከሆነ ከፈለገ ለቀበሌ መስጠት ይችላል» ብለዋል በጉባዔው ላይ አንድ ተሳታፊ::

## ትውስት

ዓለም የሚሰራበት ተጨዋቾችን በትውስት የመጠቀም ዘዴ በሀገራችን የተለየ የሚመስልበት ወቅት አጋጥሟል:: ባለፉት ዓመታት በተከታታይ ከብ/ሊግ ወደ ፕሪምየር ሊግ ለማለፍ እድላቸውን ያሰፉ አራት ቡድኖች የዙር ጨዋታቸውን ማድረግ ከመጀመራቸው በፊት ከሀገሪቱ ትልልቅ ቡድኖች እየተዋሱና እየመነተፉ ቢሳካም ባይሳካም ጉዟቸው እንዲሰምር ሲጣደፉ ይስተዋላል:: ይህን የአንድ ሰሞን ተገቢ ያልሆነ እሽቅድድም «ይገታል» የተባለ ደንብ ፀድቋል:: ማንኛውም በብ/ሊግ የሚወዳደር ክለብ በፕሪምየር ከሚወዳደር ዋና ቡድን ተጨዋች «በትውስት» ማግኘት እንዳይችል ተወስኗል:: በፕሪምየር ሊግ ከሚገኙ ወጣት ቡድኖች ተጨዋቾችን ማዘዋወር ግን ተፈቅዷል:: የትውስት ጊዜ በተጨዋቾች የዝውውር ወቅት ማለትም የሊግ ውድድሮች እንከሚጀመሩበት ጊዜ ድረስ ይፈቀዳል:: አንድ ክለብ በትውስት ማግኘት የሚችላቸው የተጨዋቾች ብዛት በሦስት ተገድቧል::

በዶ/ር አሸብር የሚመራው ፌዴሬሽን በ1997 ዓ.ም ያወጣው መተዳደሪያ ደንብ ከአምስት ክለቦችና ከአንድ የክልል ፌዴሬሽን (መስተዳድር) የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል ማንኛውም ግለሰብ ለፕሬዚዳንትነትና ለስራ አስፈፃሚነት መወዳደር እንደሚችል ይደነግጋል:: ይህ አንቀጽ በዚህ ጉባዔም ድጋፍ አግኝቶ ፀድቋል:: በእጩነት ለመወዳደር «መተዋወቅና የጉንዮሽ ትስስርን የሚጠይቅ» ተብሎ ለበርካታ ጊዜያት የተተቸው ይህ አንቀጽ ላይ ማሻሻያ አለመደረጉ ግራ አጋብቷል::

ክለብ አልባ የሆኑት ጋምቤላ፣ አፋር፣ ቤንሻንጉልና ሱማሌ እጩ ማቅረብ ከፈለጉ ከክልል ፌዴሬሽን ብቻ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ ተብሎ በቤቱ ይሁኝታ አግኝተዋል:: ለአውራምባ ታይምስ አስተያየት የሰጡ «በቀጣዩ ምርጫ ሁሉም የእነዚህ ክልል አባል ሆኖ ለመወዳደር አስቀድሞ ሩጫ እንዲጀምር በር የሚከፍት» ሲሉ ደንቡን ተችተውታል::

ከአንድ የጉባዔው ተሳታፊ «ፊፋ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከሚሰጠው ገንዘብ ላይ ለክልል ፌዴሬሽኖች የመስጠት ግዴታ አለበት» የሚል ጠንከር ያለ ጥያቄ ያነሱ ሲሆን የኢ.እ.ፌ ም/ፕሬዚዳንት የሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ወንድሙ ታደሰ «ፊፋ ገንዘብ የሚለቀው ፕሮፖዛል ተመልክቶ ነው:: ለክልሎች ጥሬ ገንዘብ ቆጥረን አንሰጥም:: ወደ ልማት እንዲለወጥ ግን እናደርጋለን» ሲሉ ፊፋ ከሚልከው 250 ሺህ ዶላር ላይ «የድርሻችንን?» ላሉት ሰው ምላሽ ሰጥተዋል::

## እምቢ 18 / 20?

በጉባዔው ላይ አስተያየት የሰጡ የክለብ ኃላፊዎች በቀጣዩ ዓመት በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የሚወዳደሩ ክለቦች ቁጥር ሁለት ጨምሮ 18 መሆኑ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ሳህሉ ሲያሳውቁ ከፍተኛ ተቃውሞ በጉባኤው ተሰምቷል:: «የበጀት

አቅማችንን የምንወስነው ክለቦች ሆነን ፌዴሬሽኑ የተወዳዳሪ ክለቦችን ቁጥር በመጨመር ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርገን አይገባውም» ብለዋል የክለብ ተወካዮች። «ይህ የአቅጣጫና የመተባበር ጉዳይ ነው። ለዚህ ዓመት ብቻ እባካችሁ ተባበሩን» ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ተማጽኖ ቢያቀርቡም «እሽታ» ማግኘት ግን ሳይችሉ ቀርተዋል። የኢትዮጵያ ቡና የቦርድ አባል የሆኑት ሻምበል ሀለፎም «ይህ የሚደረገው የተወሰኑ ክለቦችን ለመጥቀም ሆን ተብሎ ነው። አቅም የለንም፣ አንችልም።» ያሉ ሲሆን «ወይ አንደኛውን 36 እናድርገው» ሲሉ ቁጣ በተቀላቀለበት ሁኔታ ተናግረዋል። የደቡብ ፖሊስ ቡድን ተወካይ በበኩላቸው «ቁጥሩ ከፍ ካለ ላንወዳደር እንችላለን» ሲሉ አሳውቀዋል። የሜታ ቢራ ተወካይም ተቃውሟቸውን አቅርበዋል። የቅ/ጊዮርጊስ ክለብን ወክለው በጉባዔው ላይ የተገኙት አቶ ነዋይ በየነ ይህ ውይይት በሚደረግበት ወቅት በአዳራሹ አልነበሩም። አንድ አንድ የጠ/ጉባዔው አባላት በይሉኝታ ታጥረው በአዳራሹ አስተያየት ባይሰጡም በደጅ በማዘን ቅሬታ ሲያቀርቡ ነበር።

እንደ አቶ ሳህሉ ገለፃ ከሆነ ተጨማሪዎቹ ሁለት ቡድኖች ወደ ፕሪምየር ሊግ የሚገቡት ደደቢት፣ ሻሸመኔ ከነማ፣ ኒያላና ትራንስ ኢትዮጵያ በአንድ ዙር በሚያካሂዱት የዙር ጨዋታ የተሻለ ነጥብ ማስመዝገብ የቻሉት ናቸው። አውራምባ ታይምስ በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባለሆነ መልኩ ያነጋገረቻቸው በርካታ የጉባዔው ተሳታፊዎች የቁጥሩን 18 መሆን በእጅጉ ተቃውመውታል። የፕሬዚዳንቱ ለዚህ ዓመት ብቻ የ«ተባበሩን» ልመና ሊዋጥላቸው እንዳልቻለ እንዲሁም በጀታቸውን 16 ቡድንን ማዕከል ባደረገ መልኩ አውጥተው በመጨረሳቸው በ18 ከፀና በቀጣይ ወዴት አቅጣጫ ሊሄዱ እንደሚችሉ እርግጠኛ እንዳላደረጋቸው ገልፀውልናል። «ክለብ ማቋቋም እንጂ ማፍረስ ቀላል ለሆነበት ሀገር ውሳኔው ጥሩ መልዕክት የሌለው» ብለውታል። «ፌዴሬሽኑ ወስኖ ከጨረሰ በኋላ "ተባበሩን" ማለቱ «የሚጣረስ ሁለት ሀሳብ ነው።»

## መራር ቅዋሜ

በጉባዔው ላይ በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ አባላት የሚመሩ ንዑሳን ኮሚቴዎች አባላት ስም ዝርዝር በተገለፀበት ወቅት በርካታ ቅሬታዎች ተስተናግደዋል። አቶ አፈወርቅ አየለ የሚመሩት የውድድርና ስነ-ስርዓት ኮሚቴ አብላጫ ቅሬታ በማስተናገድ ቀዳሚ ሆኗል። በተለይ አቶ አፈወርቅ ስለ ሰዎቹ ማንነት ሲገልፁ «ስታዲየም የሚገባ» በሚል እንደ አንድ መስፈርት መጠቀማቸው አላግባባም። የጠቅላላ ጉባዔው አባላት «እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ችግሮች የተፈጠሩት በዚህ ኮሚቴ አማካኝነት መሆኑ እየታወቀ የማይታወቁ ሰዎች መጠቆማቸውና ስታዲየም ይገባል መባል እንደ መስፈርት መቆጠሩ ስህተት ነው።» በማለት «አናውቃቸውም ድምጽ አንሰጣቸውም» ብለዋል። የጉባዔው አባላት «አዳዲስ ሰው ይመረጥ» እያሉ የተመረጡትም አዲስ መሆናቸው እየተነገረ መግባባት አለመፈጠሩ እንቆቅልሽ መኖሩን የጠቆመ ሲሆን ጥርጣሬው የቱጋ እንደሆነ በግልጽ አልተነገረም። ጥቅምት 14 ክለቦች ከፌዴሬሽኑ ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ስላላቸው በዚያ ወቅት ጥቆማ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩበት ተነግሯል።

ሌላው ቅሬታ የቀረበበት በረዳት ፕሮፌሰር ወንድሙ የቀረበው የቴክኒክ ኮሚቴ ነው:: አሰግድ ተስፋዬ፣ (የኢትዮጵያ ቡና ተጨዋች የነበረ) ኤፍሬም ግዛቸው (የቅ/ጊዮርጊስ የቴክኒክ ኮሚቴ አባልና የቡድን መሪ የነበረ) ሽዋ ረጋ ደስታ (የኢትዮጵያ ባንኮች ተጨዋች የነበረ) ከስድስቱ የኮሚቴ አባላት ሦስቱ ሲሆኑ «ለቀድሞ ክለባቸው ድጋፍ እንደማያደርጉ በምን ርግጠኛ መሆን ይቻላል?» ሲሉ ጠይቀዋል የጉባዔው አባላት:: አሰራሩ ጥርጣሬ እንደያሳድር፣ ግልጽና የጠራ እንዲሆንም የሦስቱ ስም እንዲወጣ ተጠይቋል:: ለውሳኔም ለጥቅምት 14 ተቀጥሯል:: በዳኞች ኮሚቴ ስር ሰማቸው የተጠራው ዓለም ንፀብቅ በርካታ ተቃውሞ ቀርቦባቸው እንዲሰረዙ ተደርጓል::

በሌላ በኩል የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት እንዲመሩ የተመረጡት አቶ ሰለሞን አለምሰገድና የዳኞች ኮሚቴ የሚሰሩት ኢንስትራክተር ሽፈራው እሸቱ (ሁለቱም በቀድሞ ጊዜ በአርቢትርነት ሰርተዋል) «ለቦታው ተገቢና የሚመጥኑ» ተብለው ተሞካሽተዋል::

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ፌዴሬሽኑ ከረዥም ጊዜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሀዋሳ ላይ አጭር ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል:: አውራምባ ታይምስ ለፕሬዚዳንቱ «የክለቦች ቁጥር 18 ይሁን በመባሉ ክለቦች በዚህ ቅሬታቸውን በግልጽ ተናግረዋል፤ የኢንተርናሽናል ባጅ ለማግኘት የሚደረገውን ፈተና የወደቁ ዳኞች ስም በድጋሚ እንዲተላለፍ ተደርጓል:: ይህ ደፍሮ ውሳኔ መወሰን ካለመቻል የመጣ ነው:: ይህ የማቻቻል አካሄድ ፌዴሬሽኑ የመጀመሪያ ፈተናውን በአግባቡ እንዳልተወጣ አያሳይም?» ተብሎ ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን «ችግሩ የተፈጠረው የነበረው ፌዴሬሽን (በፊፋ እውቅና ያልተሰጠው) የልማት ስራዎችና ውድድሮችን እያከናወነ ሲያግዝ በሁለት ትልልቅ ተልዕኮዎች መሀከል በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት ነው:: ዞሮ ዞሮ ጉባዔተኛው ተቀብሎት ነው የሄደው ይህም በራስ መተማመናችንን እንድናጉለብት አድርጉናል:: (ይህ ከጉባዔው አባላት መንፈስ ጋር ተቃራኒ ይመስላል) ያለተመቻቹ ነገሮችን ጠራርገን ለ2003 ዓ.ም የምናዘጋጅበት ዓመት በመሆኑ ማቻቻል በዝቶብናል ትክክል ነው:: ይህ ግን ሰላምና አንድነትን ለመፍጠር ነው» ብለዋል::

«ዳኞችን ውጤታቸውን አስቀምጠን በደረጃ ልከናል:: ፊፋ ሁኔታውን ያጤነዋል ብለን እናስባለን:: ይህ ካልሆነ ግን ውጣ ውረድ ያለ ነው እንቀበላለን» ሲሉ መልሰዋል:: «በኮሚቴና በንዑሳን ኮሚቴ ውስጥ የመንግስት አካላት ስም በዝቷል:: ይህ መንግስት ላይ ያላችሁን ጥገኝነት አያሳይም?» ተብሎ ከአውራምባ ታይምስ ተጨማሪ ጥያቄ ቀርቦላቸው «ብዙ ክለቦች በመንግስት የሚተዳደሩ ናቸው:: ክለቦች በግል ሲተዳደሩ በዕድገቱ ጋር አብረን እንጓዛለን:: የመረጥናቸው የመንግስት አካላት ቢሆኑም ጊዜያቸውን መስጠት የሚችሉትን ነው::» ብለዋል::

በተያያዘ ዜና በዚህ ዓመት ከወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከስታዲየም ማስታወቂያ፣ ከፊፋ፣ ከሼል ማደያ (ስታዲየም አጠገብ የሚገኝ ነው።)፣ ከፓርኪንግ ኪራይ፣ ከስታዲየም ገቢ፣ በክለቦች ምዝገባ ፣ ከደ/አፍሪካ የዓለም ዋንጫ የቴሌቭዥን ማስታወቂያ በድምሩ 16.8 ሚሊየን ብር ለማግኘት አቅዷል።

በጉባዔው ላይ ከሀገራዊ አስተሳሰቦች ይልቅ ክልላዊ፣ ክለባዊና ግለሰባዊ አስተያየቶች እንደነበሩ የአስተያየት ሰጪዎች ገልፀው «እኔ» ከሚል የሚነሱ አስተያየቶች መልካም አይደሉም ብለዋል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠ/ጉባዔውን ያድርግ እንጂ ውሳኔዎችን አሳልፎ አላጠናቀቀም። ለጥቅምት 14 በይደር ያሳቀመጣቸው ጉዳዮች አሉት። ከእነዚህም ዋነኛው የዲስፕሊን ረቂቅ ደንብ ነው።

በማቻቻል የተጀመረው አዲሱ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አሰራር ከ«ተባበሩን» ጥያቄ ቀጥሎ ወዴት እንደሚጓዝ ማንም እርግጠኛ አልሆነም።